
# አማርኛ

## እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ



## ስምንተኛ ክፍል

ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ

# አማርኛ

# እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ

## ስምንተኛ ክፍል


የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ

አዘጋጆች

ትዕግስት ዳዊት/MA/

ማርቆስ በላቸው

መኮንን ሆርዶፋ

አርታኢ

ፍቅርተ መኮንን/MA/

ጥራት ተቆጣጣሪዎች

አወቀ ጸጋዬ / MA/

እንግዳ ዘውዴ (ዶ/ር)

የማጣሪያ ንባብ

ምስራቅ ጠና (ዶ/ር)

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በኩል በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ሲሆን የኢ.ፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ እና በዲላ ትምህርት ኮሌጅ የቴክኒክ ድጋፍ በ አማርኛ_ቋንቋ የተዘጋጀ ሲሆን አጠቃላይ የሕትመት ወጪው በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተሸፍኗል፡፡

የመጽሃፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት © 2014 ዓ.ም የኢ.ፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ናቸው፡፡

## መግቢያ

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው፡፡ መጽሐፉ አስር ምዕራፎችን ይዟል፡፡

በአስሩ ምእራፎች ውስጥ የተነሱት ርእሶች ወቅታዊነት ባላቸው አገራዊና ክልላዊ ጉዳዮችና ጭብጦች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ በየምእራፎቹ ውስጥ ለትምህርት የቀረቡት ይዘቶች ከትምህርቱ ውጤት ጋር ትስስር እንዲኖራቸው ታቅደው የተዘጋጁ ሲሆኑ አቀራረባቸውም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ የመማር ደረጃን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

በየምእራፉ መነሻ ላይ ከተማሪው የሚጠበቁ ውጤቶች በአጭሩ ተገልጸዋል፡፡ ውጤቶቹ የሚለኩና ከትምህርቱ በኋላ የተማሪዎቹን ለውጥ በግልጽ ያሳያሉ ተብለው የታቀዱ ናቸው፡፡ከተማሪዎች የሚጠበቀው ውጤት በቋንቋው የማዳመጥ ፤የመናገር ፣የማንበብና የመጻፍ ክህሎት ሲሆን፤ እነዚህ ክሂላት በቃላትና በሰዋስው አጠቃቀም እየታገዙ፣በስነ ጽሑፍ ዘውጎች መሳሪያነት እየዳበሩ በትምህርቱ ለተግባር ልምምድ ቀርበዋል፡፡

እነዚህ ልምምዶች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከመማሪያ ክፍል ውጭ በመኖሪያ ቤት በወላጆች ድጋፍ የሚተገበሩ ይሆናሉ፡፡ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚከናወኑት ልምምዶች የመምህር ድጋፍና ክትትልን የሚሹ ቢሆንም የተማሪዎችን የጋራ ስራና ተሳትፎ ያማከለ አሰራርን የሚያረጋግጡ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

## ማውጫ

ምእራፍ ገጽ


ምዕራፍ አንድ፦ የሕይወት ቅመም………..……………………………….. 1

ምዕራፍ ሁለት፦ የህይወት መመሪያ……………………………………….12

ምዕራፍ ሶስት፦ የሰው ልጆች አቅም ………………………………… .21

ምዕራፍ አራት፦ አካቶ ትምህርት ………………………….................34

ምዕራፍ አምስት፦ የተሰደዱ ስሞች ………………………………... 44

ምራፍ ስድስት፦ ወዳጅ ሲከዳ…...…………………………………… 55

ምዕራፍ ሰባት፦ ኮተት………. ………………………………………… ..64

ምዕራፍ ስምንት፦ ወራሾቹ……………………. …………………………. 84

ምዕራፍ ዘጠኝ፦ አባይ …………………..………………………………. 93

ምዕራፍ አሥር፦ ሀብታሙ ሰው……………………………………… 103.

## ምዕራፍ አንድ

## የሕይወት ቅመም

|  |
|---|
| የሚጠበቁ ውጤቶች<br>ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ<br>• ምንባብ አዳምጣችሁ አስተያየት ትሰጣላችሁ፡፡<br>• በቀረበላችሁ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ውይይት ታደርጋላችሁ፡፡<br>• የቃላትን ፍች በቃል ትገልጻላችሁ፡፡<br>• በምንባቡ መሠረት ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ፡፡<br>• የምንባቡን ዋና ሃሳብ ትገልጻላችሁ፡፡<br>• የአረፍተ ነገር ክፍሎችን ለይታችሁ ትጽፋላችሁ፡፡<br>• አንቀጽ ትጽፋላችሁ፡፡ |

አንደኛ ሳምንት፡- አንደኛ ቀን

ትምህርት አንድ ፡- ማዳመጥ

ተግባር አንድ

*መምህራችሁ ምንባብ ያነቡላችኋል፡፡ ምንባቡን ከማዳመጣችሁ በፊት ከዚህ በታች የተመለከቱትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡*

- የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች የሚመስላችሁን መልስ ስጡ፡፡

1. ቤተሰቦቻችሁ ገንዘብ ለምን ጉዳይ ይከፍላሉ?
2. ቤተሰቦቻችሁ የትምህርት ቤት ክፍያ በምን ምክንያት ይከፍላሉ?
3. መንገዶች የሚገነቡት በማን ወጪ ይመስላችኋል?

*ከዚህ ቀጥሎ መምህራችሁ ስለ ግብር/ታክስ አንድ አጭር ምንባብ ያነቡላችኋል፤እናንተ በትኩረት አዳምጡ፡፡*

- የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄ

ተግባር ሁለት ፡ በማዳመጥ ጊዜ መምህራችሁ ማንበባቸውን አቋርጠው ጥያቄ ሲጠይቋችሁ እናንተ በቃል መልሱ፡፡

መንግስት የሚያወጣውን ወጪ የሚሰበስበው ከየት ነው?

- የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ተግባር ሶስት ፡- ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሠረት አድርጋችሁ የሚከተሉትን

ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. ታክስ የሚከፈለው ለምንድን ነው?
2. ታክስ የሚከፍለው ማነው?
3. ታክስ መክፈል ግዴታ ነው?
4. መንግስት ለትምህርት የሚያወጣው ወጪ ከየት ይገኛል?

**አንደኛ ሳምንት፡ ሁለተኛ ቀን**

**ትምህርት ሁለት፡ መናገር**

<u>በታክስ ጉዳይ ላይ የተሰጠውን የመምህር ማብራሪያ ካዳመጣችሁ በኋላ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ጥንድ በመሆን ተወያዩ፡፡</u>

1. ቀደም ሲል ስለ ግብር / ታክስ የነበራችሁ ግንዘቤ ምን እንደነበር አስታውሳችሁ ከጓደኛችሁ ጋር ተነጋገሩ፡፡
2. የመምህራችሁን ገለጻ ካደመጣችሁ በኋላ በውይይታችሁ ያገኛችሁትን የጋራ መልስ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
3. ግብር /ታክስ/ ምን እንደሆነ ቤተሰቦቻችሁን፣ በአካባቢያችሁ የምታገኟቸውን የመንግስት ሰራተኞችና ነጋዴዎችን ጠይቃችሁ መልሱን በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ ለሚኖራችሁ ውይይት አዘጋጁ፡፡

## አንደኛ ሳምንት ፤ ሶስተኛ ቀን

1. በግብርና በታክስ ጉዳይ ላይ ወላጆቻችሁ የነገሯችሁን ሃሳብ ለክፍል አቻዎቻችሁ ንገሩ ፡፡
2. መልሳችሁ ልዩነት አለው? ልዩነት ካለው ልዩነቱን ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡ የሰጧችሁን መልስ አንደገና ተወያዩበት፡፡
3. በአካባቢያችሁ ያገኛችኋቸው ነጋዴዎችና የመንግስት ሠራተኞች ስለሚከፍሉት ግብር ምን አሏችሁ? መልሳችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

### ሁለተኛ ሳምንት፤ አንደኛ ቀን

**ማንበብ ፡ ትምህርት ሶስት ፡ አንብቦ መረዳት**

**ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

**ተግባር አንድ፡ ቀጥሎ የቀረበላችሁን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት ከመምህራችሁ ጋር በሚቀጥሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ** ፡፡

ሀ. በገበያ ውስጥ ካያችኋቸው የምግብ ማጣፈጫዎች መካከል ምን ምን ታስታውሳላችሁ?

ለ. በአካባቢያችሁ የተለመደ መድኃኒት ታውቃላችሁ?



ተግባር ሁለት፡- የግል ንባብ

የሕይወት ቅመም

በጥቁር አዝሙድና በሕመም ፈዋሽነቱ ዙሪያ የተሰሩ በርካታ ሳይንሳዊ ምርምሮች አሉ። የሚከተሉት በናሙናነት ቀርበዋል፡፡ በዚህ ሳይንሳዊ ምርምር ላይ እንደ መነሻ ሃሳብ የቀረበው ጥቁር አዝሙድ ለዘመናት እንደ ፍቱን መድሐኒትነት እውቅና እንዳለውና  በውስጡ የሚገኘው ሀያል ንጥረ ቅመም ካንሰር (ነቀርሳ) ፣ የልብ ህመም ፣ የስኳር ሕመም ፣አስም፣የኩላሊት በሽታዎችን ወዘተ. በመፈወስ ብቃት ከጥንትም ጀምሮ የሰው ልጆች ሲገለገሉበት ነበር፡፡ ይህም እውነታ በበርካታ ሳይንሳዊ ምርምሮች ተረጋግጦ በዘመናዊ ህክምና ውስጥ ተካቷል፡፡

ጥቁር አዝሙድ በተለይ ለፕሮስቴት ፣ ለጡት  ፣ ለደም ፣ለጉበት፣ ለኩላሊትና ለሳንባ ካንሰር እንደ አማራጭም ሆነ አንደ አጋዥ መድሐኒት መፍትሔ የማምጣት ብቃት እንዳለው ይገለጻል፡፡

ጥንታዊ የሕክምና ባለሙያዎች የጥቁር አዝሙድን የጸረ ካንሰር ብቃት ተፈጥሮ በለገሳቸው ጥበብ ጠንቅቀው ያውቁ የነበረ ቢሆንም በሳይንሳዊ ምርምር ተደርሶበት ጸረ ካንሰር ጠቀሜታው በዘመናዊ መልክ ይፋ መደረግ የጀመረው ግን ካለፉት ሁለትና ሶስት አስርት አመታት ወዲህ ነው፡፡

**እስካሁን ያነበባችሁት ዋና ሃሳብ ምን ላይ ያተኮረ ነው?**

**መልሳችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡**

ባለንበት የስልጣኔ ዘመን ካንሰር የሰውን ልጅ ከሚፈታተኑት በሽታዎች አንዱ ብቻ ሳይሆን ዋንኛውም ነው ሊባል ይችላል፡፡ ከሌሎች በሽታዎች ለምሳሌ ከደም ግፊት፣ ከስኳር ፣ከልብ ሕመም ወዘተ. አንጻር ካንሰር ክፉ ደዌ ነው፡፡ ይህ የተባለበት ምክንያት እስካሁን ድረስ በሳይንሳዊ እርምጃ የተገኙት ዘመናዊ መድሐኒቶች ዝርዝር በቁጥርም ሆነ በውጤታማነት የልብ አድርስ ናቸው ብሎ ለመናገር የሚያስችል ምእራፍ ላይ ሊያደርሰን ባለመቻሉ ነው፡፡

ካንሰርን የመከላከልም ሆነ አክሞ የማዳን ጥበብ ከፍተኛው የስኬት ጫፍ ላይ ባለመድረሱ ምክንያት አሁንም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በመራር ሕመም እየተሰቃዩ ይገኛሉ፡፡ ሳይንቲስቶችም ወደፊትም ወደ ኋላም እያማተሩ ከጥንቱም ሆነ ከዘመናዊው እውቀት መሀል መፍትሔ ለማግኘት በመትጋት ላይ ይገኛሉ፡፡

በሽታን መከላከል ከመፈወስ ወይም ከማዳን ያልተናነሰ ታላቅ ሥነ ሕይወታዊ ፋይዳ አለው፡፡ ጥቁር አዝሙድ ጸረ ካንሰር ኃይል ነው ብለን ስንገልጽ ከፊት ለፊት የመከላከል ብቃቱን በማስቀደም ነው፡፡ ልክ ጨውን ስኳርን በሁለገብነት እንደ ማጣፈጫ እንደምንጠቀመው ሁሉ የጥቁር አዝሙድን ዱቄት በማንኛውም ምግባችንና መጠጣችን ውስጥ በጥቂቱ ነስነስ ወይም በተን አድርገን በመጠቀም ራሳችንን ከካንስር ተጋላጭነት መታደግ እንችላለን፡፡ ይህንን የጥንቱ አዋቂዎችም ሆነ የዘመኑ ሳይንቲስቶች በእኩል ድምጽ ይስማሙበታል፡፡

ምንጭ ጥቁር አዝሙድ የህይወት ቅመም
በዶ/ር ኬኬ ከገጽ 49-50 ማንኩሳ አሳታሚ 2006 ዓ.ም

ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

ተግባር ሶስት፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. የሕይወት ቅመም የተባለው ምንድን ነው?
2. ካንሰር የሚለው ቃል በምንባቡ ውስጥ በምን ቃል ተወክሏል?
3. ጥቁር አዝሙድ ፍቱን መድሐኒት የሆነው ለምን ለምን በሽታ ነው?
4. ሳይንስና የባህል ሕክምና በጥቁር አዝሙድ ጉዳይ ላይ የሚስማሙ ይመስላችኋል?
5. የባህል ሕክምና መድሐኒቶች ከምን የሚገኙ ናቸው?

ቀጥሎ ለተመከቱት ቃላት አውዳዊ ፍች ፈልጉ

| | | |
|---|---|---|
| 1. ፍቱን<br>2. ንጥረ ቅመም<br>3. በለገሳቸው<br>4. ይፋ | 5.<br>6.<br>7. | ደዌ<br>እያማተሩ<br>ፋይዳ |

ሁለተኛ ሣምንት፡ሁለተኛ ቀን


## ትምህርት አራት፡ መጻፍ /አረፍተ ነገር መመስረትና አንቀጽ ማዋቀር/

በዚህ ትምህርት አራት አንቀጾችን የያዘ አንድ አጭር ጽሑፍ ቀርቧል፡፡ ጽሑፉ የስራ ክፍፍል የሚል ርእስን መነሻ አድርገው የተስፋፉ አረፍተ ነገሮችን ይዟል፡፡ አንቀጽ ለመጻፍ የአረፍተ ነገር አወቃቀርን ሂደት በደንብ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ በአንድ አንቀጽ ውስጥ ዋና ሐሳብ የያዘ አንድ አረፍተ ነገርና እሱን የሚያብራሩ ዝርዝር አረፍተ ነገሮች ያስፈልጋሉ፡፡ ለመጻፍ እንዲረዱን የሚከተሉትን ሂደቶች እንመልከት፡፡

ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ የአንቀጽ አደረጃጀትን መፈተሽ ይቻላል፡፡

1. ርእሱ ስለምን ይገልጻል?
2. የመጀመሪያው አንቀጽ ውስጥ ያሉ አረፍተ ነገሮች ስለምን ይገልጻሉ?
3. አንዱ አረፍተ ነገር ከሌላው ጋር ትስስር አለው?
4. በአረፍተ ነገሮቹ መካከል የሃሳብ ዝምድና አለ?

ከመጀመሪያው አንቀጽ ውስጥ የሚገኙ አረፍተ ነገሮችን አደረጃጀት የሚያሳይ የቢጋር ሰንጠረዥ ምሳሌ




ከዚህ ቀደም ብሎ የተመለከተው የቢጋር ሰንጠረዥ የስራ ክፍፍል በሚል ርእስ አንቀጽ ለመመስረት የሚረዱ አረፍተ ነገሮች ስበስብ የያዘ ነው፡፡ እነዚህን አረፍተ ነገሮች በማዋቀር አንቀጹ ተመስርቷል፡፡

**ተግባር አንድ**

የሁለተኛውን አንቀጽ ዋና ሃሳብና ዝርዝር አርፍተ ነገሮችን በምሳሌው መሰረት ለይታችሁ ጻፉ፡፡

**የስራ ክፍፍል**

መንደራችን ወስጥ ተጋግዞ የመስራት ባህል አለ፡፡ ተጋግዞ የመስራት ባህልን ማኅበረሰቡ ተቀብሎ ሲተገብረው ኖሯል ፡፡ የአካባቢው ነዋሪ ስራን ተከፋፍሎ የመስ ራት ልምድ አለው፡፡ ነዋሪው የጠንካራ አስተሳሰብ ባለቤት ማህበረሰቦች ምሳሌ ነው፡፡

በአካበቢያችን በእድሜ የገፉ አቅመ ደካማዎችን የመደገፍና የመርዳት ማሕበራዊ ግዴታ አለ፡፡ ይህን ግዴታ ተቀብለው የሚኖሩ ወንዶችና ሴት ወጣቶች አሉ፡፡  ጊፋቴ፣ዳሮታ፣ኩሊቴ፣ፋዮና አህመድ በአርአያነት የሚጠቀሱ

ናቸው፡፡ ወጣቶቹ ባህል፣ ቋንቋና ሃይማኖት ሳያግዳቸው ያለ ልዩነት አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

አቶ ጠንክር የ65 ዓመት አዛውንት ናቸው፡፡ እኚህ አዛውንት አብሯቸው የሚኖር ልጅ የላቸውም ፡፡ ባለቤታቸውና ራሳቸው ብቻቸውን ይኖራሉ ፡፡ እርዳታ እንደሚያስልጋቸው የተረዱት የመንደራችን ወጣቶች የስራ ክፍፍል አድርገዋል ፡፡ ወጣቶቹ ተገቢውን እገዛ በመስጠት የድርሻቸውን በደስታ ያከናውናሉ፡፡

ጊፋቴ የታለበውን ወተት ትንጣለች፡፡ ዳሮታ እንጨት በመፍለጥ ያግዛል፡፡ ኩሊቴ ደግሞ ውሃ በመቀዳት ትሳተፋለች፡፡ ፋዮ ጎመን ቀቅላ ምሳ ታዘጋጅላቸዋለች፡፡ አህመድ ከብት በማገድ ያገለግላቸዋል፡፡

**ተግባር ሁለት**

<u>የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ቀድሞ ከቀረበው ጽሑፍ የተወሰዱ ናቸው፡፡ ቀጥሎ የቀረቡትን ምሳሌዎች መሠረት በማድረግ የአረፍተ ነገሩን ባለቤት፣ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ ለይታችሁ ጻፉ፡፡</u>

- ጊፋቴ ወተት ናጠች ፡፡
  - ባለቤት( አድራጊ) ጊፋቴ
  - ተሳቢ (ድርጊት ተቀባይ) ወተት
  - ማሰሪያ አንቀጽ (ድርጊት) ናጠች
- ዳሮታ እንጨት ፈለጠ ፡፡
  - ባለቤት ዳሮታ
  - ተሳቢ እንጨት
  - ማሰሪያ አንቀጽ ፈለጠ

1. አህመድ ከብት ያግዳል፡፡
   ባለቤት__________________
   ተሳቢ__________________
   ማሰሪያ አንቀጽ ____________________
2. ኩሊቴ ውሃ ቀዳች፡፡
   ባለቤት__________________
   ተሳቢ__________________
   ማሰሪያ አንቀጽ ____________________
3. ፋዮ ጎመን ቀቀለች፡፡

ባለቤት___________________

ተሳቢ____________________

ማሰሪያ አንቀጽ _______________

**ሁለተኛ ሳምንት ፡ ሶስተኛ ቀን**

**ትምህርት አምስት ፡አንቀጽ መጻፍ**

**ማስታወሻ**

**<u>የአንቀጽ ሐይለ ቃልና መዘርዝራዊ አረፍተ ነገሮች</u>**

አንቀጽ አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ አረፍተ ነገሮች ቅንጅት የሚፈጠር አነስተኛ የድርሠት አካል ነው፡፡ አንቀጽ የተለያዩ አረፍተ ነገሮች ቅንጅት ይሁን እንጂ በውስጡ አንድ ሀሣብን ብቻ የያዘ የድርሠት ክፍል ነው፡፡ የአንቀጽ መገንቢያ አካላት ኃይለቃልና መዘርዝራዊ አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡

ሀይለቃል የሚባለው የተለያዩ አረፍተ ነገሮች ተሰብስበው በመተጋገዝና በመቀባበል የሚያስፋፉትንና የሚተነትኑትን ጉዳይ /ሐተታ/ አጠቃሎ በመምራት የአንቀፁን አጠቃላይ መሠረታዊ አቋም የሚያስቃኝ አንድ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ሀይለቃል በአንድ አንቀፅ ውስጥ የሚገኝ አንድ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ሀይለቃል የአንድ አንቀፅ “መሪ ቃል” ነው፡፡ ሀይለ ቃሉ በአንቀጽ ውስጥ ለሚፈጠረው ተግባቦት መሠረት ይጥልልናል፡፡

መዘርዝራዊ አረፍተ ነገሮች አታች አረፍተ ነገሮች ማለት ናቸው፡፡ መዘርዝራዊ አረፍተ ነገሮች የት? ማን? መቼ? ለምን? እንዴት፣ ወዴት፣ በምንና የመሳሰሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚያስችሉና ሐሳብን በማፍታታት የሚያሳውቁ ዝርዝር አረፍተ ነገሮች ናቸው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

**<u>በማስታወሻው ላይ የተመለከታችሁትን ሃሰብ መነሻ በማድረግ</u>**

- አንድ ርእስ አስቡ፡፡
- አንድ ዋና ሃሳብ የያዘ አረፍተ ነገር መስርቱ
- ዋናውን ሀሳብ የሚያብራሩ ተጨማሪ አረፍተ ነገሮች ጨምራችሁ ጻፉ፡፡

**ሶስተኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን**

**ተግባር አንድ፡**<u>ከዚህ በታች ያለውን ገጠመኝ ካነበባችሁ በኋላ በምሳሌው መሠረት ገጠመኛችሁን በአንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡</u>

**የእኔና የቤተሰቤ ገጠመኝ**

እኔ ተማሪ ታሪኩ ገመዴ እባላለሁ፡፡ የምኖረው በአንዲት የገጠር መንደር ነው፡፡ የአርሶ አደር ቤተሰብ ልጅ ነኝ፡፡ አባቴ፣እናቴ፣እኔና እህቴ በአንድ ክፍል ቤት ውስጥ እንኖራለን፡፡ አልፎ አልፎ ውሻችን ቤት ውስጥ ያድራል፡፡ ድመታችን ግን ሁልጊዜም የምታድረው ከቤት ውስጥ ነው፡፡ አንድ ቀን ሌሊት ድመታችን አይጥ ስታሳደድ አይጡ ወደ ውሻው ሲሸሽ ድመትና ውሻው በድንገት ተጋጩ፡፡ ሁለቱ ሲጣሉ፣ ከእንቅልፋችን ቀሰቀሱን ፡፡

**ተግባር ሁለት፡-** <u>የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ፡፡</u>

1. ባለ ታሪኩ ማን ይባላል?
2. ባለታሪኩ የሚኖረው የት ነው?
3. የባለታሪኩ ቤተሰቦች እነማን ናቸው?
4. ባለታሪኩ የገጠመው ችግር ምንድን ነው?
5. ባለታሪኩ መናገር የፈለገው ዋና ሃሳብ ምንድን ነው?
6. የተጣሉት እነማን ናቸው?

<u>አስቀድሞ የቀረበላችሁን አንቀጽ በማንበብ እናንተም የግል ገጠመኞቻችሁን የሚገልጽ አንድ አንቀጽ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ጻፉ፡፡</u>

**ሶስተኛ ሳምንት ፤ ሁለተኛ ቀን**

- በየቡድናችሁ ለሚገኙ ጓደኞቻችሁ ገጠመኞቻችሁን በየተራ አንብቡላቸው፡፡

## ሶስተኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን

- ተማሪዎች የጻፉችሁትን አንቀጽ በክፍሉ ፊት ቆማችሁ ለማንበብ ተዘጋጁ፡፡

## የምንባቡ ማበልጸጊያ ጥያቄዎች

1. የአረፍተ ነገር ክፍሎች ምን ምን ናቸው?
2. የአንድ አንቀጽ መሰረታዊ ክፍሎችን በመለየት በጽሑፍ ማብራሪያ ስጡ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## የህይወት መመሪያ

የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ

- ጠንክሮ መስራት የሚለውን ምንባብ አዳምጣችሁ አስተያየት ትሰጣላችሁ፡፡
- በመማሪያ መጽሀፋችሁ የቀረበውን የሚና ጨዋታ መሰረት በማድረግ ምልልስ ታደርጋላችሁ፡፡
- መመሪያዎችን አንብባችሁ በጽሁፍ  ትገልፃላችሁ፡፡
- የእለት ውሎ ዘገባ ትጽፋላችሁ፡፡
- የቃላትን ተመሳሳይ ፍች ታዛምዳላችሁ፡፡
- የቃላትን ተቃራኒ ፍች ትጽፋላችሁ፡፡

**አንደኛ ሳምንት ፣ አንደኛ ቀን**

**ትምህርት አንድ ፡- ማዳመጥ**

**የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄ**

**ተግባር አንድ**

<u>ቀጥሎ ለቀረበው ጥያቄ በቃል ምላሽ ስጡ፡፡</u>

ጠንካራ ሰራተኛ የሚባለው እንዴት ያለ ሰው ነው?

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ምንባብ በጥንቃቄ አዳምጡ፡፤

**ተግባር ሁለት፡ የማዳመጥ ጊዜ**

- ባዳመጣችሁት ጽሁፍ ውስጥ እስካሁን ምን ምን ነጥቦች ተነስተዋል?

**ተግባር ሶስት፡**

**ድህረ ማዳመጥ**

መምህራችሁ ሲያነቡ ያዳመጣችሁትን ጽሁፍ መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ስጡ፡፡

1. ቀኑን ሙሉ ያለ እረፍት መስራት ስኬታማ ያደርጋል?
2. ሰዎች በተሰማሩበት የስራ መስክ ውጤታማ ለመሆን ምን ማድረግ አለባቸው?
3. ለፍታችሁ አጥንታችሁ የልፋታችሁን ያህል ውጤት ካላገኛችሁ ምን ማድረግ አለብን ብላችሁ ታስባላችሁ?

**አንደኛ ሳምንት ፣ሁለተኛ ቀን**

**ትምህርት ሁለት - መናገር**

**ሚና ጨዋታ**

ከዚህ በታች የቀረበውን የሚና ጨዋታ አንብቡ፡፡

ሀኪምና ታካሚ

ዶክተር- "ጤና ይስጥልኝ፡፡"

ታካሚ - "አብሮ ይስጥልኝ፡፡"

ዶክተር - "ምንድን ነው የሚሰማህ ?"

ታካሚ - "ወገቤ ላይ ህመም ይሰማኛል።"

ዶክተር - "ሌላስ?"

ታካሚ - "ጎኔ ላይ ወጋ ያደርገኛል።"

ዶክትር - "ሽንትህ ቶሎ ቶሎ ይመጣል?"

ታካሚ - "አዎ ዶክተር" /እያቃሰተ/

ዶክተር - "ከዚህ በፊት ኩላሊትህን አሞህ ህክምና አግኝተህ ታውቃለህ?"

ታካሚ - "አይ! አላውቅም።"

ዶክተር - /በምርመራ ማዘዣ ወረቀት ላይ ጽፎ እየሰጠ/ "ይቺን ወረቀት ይዘህ

ላብራቶሪ ሂድና ናሙና ስጥ።"

ታካሚ - "እሺ ዶክተር። አመሰግናለሁ።" /በማለት ወረቀቱን ተቀብሎ

ይወጣል/።

ዶክተር- /ከአፍታ ቆይታ በኂላ/ "ተረኛ ይግባ!"

ታካሚ- /ተመልሶ ይገባል/

ደክተር- /የምርመራ ውጤት እየተመለከተ/ "የምርመራው ውጤት

የኩላሊት ‹‹ኢንፌክሽን›› ቁስለት ያሳያል። ስለዚህ የማዝልህን

መድሀኒት ትወስድና ደህና ትሆናለህ።"

ታካሚ - "እሺ ዶክተር፣ ሌላ ማድረግ ያለብኝ ጥንቃቄ አለ?"

ዶክተር- "በቀን እስከ ሁለት ሌትር ውሀ ጠጣ፣ በተለይም ጠዋት በባዶ ሆድህ

ውሀ የመጠጣት ልምድ ቢኖርህ ጥሩ ነው፣ ሌላው ደግሞ ጨውና

ቅባት የበዛበት ምግብ እንዳትመገብ ተጠንቀቅ፡፡"

ታካሚ- "እሽ ዶክተር አመሰግናለሁ፡፡" /በማለት ለመውጣት ይዘጋጃል/

አስቀድማችሁ ያነበባችሁትን የሚና ጨዋታ መሰረት በማድረግ መምህራችሁ በሚመድቧችሁ ቡድን ታካሚው ወደ ቤት ሲመለስ ቤተሰቦቹ የሚያቀርቡለትን ጥያቄና የሚያደርጉለትን እንክብካቤ በተመለከተ ታሪክ ፈጥራችሁ እናት፣አባት፣ እህት፣ ወንድም የመሆን ሚና ተጫወቱ፡፡

## አንደኛ ሳምንት ሶስተኛ ቀን

### ትምህርት ሶስት፡ አንብቦ መረዳት

### ተግባር አንድ ፡ ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

- ቀጥሎ የቀረበላችሁን አጭር ጽሁፍ ከማንበባችሁ በፊት ርዕሱ ስለምን ሊያስነብብ እንደሚችል ገምቱ፡፡

ተግባር ሁለት - የግል ንባብ

### የህይወት መመሪያ

መልካም ነገር እንዲሆንለት የማይፈልግ ሰው የለም፡፡ ሁሉም ሰው መወደድን፣መከበርን፣መደመጥንና አስፈላጊ በሚሆን ጊዜ መታገዝን ወዘተ. ይፈልጋል፡፡

አንዳንድ ሰዎች ለሌሎች ፍቅርን፣ትህትናን፣ አክብሮትን ፣ማሳየት እንዳለባቸው ልብ አይሉም፡፡ ወይም ችላ ይላሉ፡፡ ነገር ግን ሰዎች እንዲወዷቸውና እንዲያከብሯቸው ይፈልጋሉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ሰው ሲናገር ጣልቃ እየገቡ የራሳቸውን ሀሳብ ይናገራሉ፡፡ የሰው ንግግር ሲያቋርጡ ይቅርታ አይጠይቁም፣ የራሳቸውን ወሬ አውርተው ሲጨርሱ እንኳ ያቋረጡትን ሰው እንዲቀጥል አይጋብዙትም፡፡ በዚህ ሁኔታ ጫወታው የተቋረጠበት ሰው ያኛው ሲጨርስ

የራሱን ሃሳብ አውርቶ ለመቋጨት በማሰብ ላይ ይጠመድና ተናጋሪውን በሙሉ ልብ አያዳምጠውም፡፡ አንዳንድ ሰዎች ሌሎች እንዲያከብሯቸውና እንዲፈልጓቸው ይሻሉ፡፡ ነገር ግን እነሱ ለሰው ያላቸውን አክብሮትና ፍላጎት በተግባር አይገልፁም፡፡ ሁል ጊዜ ሰዎች እንዲያግዟቸውና እንዲተባበሯቸው ይፈልጋሉ፡፡ እነሱ ግን ያንን ሲያደርጉ አይስተዋሉም፡፡

**ተግባር ሁለት**

**የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች**

- ጽሁፉን ከማንበባችሁ በፊት ርዕሱን አይታችሁ ከገመታችሁት ጋር ተመሳሳይ ሆነ ?ወይስ አልሆነም?
- በጽሁፉ ምን ምን ነጥቦች ተነስተዋል?

የዘሩትን የማጨድ ህግ እዚህም ላይ በደንብ ይሰራልና ሰዎች ከወደድካቸው ይወዱሃል ከጠላሀቸው ግን ይጠሉሃል ስለዚህ እንዲወዱህ ውደዳቸው፤ ካከበርካቸው ያከብሩሀል ከናቅካቸው ግን ይንቁሀል ስለዚህ እንዲያከብሩህ አክብራቸው፤ካዳመጥካቸው ያዳምጡሀል ችላ ካልካቸው ግን ችላ ይሉሃል ስለዚህ እንዲያዳምጡህ አዳምጣቸው፤ ከቀረብካቸው ይቀርቡሀል ከራቅካቸው ግን ይርቁሀ ል ስለዚህ እንዲቀርቡህ ቅረባቸው፤ ከደገፍካቸው ይደግፉሀል ከተቃወምካቸው ይቃወሙሀል ስለዚህ እንዲደግፉህ ደግፋቸው፡፡ እንዲያደርጉልህ የምትሻውን መልካም ነገር አንተም አድርግላቸው፡፡

**ተግባር ሦስት**

**ድህረ ንባብ ጥያቄዎች**

<u>በጽሁፉ ውስጥ የቀረቡትን የህይወት መመሪያዎች እናንተ እንደተናገራችኋቸው አድርጋችሁ ጻፏቸው፡፡</u>

ምሳሌ፡-

ሀ/ ሰዎች እንዲያከብሩኝ እኔም አከብራቸዋለሁ ፡፡

ሰ/-------------------------------

ሐ/-----------------------------

መ/------------------------------

ሠ/-------------------------------

## ሁለተኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን

## ትምህርት አራት፡፡ መጻፍ

1. ከላይ በቀረበላችሁ ጽሁፍ ውስጥ ያሉት መመሪያዎችን ተግባራዊ ማድረግ ከባድ ነው? ለምን? በቡድን ተወያይታችሁ ምላሻችሁን ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

## ሁለተኛ ሳምንት፡ ሁለተኛ ቀን

## ትምህርት አምስት፡ ለቃላት ተቃራኒ ፍች መጻፍ

…የዘሩትን የማጨድ ህግ እዚህም ላይ በደንብ ይሰራልና ሰዎች ከወደድካቸው *ይወዱሃል* ከጠላሀቸው ግን ይጠሉሃል ስለዚህ እንዲወዱህ ውደዳቸው፤ ካከበርካቸው *ያከብሩሀል* ከናቅካቸው ግን ይንቁሀል ስለዚህ እንዲያከብሩህ አክብራቸው፤ ካዳመጥካቸው *ያዳምጡሀል* ችላ ካልካቸው ግን ችላ ይሉሃል ስለዚህ እንዲያዳምጡህ አዳምጣቸው፤ ከቀረብካቸው *ይቀርቡሀል* ከራቅካቸው ግን ይርቁሀል ስለዚህ እንዲቀርቡህ ቅረባቸው፤ ከደገፍካቸው *ይደግፉሀል* ከተቃወምካቸው ግን ይቃወሙሃል ስለዚህ እንዲደግፉህ ደግፉቸው፡፡ እንዲያደርጉልህ የምትሻውን መልካም ነገር አንተም አድርግላቸው፡፡

**ቀደም ብሎ ከቀረበው ጽሁፍ ለተወሰዱት ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒያቸውን ከዚያው ጽሁፍ ውስጥ ፈልጉ፡፡**

ምሳሌ፡ መልካም - መጥፎ

1. ያከብሩሀል----------------------
2. ያዳምጡሀል---------------------
3. ይቀርቡሀል----------------------
4. ይወዱሃል----------------------
5. ይደግፉሃል---------------------

## ሁለተኛ ሳምንት ፡ ሶስተኛ ቀን

### ትምህርት ስድስት፡ ቃላትን ከተመሳሳይ ፍቾ ጋር ማዛመድ

<u>ቀጥሎ የቀረበውን ጽሁፍ አንብቡ</u>

<u>የዕለት ውሎዬ</u>

ቀን 12/2/2014 ዓ.ም

ዛሬ በማለዳ ተነስቼ ፊቴን እየታጠብኩ በራችን ሲንኳኳ ሰማሁ፡፡ እኔ በሩን ለመክፈት እየሄድኩ ሳለ ዉሻችን ያለወትሮው ሮጦ ቀደመኝ፡፡ ምንም እንኳን በሩ ዝግ ቢሆንም በበሩ አጠገብ ባለው ቀዳዳ ሾልኮ ወጣ፡፡ ውሻችን ቸኩሎ ሰው የመንከስ ባህርይ ባይኖረውም ውጪ ቆማ ስታንኳኳ የነበረችው እንግዳ ሴት ደንግጣ ስትሮጥ ወደቀች፡፡ እኔም እንግዳዋ ነፍሰጡር በመሆኑዋ በጣም ደንግጬ ስጮህ ወንድሜ ሮጦ መጣና እንግዳዋን ከወደቀችበት ተጋግዘን በማንሳት ወደ ቤት አስገብተናት እንድትረጋጋ አደረግናት፡፡ ከዚያም ታክሲ ጠርተን ወደ ቤቷ ሸኘናት፡፡ ዉሻችንን ሁል ግዜ በማለዳ ማሰር እንዳለብንና የሚሾልክበትን ቀዳዳም መድፈን እንደሚገባን ተነጋግረን አሰርነው፡፡ በመጨረሻም ወደ ትምህርት ቤት የመሄጃ ሰአቴ መድረሱን ሳይ ቁርሴን በልቼ ደብተሮቼን ያዝኩና ከቤት ወጣሁ፡፡ የእረፍት ሰዓት ደርሶ ወደ ውጪ በወጣንበት የእንግዳዋ ነገር በጣም ስላሳሰበኝ ስልክ ደውዬ ጠየቅኳት፡፡ እሷም ክትትል ወደ ምታደርግበት ሀኪም ቤት ሄዳ ስትታይ በሆዷ በያዘችው ጽንስም

ሆነ በሷ ላይ ምንም ጉዳት እንዳልደረሰ ስትነግረኝ  በጣም ደስ አለኝ፡፡ "አምላክ ይመስገን!" የፈራሁት አልሆነም፡፡

ምንጭ- ከአዘጋጆቹ

የሚከተሉት ቃላት አስቀድሞ ካነበባችሁት ጽሁፍ የተወሰዱ ናቸው፡፡ በፍቺ ከሚመሳሰሏቸው ቃላት ጋር አዛምዷቸው፡፡

| <u>ሀ</u> | <u>ለ</u> |
|---|---|
| 1. ጽንስ | ሀ/ ጠዋት |
| 2. ያለወትሮው | ለ/ ጸባይ |
| 3. ባህርይ | ሐ/ እርግዝና |
| 4. ሁል ግዜ | መ/ ያለልማዱ |
| 5. ማለዳ | ሠ/ እርጉዝ |
| 6. ነፍሰጡር | ረ/ ዘወትር |
| | ሰ/ ያለጊዜው |

**ሶስተኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን**

**ትምህርት ሰባት፡ ዘገባ መጻፍ**

**ማብራሪያ**

ዘገባ አንድን ክንውን ወይም ሂደት በሚመለከት ለሌላ ወገን ክንውኑን ወይም ሂደቱን አስመልክተን የምንዘግብበት የጽሁፍ ዓይነት ነው፡፡ ዘገባ በባህሪው ትክክለኛነት፣ተጨባጭነት ፣ ወቅታዊነት ፣ግልጽነትና ተነባቢነት ያለው ጽሁፍ ነው፡፡

<u>ከላይ የቀረበውን ማብራሪያና የዕለት ውሎዬ በሚል ርዕስ የቀረበውን ዘገባ በማንበብ እናንተም የትናንት ውሏችሁን በዘገባ መልክ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡</u>

**ሶስተኛ ሳምንት፡ ሁለተኛ ቀን**

## ትምህርት፡ትምህርት ስምንት

<u>ባለፈው ክፍለ ጊዜ የጻፋችሁትን ዘገባ በየተራ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው</u>፡፡

ሶስተኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ዘጠኝ፡

*<u>መምህራችሁ በሚነግሯችሁ መሰረት በቡድን በመቀመጥ ልምዳችሁን ተካፈሉ፡፡</u>*

## ምዕራፍ ሶስት

## ስርዓተ ጾታ

| |
|---|
| የሚጠበቁ ውጤቶች<br>ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ<br>• ስርአተ ጾታን የተመለከተ ምንባብ አዳምጣችሁ ለጥያቄዎች ምላሽ ትሰጣላችሁ::<br>• በችግር ፈቺ ክርክር ትሳተፋላችሁ፡፡<br>• ለችግሮች የመፍትሔ ሐሳብ ታቀርባላችሁ፡፡<br>• የምንባቡን ዋና ሀሳብ ትገልፃላችሁ፡፡<br>• ለመስሪያ ቤት ማመልከቻ ትጽፋላችሁ፡፡<br>• የቃላትን መዝገብ ቃላዊ ፍች ትለያላችሁ፡፡<br>• ምዕላዶችን ነጥላችሁና አጣምራችሁ ትጽፋላችሁ፡፡<br>• ስርአተ ነጥቦችን በተገቢው ቦታ ትጠቀማላችሁ፡፡ |

አንደኛ ሳምንት ፤አንደኛ ቀን

ትምህርት አንድ፡- ማዳመጥ

ተግባር አንድ

<u>መምህራችሁ ስለ ስርዓተ ጾታ የተፃፈ ምንባብ ሲያነቡላችሁ በጥሞና አዳምጡ፡፡</u>

የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

<u>ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች የቀደመ ዕውቀታችሁን በመጠቀም ትክክል የሚመስላችሁን መልስ በቃል ስጡ፡፡</u>

1. ሥርዓተ ጾታ ምንድን ነው?

2. በፆታና በሥርአተ ፆታ መካከል ያለውን ልዩነት ግለጹ፡፡

ተግባር ሁለት

የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

እያዳመጣችሁት ያለውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. የስርዓተ ፆታ ገጽታ ይለወጣል ሲባል ምን ማለት ነው?
2. ስናራምደው የቆየነው የስርዓተ ጾታ ግንኙነት ለወንድ ያደላ መሆኑን አመላካች ነገሮችን ጥቀሱ፡፡

ተግባር ሶስት

የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. ጾታና ስርዓተ ፆታን በማነፃፀር በቡድን ተወያዩና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
2. ስርዓተ ፆታን የማካተትን ግብ በምንባቡ መሰረት ግለፁ፡፡

አንደኛ ሳምንት ፡ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ሁለት ፡መናገር

በአለፈው ክፍለ ትምህርት ስለ ስርአተ ፆታ ያገኛችሁትን ግንዛቤ በማስታወስና መምህራችሁ የሚነግሯችሁን አጭር ማብራሪያ በማዳመጥ ከስርዓተ ፆታ

አንፃር የአካባቢያችሁ ማህበረሰብ ያለውን  የተዛባ አመለካከትና ሚና በቡድን ተወያዩበት፡፡

**አንደኛ ሳምንት ፤ ሦስተኛ ቀን**

**ትምህርት ሦስት ፡- የንግግር ክህሎትን ማዳበር**

በአለፈው ክፍለ ትምህርት በምትኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ስለ ስርዓተ ፆታ ያለውን የተዛባ አመለካከትና ሚና በተመለከተ ያደረጋችሁትን ውይይት አጭር ማስታወሻ በመያዝ በንግግር ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

**ሁለተኛ ሳምንት ፤ አንደኛ ቀን**

**ትምህርት አራት፦ ችግር ፈች ክርክር**

ተማሪዎች ከዚህ በታች የቀረበውን አጭር ታሪክ መነሻ በማድረግ እናንተም በርዕስ ጉዳዩ ላይ በአነስተኛ ቡድን በመደራጀት ተከራከሩ፡፡

## ኤርጎጎና ላጲሶ

አቶ ኤርጎጎና አቶ ላጲሶ በሀዲያ ዞን ውስጥ በአንድ የገጠር መንደር የሚኖሩ አርሶ አደሮች ናቸው። ከእርሻ ስራ ጎን ለጎን ከብት ማርባት ይወዳሉ።
ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የአየሩ ሙቀት መጨመር፣ የድርቅ መደጋገምና የበረሃ አንበጣ መራባት መሰል ክስተቶች በእርሻ ስራቸው ላይ ተጽዕኖ ፈጥሮባቸዋል። በሙቀት መጨመር ምክንያት ከቤት ውጪ የሚሰሩ ስራዎችን መስራት አለመቻል፤የአስምና ሌሎችም የብግነት (የአለርጂ) በሽታዎች መብዛት ፤የምግብ እህል መወደድና የንፁህ መጠጥ ውሃ እጥረት አሳስቧቸዋል ።
አቶ ኤርጎጎ እነዚህ ክስተቶች በሰው ልጆች ኃጢያት ምክንያት የተከሰቱ የፈጣሪ ቁጣ ናቸው የሚል ሀሳብ ያለው ሲሆን፤ አቶ ላጲሶ ግን ይህ የፈጣሪ ቁጣ ሳይሆን ደን በመጨፍጨፉ፤ የደን መሬቶች ወደ እርሻ መሬትነት በመቀየራቸው፤ ከኢንዱስትሪና ከመኖሪያ ቤት በሚለቀቁ ጋዞች እና በመሰል የሰው ልጅ ድርጊቶች የተከሰተ የአየር ንብረት ለውጥ ውጤት ነው ብሎ ያምናል።
ከእለታት አንድ ቀን ሁለቱ ግለሰቦች ክስተቱ ''የእግዜር ቁጣ ነው፤ አይደለም''፣ ''የአየር ንብረት ለውጥ ውጤት ነው፤ አይደለም'' በሚል ሀሳብ ሲከራከሩ አመሹ።

ተማሪዎች እነዚህ ክስተቶች በምን ምክንያት እንደሚከሰቱ በቡድን በመሆን ተከራከሩባቸው። በአቶ ኤርጎጎ አሳብ የምትስማሙ እና በአቶ ላጲሶ ሀሳብ የምትስማሙ የራሳችሁን አሳማኝ ሀሳብ እያቀረባችሁ ተከራከሩ።

**ሁለተኛ ሳምንት ፡ ሁለተኛ ቀን**

**ትምህርት አምስት፦ በአየር ንብረት ለውጥ ላይ መነጋገር**

ባለፈው በትምህርት አራት ያደረጋችሁትን ክርክር በማስታወስ እና አጭር ማስታወሻ በመያዝ በየቡድናችሁ ስለመፍትሄው ተነጋገሩና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

**ሁለተኛ ሳምንት ፤ ሦስተኛ ቀን**

**ትምህርት ስድስት ፡- ዋና ሀሳብ ለማግኘት ማንበብ**

ቅድመ ማንበብ ጥያቄዎች

<u>ተማሪዎች ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት ፍቺ ተናገሩ</u>

| | |
|---|---|
| ሀ/ ሰገነት | ለ/ ቡራቡሬ |
| ሐ/ ቀልብ | መ/ ዝንባሌ |
| ሠ/ ወረት | |

**የሰው ልጆች አቅም**

የሰው ልጆች ነፃ ፈቃድ አላቸው፡፡ ነፃ ፈቃድ ግን ሙሉ ፈቃድ አይደለም፡፡ የሰው ልጆች ነፃ ፈቃድ በየጊዜው እያደገ የሚሄድና በዕድገቱ ውስጥም የዕውቀትና የሥነ- ልቦና ኃይል እያዳበረ የሚሄድ ነው፡፡ የሰው ልጆች ጉዞም ነፃ ፈቃዳቸውን እያጠናከሩ ከአካባቢና ከተፈጥሮ ባሪያነታቸው ነፃ እየወጡ የሚመጡበት ሂደት ነው፡፡ ስለዚህ የሰው ልጅ ነፃ ፈቃድ ቀደም ብለው በሰሩት ሥራ ላይ የሚመሰረት ነው፡፡ ይህም ማለት ትናንት የሰሯቸው ስራዎች ለቀጣይ ሥራቸው መነሻ <u>ወረት</u> ይሆናቸዋል ማለት ነው፡፡

የሰው ልጅ በብዙ ነገሮች እየተራቀቀ ከመጣበትና አሁን ከደረሰበት የሥልጣኔ <u>ሠገነት</u> ላይ ቢገኝም ቅሉ የሠው ልጆች ፍላጎት አሁንም በአግባቡ በተሟላ መልኩ እየተመለሰ አይደለም፡፡ አሁንም የሰው ልጆች በረሃብ ይረግፋሉ፡፡ አሁንም በመድሃኒትና በህክምና እጦት ይማቅቃሉ፡፡አሁንም እርስ በእርሳቸው የሚገዳደሉና ኑሮአቸው ከተዘዋዋሪ አደን ያልተላቀቀ ነው፡፡ የሰው ልጆች

ሥልጣኔ ስለምን <u>ቡራቡሬ</u> ሆነ? የአንዱ ፋላጎት ሲሟላ የሌላው ፍላጎት ስለምን ጦሙን ያድራል?

የሰው ልጆች የስልጣኔ ደረጃ ልዩነት የሰው ልጆችን ተፈጥሮ በተመለከተ ሁለት የተለያዩ ሀሳቦችን አስነስቷል፡፡ ይኸውም አንደኛ የሰውን ልጅ ስግብግብ ፣ራስ ወዳድ፣ ተፎካካሪ እና ጠበኛ ፍጥረት ነው፤ የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሰው ልጅ በመሰረቱ መልካም፣ ተባባሪ እና ለሌሎች አሳቢ ፍጥረት ነው፤ የሚለው ነው፡፡ በእነዚህ ሃሳቦች ምክንያት የክርክር አጀንዳ ተፈጥሯል፡፡

የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የሰው ልጆች ነፃ ፈቃድ ቀደም ሲል በሰሩት ሥራ ላይ የሚመሰረት ነው ሲል ምን ለማለት ነው ?
2. የሰው ልጆችን ተፈጥሮ በተመለከተ የተነሱት አከራካሪ ሀሳቦች መነሻ ምክንያት ምንድነው?

ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ሊቃውንቱ ጦርነቱ በፈጠረባቸው ተጽዕኖና ሽብር ምክንያት "የሰው ልጅ ጨካኝና አደገኛ ፍጥረት ነው"የሚል ሀሳብ አምጥተዋል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ በዓለም ላይ የኮምዩኒዝም **<u>ርዕዮተዓለም</u>** እየሰፈነ ሲመጣ የሊቃውንቱ **<u>ቀልብ</u>** በሰው ልጅ የትብብርና የመልካምነት ተፈጥሮ ላይ እያተኮረ መጣ፡፡

የሰው ልጅ የፍቅርም ሆነ የትብብር ፣የጠበኝነትም ሆነ የሰላማዊነት **<u>ዝንባሌው</u>** በእጁ ላይ ነው፡፡ የሚፈልገውን ባህሪ የመገንባትና የማጠናከር አቅም አለው፡፡ ወጣ ገባ ብሎ የበሰለው የሰው ልጅ ስልጣኔ የእያንዳንዱን ሰው ፍላጎት በማሟላት ሙሉ በሙሉ የበሰለ እውነተኛ ስልጣኔ እንዲሆን ይህን የሰው ልጅ አቅም መገንዘብ የግድ ይላል፡፡

ምንጭ ፡- አብይ አህመድ (ዶ/ር)፡፡ 2012 ዓ/ም፤

መደመር፤ ገጽ 8–12: ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡

የድህረ ንባብ /አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

1. የሰው ልጆች ነፃ ፈቃድ መጠናከር ከተፈጥሮ ባርነት ነፃ ያወጣቸዋል፡፡
2. የስልጣኔ ቡራቡሬ መሆን አንዱ የእድገት ምልክት ነው፡፡
3. የጦርነት መከሰት ለሰው ልጅ ጨካኝነት አንዱ መንስኤ ሆኖ ቀርቧል፡፡
4. ኮሚዩኒዝም ትብብርንና መልካምነትን የሚያራምድ ርዕዮተ አለም ነው፡፡
5. የሰው ልጅ የራሱን ባህሪይ እንደፈለገው መገንባት ይችላል፡፡

**ሶስተኛ ሳምንት ፡- አንደኛ ቀን**

**ትምህርት ሰባት ፡- የምንባቡን ዋና ሀሳብ መናገር**

በትምህርት ስድስት ያነበባችሁትን የሰው ልጆቸ አቅም የሚለውን ምንባብ ዋና ሀሳብ በቡድን ማስታወሻ በመያዝ ተወያዩበትና በተወካዮቻችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

**ሶስተኛ ሳምንት ፤ሁለተኛ ቀን**

**ትምህርት ስምንት፡ ማመልከቻ መጻፍ**

ተግባር፦ ከዚህ በታች የቀረበውን ማመልከቻ መነሻ በማድረግ ማመልከቻ መፃፍ ተለማመዱ፡፡

ለደቡብ ኦሞ ዞን ትምህርት መምሪያ
ጂንካ
**ጉዳዩ ፡- የደረጃ ዕድገት እንዲሰራልኝ ስለመጠየቅ፤**

አመልካች እኔ መ/ር ሉቡቴ ሎንግሪች  የቡሜ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር ነኝ፡፡ በመምህርነት ከተቀጠርኩ 3 ዓመት የሆነኝ ሲሆን እስከ አሁን ድረስ በጀማሪ መምህርነት ላይ እገኛለሁ፡፡
ከእኔ ጋር የተቀጠሩ መምህራን በዘንድሮ አመት የመለስተኛ መምህርነት ደረጃ የተሰጣቸው ሲሆን ለእኔ ግን አልተሰራልኝም፡፡ ስለዚህ መምሪያው የቅጥር ጊዜዬን እንዲሁም የሥራ አፈፃፀሜን ከግምት አስገብቶ የደረጃ እድገት እንዲሰራልኝ ስል በታላቅ ትህትና እጠይቃለሁ፡፡

// ከሰላምታ ጋር//

ፊርማ

መምህር ሉቡቴ ሎንግሪች

**መልመጃ**፡- ከዚህ በላይ በቀረበው ማመልከቻ አስረጂነት እናንተም የጠፋባችሁን የልደት የወሳኝ ኩነት ማስረጃ በድጋሚ እንዲሰጣችሁ ለቀበሌያችሁ ማመልከቻ ፃፉ፡፡

ማመልከቻ ስትጽፉ ማስታውስ ያለባችሁ ፍሬ ነገሮች

1. ቀንና ማመልከቻው የተፃፈለት መስሪያ ቤት ስም
2. ማመልከቻው የሚፃፍበት ጉዳይ በአጭሩ መቅረብ አለበት
3. ዝርዝር ሀሳቡ በግልጽ መፃፍ አለበት
4. አጭር ማጠቃለያ ፣ሰላምታ ፣ፊርማና የአመልካቹ ስም መረሳት የለበትም

**ሶስተኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን**

**ትምህርት ዘጠኝ ፡- የጥሪ ደብዳቤ መፃፍ**

ተግባር ፡- ከዚህ በታች አንድ የሰርግ ጥሪ ደብዳቤ ቀርቦላችኋል፡፡

የሰርግ የጥሪ ደብዳቤውን አስተውላችሁ ተመልከቱና የምረቃ የጥሪ ደብዳቤ በመፃፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

**ሠርግ**

| |
|---|
| የማክበር ሰላምታችንን እያቀረብን የልጃችንን የአቶ ተሰማ ኮራ እና የወ/ሪት ሀና ቡቺቱ የጋብቻ ስነ ስርአት ሚያዝያ 22/ 2014 ዓ/ም ስለሚካሄድ በእለቱ ከምሽቱ 12:00 ሰዓት በመኖሪያ ቤታችን በሚደረገው የራት ግብዣ ላይ ከባቤትዎ ጋር በመገኘት የደስታችን ተካፍይ ይሆኑ ዘንድ በማክበር ጠርተንዎታል፡፡<br>አድራሻ፡- አማሮ ኬሌ ቴክኒክና ሙያ<br>ት/ሥ/ኮሌጅ ፊትለፊት<br>ጠሪዎች<br>ወ/ሮ ጫኮ ኤለማ<br>እና<br>አቶ ኮራ ቡቴ |

<u>መልመጃ</u>

እናንተም ከላይ በተሰጣችሁ የሠርግ ጥሪ ደብዳቤ አስረጂነት የምረቃ ጥሪ ድብዳቤ ጽፉችሁ ለጓደኞቻችሁ አንብቡ እንዲሁም ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

**አራተኛ ሳምንት ፤ አንደኛ ቀን**

**ትምህርት አስር፡ የቃላትን መዝገበ ቃላዊ ፍች መፃፍ**

ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ውስጥ የቀረቡት ቃላት ስርአተ ፆታ በሚል ርእስ ካደመጣችሁት ምንባብ የወጡ ናቸው፡፡ ለቃላቱ አንድ ወይም ከአንድ በላይ መዝገበ ቃላዊ ፍች ስጡ፡፡

| ቃላት | መዝገበ ቃላዊ ፍች |
|---|---|
| መዘነ | 1.ለካ፣ ሰፈረ ፣መጠነ<br>2.ከሌላው ይበልጥ ከበደ፣ ወደ አንድ ወገን አጋደለ<br>3.ገመተ ፣ ገመገመ |
| ፆታ | 1. |
| | 2. |
| ስርዓት | 1. |
| | 2. |
| ሚና | 1. |

| | |
|---|---|
| | 2. |
| እድል | 1. |
| | 2. |
| ልማት | 1. |
| | 2. |

**አራተኛ ሳምንት ፤ሁለተኛ ቀን**

**ትምህርት አስራ አንድ :<u>ምዕላዶችን መነጠልና ማጣመር</u>**

ተግባር አንድ ፡- ምዕላዶችን መነጠል

መመሪያ፦ ከዚህ በታች በሠንጠረዥ ውስጥ የቀረቡት ቃላት ኤርጎጎና ላጲሶ ከሚለው ምንባብ የተወሰዱ ናቸው፡፡ በቀረበው ምሳሌ መሰረት ምዕላዶችን በመነጠል ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ/ ቤቶች = ቤት - ኦች

ለ/ ልጅነት = ልጅ - ነት

| ቃላት | ነፃ ምዕላድ | ጥገኛ ምዕላድ |
|---|---|---|
| 1.ጋዞች | | |
| 2.መሬትነት | | |
| 3.ስራዎችን | | |
| 4.ሌሎችም | | |
| 5.የራሳችሁን | | |

**ተግባር ሁለት፡- ምዕላዶችን ማጣመር**

**መመሪያ**፦ ከዚህ በታች የሰው ልጆች አቅም ከሚለው ምንባብ የወጡ ቃላት በምዕላድ መልክ ቀርበዋል፡፡ በተሰጣችሁ ምሳሌ መሰረት ምዕላዶችን አጣምራችሁ ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ/ ክብር -ኧት = ክብረት

ለ/ ሰልፍ -ኧኛ = ሰልፈኛ

1. እውነት-ኧኛ = ……………………………………
2. ከ- አንድ -ኧኛ -ው =……………………………
3. የ- ሊቅ -ኣውንት -ኡ = ………………………..
4. ባሪያ -ነት -ኣቸው =……………………………
5. ፈቃድ -ኣቸው -ን =……………………………..
6. በ- ዕድገት -ኡ = ………………………………..
7. በ- ፈጠረ -ብ -ኣቸው = ………………………..

አራተኛ ሳምንት፤ ሶስተኛ ቀን

ትምህርት አስራ ሁለት፡- ስርአተ ነጥብ

ተግባር አንድ፡- በመቀጠል ስለስርአተ ነጥብ አይነቶችና ስለአገልግሎታቸው የቀረበውን ማስታወሻ በትኩረት አንብቡ፡፡

<u>ስርአተ ነጥቦችና አገልግሎታቸው</u>

<u>ዋና ዋና ስርአተ ነጥቦችና ቅርፃቸው</u>

| | |
|---|---|
| አንድ ነጥብ= (.) | የጥያቄ ምልክት = (?) |
| ሁለት ነጥብ= (፡) | ትእምርተ አንክሮ = (!) |
| አራት ነጥብ= (፡፡) | ትእምርተ ስላቅ = (¡) |
| ነጠላ ሰረዝ= (፣) | ትእምርተ ጥቅስ=(‹‹ ››) |
| ድርብ ሰረዝ= (፤) | ቅንፍ = ( ) |

<u>የነጠላ ሰረዝ፣ የድርብ ሰረዝ፣ የትእምርተ አንክሮና የትእምርተ ጥቅስ አገልግሎት</u>

<u>ነጠላ ሰረዝ</u> በአረፍተ ነገር ውስጥ በተከታታይ ተደርድረው የሚቀርቡትን ተመሳሳይ ሙያ ያላቸውን የቃላት ድርድር ለመለየት ያገለግላል፡፡

ምሳ. ከበደ ገበያ ሄዶ ኮት፣ ሱሪ፣ ሸሚዝና ጫማ ገዛ፡፡

<u>ድርብ ሰረዝ</u> በየራሳቸው ማሰሪያ አንቀፅ ሊወሰኑ የሚችሉና የሐሳብ ቁርኝት ያላቸው አረፍተ ነገሮችን አጣምሮ ለማቅረብ

ምሳ. ወባ በየጊዜው እየተነሳበት ያስቃየዋል፤ እስከአሁን ግን ለክፉ አልሰጠውም፡፡

<u>ትእምርተ አንክሮ</u> መገረምን፣መደነቅን፣ቁጣን፣ትእዛዝንና ግዴታን ያመለክታል፡፡

ምሳ. ጀመርክ እንግድህ !

<u>ትእምርተ ጥቅስ</u> ፀሐፊው የሌላን ሰው ንግግር ወይም ፅሑፍ በቀጥታ ቀድቶ በሚወስድበት ጊዜ ድርብ ትእምርተ ጥቅስ መጠቀም አለበት፡፡

ምሳ. ‹‹ በስልጣን ከፍ እያልክ ስትሄድ ለሕዝብ መልካም ሁን ›› (የሻው ተሰማ 1996፣139)

<u>ተግባር ፡- በመቀጠል የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች ተገቢውን ስርአተ ነጥብ በማስገባት አሟሉ፡፡</u>

1. ሆዴ ባዶ ነው___የመመገብ ፍላጎት ግን የለኝም፡፡
2. ___ተግባርና ሳይንስ፣ ከእነዚህ ሁለት ሀይላት የሚልቅ ነገር በምድር ላይ የለም፡፡___ማክሲም ጎርኪ፡፡
3. እማዬ___እባቡ መጣብኝ____፡፡
4. ወንድሜ ጃኬት___ሱሪ___ሸሚዝና ጫማ ገዛልኝ፡፡

## <u>የምዕራፉ ማበልፀጊያ ጥያቄዎች</u>

1. ስለ ስርአተ ፆታ የተፃፉ ልዩ ልዩ ጽሁፎችን በማንበብ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ መልክ ፃፉና አቅርቡ፡፡
2. በአካባቢያችሁ የሚገኙ አምስት ሰዎችን በማነጋገር ስለ ስርአተ ፆታ ያላቸውን ግንዛቤና ስለ ሴትና ስለ ወንድ ስራ (ሚና) ያላቸውን አመለካከት ሁለት ገጽ ዘገባ ጽፋችሁ አቅርቡ፡፡
3. የአየር ንብረት ለውጥ ምንድነው? የአየር ንብረት ለውጥ በምን በምን ምክንያት ሊከሰት ይችላል? የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለው ችግር ምንድነው? የመፍትሄ ሀሳቦቹስ? ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ሊሰጥ የሚችል ከሁለት ገጽ ያልበለጠ ድርስት ፃፉ፡፡

4. መታወቂያ እንዲሰጣችሁ ለቀበሌ አስተዳደር ማመልካቻ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

# ምዕራፍ አራት

## የአካቶ ትምህርት

| |
|---|
| የሚጠበቁ ውጤቶች<br>ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ<br>• ሳይንስና ቴክኖሎጂን ያካተተ መረጃ የያዘ ጽሑፍ አዳምጣችሁ አስተያየት ትሰጣላችሁ፡፡<br>• ስእሎችንና ሁነቶችን በመተንተን የተጓደሉ ሃሳቦችን ታሟላላችሁ፡፡<br>• በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት በማድረግ ትሳተፋላችሁ<br>• ያልተሟላ አረፍተ ነገር የያዙ አንቀጾችን ታሟላላችሁ፡፡<br>• የቃላትን መሰረት በመለየት ቃላትን ትመሰርታላችሁ፡፡<br>• ቃላትን በቃል ክፍሎቻቸው መሰረት ትመድባላችሁ፡፡ |

አንደኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን

ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ተግባር አንድ፡ ከዚህ በታች የቀረበውን ጥያቄ መልስ ገምቱ፡፡

የማህበራዊ ትስስር ገጽ (face book)፣ በይነመረብ(internet)፣ድረ ገጽ(website) ሲባል ሰምታችኋል? ምን ማለት ይመስላችኋል?

<u>የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት የሚል ምንባብ መምህራችሁ ያነቡላችኋል ፤እናንተ በጥንቃቄ አዳምጡ</u>

ተግባር ሁለት፡ የማዳመጥ ሂደት

አስካሁን ካዳመጣቸሁት ምን ተረዳችሁ አስኪ አጠር አድርጋችሁ ተናገሩ፡፡

ተግባር ሶስት፡

ንባቡን ካዳመጣችሁ በኋላ በሚከተሉት የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

1. ባዳመጣችሁት ንባብ ውስጥ ቴክኖለጂ ከምን ጋር ተያይዞ ቀርቧል?
2. ልማዳዊ አሰራር የተባለው ምንድነው?
3. የእጅ ስልካችንና ፕላዝማዎች ምን እንዲደረግባቸው የንባቡ ሃሳብ ይጠቁመናል?
4. ቴክኖሎጂን መጠቀም የሚሰጠው ጥቅም ምንድን ነው?
5. ቴክኖሎጂ በትምህርታችሁ ምን አይነት እገዛ እንዲያቀርብላችሁ ትፈልጋላችሁ?

አንደኛ ሳምንት፡ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ሁለት

ተግባር ፡ መናገር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንብባችሁ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩባቸው።

- ቴክኖሎጂን ለሀገር ልማት እንዴት መጠቀም ይቻላል?
- ሰዎች የእጅ ስልካቸውን ለምን ለምን አገልግሎት ሲያውሉ ታዝባችኋል?
- በይነመረብ/ኢንተርኔት/ ለምን የሚያገለግል ይመስላችኋል? ሀገርን ለመገንባት የሚውልበት መንገድ አለ ብላችሁ ታስባላችሁ?

አንደኛ ሳምንት፡ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ሶስት ፡ማንበብ (የግል ንባብ)

የአካቶ ትምህርት

ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ተግባር አንድ፡የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ ገምቱ።

ሀ. የአካል ጉዳት የሚደርሰው በምን ምክንያት ይመስላችኋል?

ለ. የአካል ጉዳት ከሌሎች ጋር አብሮ መማር ይከለክላል?

ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ በጸጥታ አንብቡ

## የአካቶ ትምህርት

እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በ1955 ዓ.ም እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር 1948 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ጥበቃ ለሁሉም ህጻናት ትምህርትን በእኩል ደረጃ የማግኘት መብት ድንጋጌን ሐገሮች የህጋቸው አካል አድርገው ተቀብለው እንዲተገብሩት የሚያስገድድ ድንጋጌን አጸደቀ፡፡

ይህ ድንጋጌ ህጻናት፣በአካል ጉዳተኝነታቸው፣ በጾታቸው፣ በማንነታቸው፣ በድህነታቸው ወዘተ. ምክንያት ከትምህርት ገበታ ላይ እንዳይገለሉ በማድረግ ሀገሮች በትምህርት ፖሊሲያቸው ውስጥ በማካተት መብታቸውን እንዲያረጋግጡላቸው አጥብቀው የሚያሳስቡ አንቀጾችን የያዘ ነው፡፡

እንደ ሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በህዝቡ ባህላዊ እምነትና አመለካከት የተነሳ የአካል ጉዳትን ካለመቻል ተፈጥሯዊ ስጦታ ጋር በማያያዝ፣ህጻናትን ወደ ትምህርት ቤት ሄደው እንዳይማሩ ወይም የተለየ ትምህርት ቤት ውስጥ ለብቻ ከማህበረሰብ ልጆች አግልለው እንዲማሩ በማድረግ የስነ ልቦና ጫና በማድረስ የመብት ጥሰት ሲደረግባቸው እንደቆየ የተደረጉ ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡፡

**አስካሁን ባለው የንባብ ሂደት ስለ አካቶ መማር ምን ተረዳችሁ?**

አካቶ ትምህርት የሁሉንም የማህበረሰብ ልጆች ተቀብሎ ያለ አንዳች ልዩነት እኩል የሚያስተናግድበት አሰራር ነው፡፡የአካል ጉዳት፣የችሎታ ልዩነት፣ጾታዊ ልዩነት፣ማንነት ትምህርትን ሊያስከለክል የሚችል ምክንያት የለውም፡፡ ስለሆነም ማንኛቸውም የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ክፍሎች ለእነዚህ ህጻናት የመማሪያ ክፍሎችን፣የመጫወቻ ስፍራዎችን፣ የመጸዳጃ አገልግሎቶችን የማንበቢያ ስፍራዎችን ምቹ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

የአካቶ ትምህርትን የሚያስተናግዱ ትምህርት ቤቶች ማወቅና ማድረግ የሚገባቸው ከሞላ ጎደል የሚከተሉት ናቸው፡፡ ስብእናን ዝቅ ከሚያደርጉ መጠሪያዎች መቆጠብ፣በቂ ድጋፍ መስጠት፣በተግባር የሚሰጡ ትምህርቶች ላይ ማሳተፍ፣ልዩነት ያለመፍጠር፣ይችላሉ ብሎ ማመንና እምነት ማሳደር፤ ምቹ የሆኑ የመጠቀሚያ ቁሶችን አስቀድሞ ማዘጋጀትና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡

ለመምህራንና ለትምህርት ቤቱ ማሕበረሰብ ክፍሎች ስለአካል ጉዳትና በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ በተመለከተ በቂ ስልጠና መስጠት ያስፈልጋል፡፡ስልጠናው የአካል ጉዳት ያለባቸውን ህጻናት ስሜት ሊጎዱ የሚችሉ ስያሜዎችን ከመጠቀም መቆጠብ፣በክፍል ውስጥ ምቹ የመማሪያ ስፍራ፣ከሌሎች ተማሪዎች እኩል በትምህርቱ ሂደት የመሳተፍ፣የማበልጸግና የመደገፍ እድል፣ በቂና ምቹ የሆኑ የመንቀሳቀሻ ስፍራዎች፣ የዕረፍት ጊዜ ማሳለፊያና መጫወቻ ቦታዎች፣ንጽህናቸውን የጠበቁ ለመጠቀም ምቹ የሆኑ የመጸዳጃ አገልግሎቶች ማግኘትን የሚመለከቱና ሌሎችንም አገልግሎቶች የሚያካትቱ ደንቦችን የያዙ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

1/ ከምንባቡ ሀሳብ ጋር የሚስማማ ከሆነ እውነት የማይስማማ ከሆነ ሐሰት በማለት መልሱ

ሀ. የአካቶ ትምህርት ውስጥ ማግለል አይፈቀድም፡፡

ለ. ስብእናን ዝቅ ማድረግ መናቅ አይደለም፡፡

ሐ. የአካል ጉዳት ያለባቸውን በተግባር ትምህርት ላይ ማሳተፍ መጉዳት ነው፡፡

2/ ‹‹የመብት ጥሰት የስነ ልቦና ጫና ያሳድራል፡፡›› የሚለውን ሃሰብ በምን መልክ ተረዳችሁት ሃሳባችሁን ለአቻችሁ አጋሩ፡፡

ሁለተኛ ሳምንት ፤አንደኛ ቀን

መጻፍ

ትምህርት አራት፡ያልተሟላ አንቀጽን ማጠናቀቅ

ከዚህ በታች የምታይዋቸው ምስሎች ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ ለዩ፡፡ ስእሎቹ አንቀጹን ለማጠናቀቅ የሚያስችል ሃሳብ ይሰጧችኋል፡፡ በመቀጠል የመጓጓዣ አይነቶች በሚል ርእስ ተጀምሮ ያልተጠናቀቀውን አንቀጽ ራሳችሁ እየጻፋችሁ አሟሉ፡፡



የመጓጓዣ ዓይነቶች

የመጓጓዣ መሳሪያዎች ሸቀጦችንና ምርቶችን ከአምራቹ ለተጠቃሚ የሚያጓጉዙና የሚያደርሱ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ሰዎችም በእነዚህ መሳሪያዎች አማካይነት ከአንድ ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ ይጓጓዛሉ፡፡ እነዚህ የመጓጓዣ አይነቶች እንደሚሰጡት አገልግሎት ተግባር ይለያያሉ፡፡ እነሱም…

ሁለተኛ ሳምንት፡ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት አምስት፡- ቃል ምስረታ

ባለፈው ትምህርት የመጓጓዣ አይነቶች በሚል ርእስ አንቀጽ አሚልታችሁ ጽፋችኋል፡፡ በአንቀጹ ውስጥ መጓጓዣ፣መጫኛ ፣መሳፈሪያ የሚሉ ቃላትን ተጠቅማችሁ ይሆናል፡፡ አነዚህ ቃላት የተመሰረቱበት ዋና ቃል አላቸው፡፡

ከዚህ በታች የተሰጡትን ምሳሌዎች ተመልከቱ

| | ዋና ቃል /ግስ/ | ቃሉ/ ስም/ |
|---|---|---|
| 1 | ሄደ | መሄጃ |
| 2 | ጫነ | መጫኛ |
| 3 | ደረሰ | መድረሻ |

ቀደም ሲል በቀረበው ምሳሌ መሰረት የሚከተሉትን ስሞች ዋና ቃል /ግስ/ጻፉ

1. ማስታወሻ _____
2. ማጠቢያ _________
3. መጻፊያ ______
4. መግረፊያ _____
5. መማሪያ_______

ሁለተኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ሰድስት፡ የቃል ክፍሎች (ስምና ፣ተውላጠ ስሞች)

ባለፈው ትምህርት አንቀጹን ስታሚሉ የራሳችሁን አረፍተ ነገር ጨምራችሁ መጻፋችሁ ይታወሳል፡፡ ከምን የቃል ክፍሎች እንደተገነቡ አስተውላችሁ ነበር? እስኪ የሚከተሉትን ምሳሌዎች ተመልከቱ፡፡

ሀ.መኪና መጓጓዣ ነው፡፡

- **መኪና** የቃል ክፍሉ ስም ነው፡፡
- **መጓጓዣ** የቃል ክፍሉ ስም ነው፡፡
- **ነው** የቃል ክፍሉ ግስ ነው፡፡

ለ. ተውላጠ ስሞች ጠቋሚዎች ናቸው፡፡

የሚከተለውን ምሳሌ ተመልከቱ፡፡

ምሳሌ፡ **እኔ** ተማሪ **ጠንክር** አባላለሁ፡፡ ወንድሜ **ዘርጋ** ይባላል ፡፡**እሱ** ወታደር ነው፡፡ አህቴ ደግሞ **ቆንጂት** ትባላለች፡፡ **እሷ** ባለትዳር ነች፡፡ **እኛ** ሁላችንም የኖርነው በመተጋጋዝ ነው፡፡

- **እኔ** የሚለው ቃል **ጠንክር** የሚለውን ስም ይጠቁማል፡፡
- **እሱ** የሚለው ቃል **ዘርጋ** የሚለውን ቃል ይጠቁማል፡፡
- **እሷ** የሚለው ቃል **ቆንጂት** የሚለውን ይጠቁማል፡፡
- **እኛ** የሚለው የሚጠቁመው ሶስታችንን ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ተውላጠ ስሞች አጠቃቀማቸውን አይታችኋል፡፡ ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ ተውላጠ ስሞች ተዘርዝረዋል፡፡ እነዚህ ተውላጠ ስሞች በሶሰት መደብ ተከፋፍለዋል ፣ ጾታና ቁጥርንም ያመለክታሉ፡፡ ጾታ ተባዕታይ /ወንድ/፣ አንስታይ /ሴት/ በሚል ይከፈላል፡፡

| አንደኛ መደብ | ሁለተኛ መደብ | ሶስተኛ መደብ |
|---|---|---|
| እኔ (ነጠላ ቁጥር)<br>እኛ (ብዙ ቁጥር) | አንተ (ነጠላ ቁጥር)<br>አንቺ (ነጠላ ቁጥር)<br>እናንተ(ብዙ ቁጥር) | እሱ(ነጠላ ቁጥር)<br>እሷ (ነጠላ ቁጥር)<br>እነሱ (ብዙ ቁጥር) |

<u>በሰንጠረዡ ውስጥ የተመለከቱትን ተወለጠ ስሞች በመምረጥ ከእያንዳንዱ መደብ አንዳንድ ተውላጠ ስም በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን ጻፉ፡፡</u>

1. ______________________________

2. ______________________________

3. ______________________________

<u>ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ</u>

1. ሁለተኛ መደብ ነጠላ ቀጥር ለሴት የሚያገለግለው ተውላጠ ስም የትኛው ነው?
2. አንደኛ ምድብ ብዙ ቁጥር አመልካች ተውላጠ ስም የትኛው ነው?
3. ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ለወንድ የሚያገለግል ተውለጠ ስምን ለዩ፡፡
4. ተውለጠ ስሞችን ተጠቅማችሁ ስምንት አረፍተ ነገሮች መስርቱ፡፡

ሶስተኛ ሳምንት፤ አንደኛ ቀን

ትምህርት ሰባት፤ የቃል ክፍሎች ፣(ተውሳከ ግስና ግስ)

ባለፈው ትምህርታችሁ የስሞች መገኛ የሆኑትን ግሶች አመጣጥ አይታችኋል፡፡ በዚህ ትምህርት ደግሞ ስለ ግስ ገላጮችና /ተውሳከ ግሶች/ እንዲሁም ስለ ግሶች እንመለከታለን፡፡

አውሮፕላን የአየር መጓጓዣ ነው፡፡በአየር መጓዝ <u>**ክፉኛ**</u> የሚያስፈራቸው ሰዎች እንዳሉ ሲነገር እንሰማለን፡፡ በመኪና መጓዝ በጣም የሚያስደስታቸው ሰዎች

እንዳሉ ሁሉ፣ የሚያስፈራቸውም ሰዎች መኖራቸውን ስናስብ **ምንኛ** ይገረመን ይሆን፡፡ እናንተስ በጣም የሚያስደስታችሁ ምን አይነት መጓጓዣ ነው?

- ከላይ ካነበብነው ጽሑፍ ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት ክፉኛ፣ምንኛ የሚሉ መሆናቸውን ተመልክታችኋል፡፡ እነዚህን ቃላት ከማን ጋር እንደተቀናጁ እንመልከት፡፡
- **ክፉኛ** የሚያስፈራቸው ክፉኛ የሚለው ቃል የመፍራት ደረጃው የከፋ መሆኑን ያመለክታል፡፡
- **ምንኛ** ይገርመን ይሆን፡ ምንኛ የሚለው ቃል የመገረም ደረጃው መጨመሩን ያመለክታል፡፡
- ክፉኛ የሚለው ተውሳከ ግስ መፍራት የሚገለጽበት ሁኔታ የከፋ ደረጃ መደረሱን ይገልጻል፡፡መፍራት የሚለው ቃል መገኛው ፈራ የሚለው ግስ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ተውሳከ ግስ የግስ ገላጭ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የሚከተሉት ተውሳከ ግሶች ከጊዜና ከሁኔታ አንጻር ግስን ይገልጻሉ፡፡

- ቶሎና ገና ጊዜን ይገልጻሉ
- ክፉኛና ምንኛ ሁኔታን ይገልጻሉ

<u>እስኪ እናንተም የሚከተሉትን ተውሳከ ግሶች ተጠቅማችሁ የራሳችሁን አረፍተ ነገሮች መስርቱ፡፡</u>


1. ቶሎ
2. ገና
3. ክፉኛ
4. ምንኛ

ሶስተኛ ሳምንት፡ሁለተኛ ቀን

ግስ /ማሰሪያ አንቀጽ

አባቴ ጎበዝ ገበሬ ነው፡፡ ሰፊ የእርሻ ቦታ አለው፡፡ብዙ ጊዜውን በስራ ያሳልፋል፡፡ መሬቱን አለስልሶ ያርሳል፡፡እንደ አባቴ ጎበዝ የሆኑ ብዙ ገበሬዎች አሉ፡፡አባቴ ብዙ ምርት ከሚሰበስቡ ጎበዝ ገበሬዎች አንዱ ነው፡፡ በአካባቢያችን በቆሎ ይመረታል፡፡ ስለዚህ ገበሬዎች በርካታ የበቆሎ ምርት አምርተው ጥሩ ገቢ ያገኛሉ፡፡

ከዚህ በታች ባለው የቢጋር ሰንጠረዥ ውስጥ ያሉ ቃላት ከላይ ካለው ጽሑፍ የተወሰዱ ናቸው፡፡ የሚገኙበት ቦታ በአረፍተ ነገር መጨረሻ ላይ ነው፡፡ አገልግሎታቸው ድርጊትን ማመልከት ነው፡፡ በአይነት ስንከፍላቸው ደግሞ የመሆንና የድርጊት ግሶች ተብለው ይጠራሉ፡፡




ከላይ የተሰጣችሁን ጽሑፍና የቢጋር ሰንጠረዥ አይታችኋል፡፡ እናንተም ከመሆን ግሶች ሁለቱን፣ ከድርጊት ግሶች ሁለቱን በመጠቀም የራሳችሁን አረፍተ ነገር ጻፉ፡፡

1. ______________________________
2. ______________________________
3. ______________________________
4. ______________________________

ሶስተኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ዘጠኝ፡ቃላትን በቃል ክፍሎች መመደብ

እስካሁን ባለው ትምህርት ቃላትን በአረፍተ ነገር ውስጥ ስትጠቀሙ ነበር፡፡ እነዚህ ቃላት ስሞች፣ ተውላጠ ስሞች፣ተውሳከ ግሶችና ግሶች ናቸው፡፡

ቃላትን ለመመደብ ከሚያስችለን መስፈርት አንዱ አገባብ ሲሆን ሌላው ደግሞ ቅርጽ ነው፡፡ አረፍተ ነገር ስትመሰርቱ አስተውላችኋል?

- ስሞች በአረፍተ ነገሮች ውስጥ በባለቤትና በተሳቢ ቦታ ይገኛሉ፡፡

- ተውለጠ ስሞች በአረፍተ ነገሮች ውሰጥ ጠቋሚ ሆነው ያገለግላሉ፡፡
- ተውሳከ ግሶች ከግስ ቀድመው በመገኘት ግሱን ይገልጻሉ፡፡
- ግሶች በአረፍተ ነገር መጨረሻ ይገባሉ፡፡

ምሳሌ፡ **ካሊድ** ልብስ **አጠበ**፡፡ ካሊድ ባለቤት፣ ልብስ ደግሞ ተሳቢ ሆኖ ገብቷል፡፡

ዳንቾ ማለት **እሷ** ናት፡፡ እሷ የሚለው ተውለጠ ስም የሚጠቁመው ዳንቾ የምትባለውን ሴት ነው፡፡

አንተ ቶሎ ሂድ፡፡ ቶሎ የሚለው ተውሳከ ግስ ነው፡፡ቶሎ የድርጊቱን ሁኔታ ያሳያል፡፡ ሂድ የሚለው ግስ ነው፡፡በአረፍተ ነገሩ መጨረሻ ላይ ይገኛል፡፡

<u>ከዚህ በታች በተመለከተው ጽሑፍ ውስጥ የተለያዩ  አረፍተ ነገሮች አሉ ፡፡ በእነሱ ውስጥ ያሉ ቃላትን በመለየት በሰንጠረዡ ምሳሌ መሰረት በቃል ክፍላቸው መድቡ፡፡</u>

> ደመናው ጠቁሯል ፡፡ ዝናብ ሊዘንብ የፈለገ ይመስላል፡፡ ኬሪያ የውሃ መቅጃ ባሊ ይዛ ወደ ምንጭ ቶሎ ቶሎ ተጓዘች፡፡ ዝናቡ ዘነበ፡፡ እሷ ግን ከዝናብ መማለጥ አልቻለችም፡፡ ወንድሟ አሊ ጥላ ይዞላት መጣ፡፡ እሱ እሷ የተሸከመችውን ባሊ አገዛት፡፡ እነሱ ዝናብ ሳይጎዳቸው ቤታቸው ደረሱ፡፡

| | ስም | ተውላጠ ስም | ተውሳከ ግስ | ግስ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ደመና | እሷ | | ይመስላል |
| 2 | | | | |
| 3 | | | | |
| 4 | | | | |

## ምእራፍ አምስት

## የተሰደዱ ስሞች

| |
|---|
| የሚጠበቁ ውጤቶች<br>ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ<br>• በተላላፊ በሽታዎች ጉዳይ ላይ የተነሳውን ሃሳብ አዳምጣችሁ አስተያየት ትሰጣላችሁ።<br>• የራሳቸሁን የሕይወት ተሞክሮ ለአቻዎቻችሁ ትናገራላችሁ።<br>• በምንባቡ መሰረት ለቃላት አውዳዊ ፍች ትሰጣላችሁ።<br>• የሕይወት ታሪክ ትጽፋላችሁ።<br>• ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ ትሰጣላችሁ።<br>• ቁጥር፣ ጾታና ጊዜ አመልካች ቅጥያዎችን ትለያላችሁ። |

አንደኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን

ትምህርት አንድ ፦ ማዳመጥ

ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ተግባር አንድ ፡የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ

ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እንዳሉ ሰምታችሁ ተውቃላችሁ? ሰምታችሁ ከሆነ አስኪ ተናገሩ።

| |
|---|
| መምህራችሁ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች በሚል ርዕስ የተጻፈ አንድ ጽሁፍ ያነቡላችኋል። ጽሑፉ ሲነበብ በትክክል አዳምጡና መምህሩ ለሚያቀርቡላችሁ ጥያቄዎች መልስ ስጡ። |

ተግባር ሁለት፡

የማዳመጥ ጊዜ፡

መምህሩ ሲጠይቋችሁ ካዳመጣችሁት ትዝ የሚላችሁን ተናገሩ፡፡

ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ተግባር ሶስት፡ ካዳመጣችሁ በኂላ ከዚህ በታች ለተመለከቱት ጥያቄዎች

በጽሁፍ መልስ ስጡ፡፡

ሀ. ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች መንስኤ ምንድነው?

ለ. እኔን ወይም በቤተሰቤን ተላላፊ ያልሆነ በሽታ ሊያጋጥመን

የሚችለው ምን ስናደርግ ነው?

ሐ. የአመጋገብ ባህሪ ለተላላፊ በሽታ የሚያጋልጠው እንዴት ነው?

አንደኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ሁለት፡-መናገር

የሕይወት ተሞክሮን መናገር

የሕይወት ተሞክሮን ለመግለጽ ስለምንከተላቸው ሂደቶች አንብቡና በዚሁ መልክ የእናንተን የሕይወት ተሞክሮ በተሰጣችሁ ምሳሌ መሰረት ጥንድ ጥንድ በመሆን ተነጋገሩ፡፡

- ስማችሁን አስተዋውቁ፣
- መኖሪያ አካባቢያችሁን ግለጹ፣
- ቤተሰባችሁን አስተዋውቁ፣
- የት እንደምትማሩ ግለጹ፡፡
- ምን አይነት ጨዋታ ትወዳላችሁ፡፡
- በትርፍ ጊዜያችሁ ምን ትሰራላችህ፡፡
- ከሰፈራችሁ ልጆች ጋር ምን ዓይነት በጎ ተግባር ትሰራላችሁ፡፡

| |
|---|
| ስሜ…ይባላል፡፡ እኔ የምኖረው… ነው፡፡ አባቴ… ሲባል እናቴ…፡፡ … እህቶችና….ወንድሞች አሉኝ፡፡ የምማረው… ት/ቤት ነው፡፡ በትርፍ ጊዜዬ…እወዳለሁ፡፡አልፎ አልፎ ከሰፈሬ ልጆች ጋር… |

እሰራለሁ፡፡

አንደኛ ሳምንት፤ ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ሶስት፡- ማንበብ /አውዳዊ ፍቺ ለማግኘት/

**የተሰደዱ ስሞች**

/በስቱደንት ኦፍ ዘ ዎርልድ/ ድረ ገጽ ዝርዝር መሠረት በስፋት ***ጥቅም*** ላይ በመዋል ከአንደኛ እስከ አሥረኛ ያለውን ደረጃ የያዙት የሴቶች ስሞች«ኤደን፣ ሣራ፣ቤቲ፣ሕይወት፣ቤዛ፣ሜሮን፣ትእግሥት፣ቃልኪዳን፣ሩት እና ሰላም» ናቸው ፡፡ የወንዶቹን ስናይ ደግሞ « ዳንኤል፣ ሰሎሞን ፣ ብሩክ ፣ዳዊት፣ ሄኖክ፣ ሳሙኤል ፣ያሬድ፣ አቤል፣ ሀብታሙ እና አሸናፊ » ናቸው ፡፡

በአሁኑ ዘመን ያለው የስም አወጣጥ መንገድ የሚከተለው***ተጽዕኖ*** ይታይበታል፡፡ የመጀመርያው ሃይማኖት ነው፡፡ በክርስቲያኖች ዘንድ አጠር ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ስሞች ***እየተዘወተሩ*** ሲመጡ በሙስሊሞችም ዘንድ አጫጭር እስላማዊ ስሞች እየተለመዱ ናቸው፡፡

ሁለተኛው ደግሞ የእንግሊዝኛ ስሞች ተጽዕኖ ነው፡፡ አሜሪካኖች ከእንግሊዝ ***ቅኝ አገዛዝ*** ነጻ ሲወጡ ካደረጓቸው ነገሮች አንዱ የእንግሊዝን ስሞች *እየቆራረጡ* በማሳጠር አሜሪካዊ ስሞችን መፍጠር ነው፡፡ እነዚህ አሜሪካውያን ስሞች በኢትዮጵያውያን ስሞች ላይ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ተጽዕኖ አድርገዋል፡፡እነ ዘውዱ« ዜድ»፣ እነ ክንዴ« ኬነዲ»፣ እነ ማርያማዊት«ሜሪ»፣ እነ ቢንያም«ቢኒ» የሆኑት በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም፡፡

ሦስተኛው ምክንያት ደግሞ አንዳንድ ስሞች ***የዘመናዊነት*** መገለጫዎች እየተደረጉ መታየታቸው ነው፡፡ ትርንጎ ከመባል «ሜሪ»፣ ስሜነህ ከመባል«ሳሚ»፣ ድፋባቸው ከመባል«ዲ»፣ አስቻላቸው ከመባል «አስቹ»፣ ቴዎድሮስ ከመባል «ቴዲ»፣ ዘውዱ ከመባል «ዜድ» ሲሳይ ከመባል «ሲስ»፣ ዘመናዊነትን እያሳዩ መጥተዋል፡፡

ስም የአንድ ሕዝብ ማንነት፣ ታሪክ፣ ባህል፣ ***ፍልስፍና*** እና አመለካከት የሚያሳይ በመሆኑ ኢትዮጵያውያን የሆኑ ስሞቻችን ባይዘነጉ መልካም ይመስለኛል፡፡ አጫጭር እና ያልተለመዱ፣ ትርጉም ያላቸው እና ለአጠራር የሚቀሉ ዓይነት ስሞችንም ቢሆን ከኛው ውስጥ መርጦ ማውጣት የሚከብድ አይመስለኝም፡፡

መንግሥታት እና ሥርዓተ ማኅበሮች በተቀያየሩ ቁጥር የመለወጥ አደጋ ከሚያጋጥማቸው ***ቅርሶች*** መካከል የአካባቢ ስሞች ዋነኞቹ ናቸው። እነዚህ ስሞች ጥቅም ላይ ውለው በነበሩበት ዘመን የተጻፉ አያሌ መዛግብት አሉ። እነዚህን መዛግብት በሚገባ ለመረዳት እነዚህ ስሞች ከነአካባቢያዊ ምልከታቸው ተመዝግበው መቀመጥ አለባቸው። ማኅበረሰቡ ለአንዳንድ ነገሮች ከዘመኑ ***ክስተት*** ጋር የተያያዘ የመታሰቢያ ስም የሚሰጥበት ጊዜ አለ።

ስሞችን የምናገኝበት መዝገብ ቢኖረን ኖሮ የማንተዋወቅ ሕዝቦች ለመተዋወቅ ምክንያት ይሆነን ነበር። ባሁኑ ዘመን ስም የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ብቻ አይደሉም። መንገዶች፣ ሕንፃዎች፣ መንደሮች፣ መኪኖች፣ ባንኮች፣ ሆቴሎች፣ ሱቆች፣ ሌሎችም ስም እየወጣላቸው ነው። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ግን ከሥራቸው እና ከሃሳባቸው ጋር ተስማሚ የሆኑ ስሞችን ማውጣት ይፈልጋሉ። አንዳንድ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ተሠርተው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ተመርተው የእንግሊዝኛ ወይንም የፈረንሳይኛ ስም የሚይዙ ምርቶች፣ አገልግሎቶች እና ሥራዎች አሉ። እነዚህን ሁሉ ሀገርኛ ማድረግ ከምንችልባቸው መንገዶች አንዱ አማራጮችን ማቅረብ ይመስለኛል።

በሀገራችን ባለቤት አልባ ሥራዎችም አሉ። ከነዚህ አንዱ ኢትዮጵያውያን ስሞችን መቀረስ ነው። በአንዳንድ ሀገሮች ገንዘብ ተከፍሏቸው ለሰዎችም ሆነ ለድርጅቶች ተፈላጊ ስሞችን የሚያወጡ ድርጅቶች አሉ። የሀገር ሽማግሌዎችንም በመጠየቅ ስሞችን የመሰብሰብ፣ የመመዝገብ እና የመቀረስ ሥራ መሥራት ታሪክን፣ ባህልን፣ ፍልስፍናን እና ማንነትን የመጠበቅ እና የመጠቀም አንዱ አካል ተደርጎ የሚቆጠር ይመስለኛል።

ምንጭ ዳንኤል ክብረት/ ከድረ ገጽ ተቀንጭቦ የተወሰደ/

/www.daniel kibret.com/

መልመጃ

<u>ለሚከተሉት ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ።</u>

1. **ተጽዕኖ**
2. **እየተዘወተሩ**
3. **ቅኝ አገዛዝ**
4. **ዘመናዊነት**
5. **ጥቅም**

6. **ፍልስፍና**
7. **ቅርሶች**
8. **ክስተት**

ሁለተኛ ሳምንት፤አንደኛ ቀን

ትምህርት አራት፡- የሕይወት ታሪክ መጻፍ

ዶ/ር ካትሪን ሐምሊን

ዶ/ር ካትሪን ሐምሊን ከባለቤታቸው ከዶ/ር ሪግ ሐምሊን ጋር በመሆን የአለማችንን ብቸኛ የፌስቱላ ሆስፒታል አዲስ አበባ ውስጥ በመክፈት ልጅ በሚወልዱበት ወቅት የፌስቱላ ችግር የገጠማቸውን ኢትዮጵያውያን ሴቶች በመርዳት የሚገኙ ሴት ነበሩ፡፡ እንደ ኤሮፓ አቆጣጠር በ1924 ዓ.ም በሲድኒ አውስትራሊያ የተወለዱት ዶ/ር ካትሪን ሐምሊን ከሲድኒ ዩኒቨርሲቲ የህክምና ትምህርታቸውን ተከታትለው ***የተመረቁት*** በ24 ዓመታቸው ነበር፡፡

በ1958 የኢትዮጽያ መንግሰት በዚያን ጊዜ ልእልት ጸሐይ ሆስፒታል የወሊድ ክትትል ባለሙያና የማህጸን ስፔሻሊሰት ለመቅጠር ‹ዘ ላንሴት› በተሰኘው የህክምና ጆርናል የወጣውን ማስታወቂያ ከተመለከቱ በኋላ ነበር በቀጣዩ አመት የሶስት ዓመት ***ኮንትራት*** ፈርመው ወደ አዲስ አበባ የመጡት፡፡ በወሊድ ላይ የሚከሰት ፌስቱላ ከዚህ ቀደም አይተው የማያውቁ ባልና ሚስት ሐኪሞች ወደ ትምህርት ቤት የሚመጡት የህመምተኞች ብዛት ስላሳሰባቸውም ፌስቱላ ላይ የሚሰራ ሆስፒታል ለመክፈት አቀዱ፡፡ህልማቸውን ከ 15 ዓመታት በኋላ የአዲስ አበባ ፌስቱላ ሆስፒታልን በመክፈት እውን አደረጉ፡፡ ዶ/ር ሐምሊንና የስራ ባልደረቦቻቸው አስካሁን ከ 34 ሺህ ለሚበልጡ አትዮጵያውያን ***የችግሩ ተጠቂዎች*** ሕክምና አደርገው ካጋጠማቸው ችግር ነጻ አድርገዋቸዋል፡፡

ዶ/ር ካትሪን ሐምሊን በዚህ ታላቅ ስራቸውም ከአውስትራሊያ፣ ከኢንግላንድና ከአሜሪካ የሕክምና ማህበራት ሽልማቶችን ተቀብለዋል፡፡ ለአድናቂዎቻቸው ‹‹የምሰራው የምወደውን ተግባር ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ከነዚህ ሴቶች ጋር መስራት ***ፈተና*** ሆኖብኝ አያውቅም›› ሲሉ የሚመልሱት ዶ/ር ሐምሊን አ.ኤ.አ 1971 በሀገራችን መሪዎች በርካታ ክብሮችን ፣***እውቅናዎችን*** ሽልማቶችን ተቀደጅተዋል፡፡ ዶክተር ሐምሊን ካትሪን የተባበሩት መንግስታት አካል በሆነው በፌስቱላ ሕክምና ላይ ላስመዘገቡት ስኬት አዲስ ***የቀዶ ጥገና*** ቴክኒክና

የህክምና ዘዴ እውቅና ተሰጥቷቸዋል፡፡እ.ኤ.አ 2001 ለረጅም ዘመን የሕክምና አገልግሎት ለአፍሪካ ***በማበርከት*** በሚል ‹ሴንቲነሪ ሜዳል› የተሰኘ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡፡ በጥር 26/1983 በማህጸን ህክምና ዘርፍ በሀገራችን ላበረከቱት ***አስተዋጽኦ*** የታወቀው ‹የኦርደር ኦፍ አውስትራሊያ› አባል እንዲሆኑ የተደረገ ሲሆን ከ 12 አመታት በኋላ በሀገሪቷ ከፍተኛ ግምት ወደሚሰጠው ‹ካምፓኒየን ኦፍ ዘ ኦርደር ኦፍ አውስትራሊያ› ክብር ከፍ ተደርጎላቸዋል፡፡ የዘመኑ ‹ማዘር ቴሬዛ› እየተባሉ ***የሚወደሱት*** አትዮጵያዊነት አጥብቆ ይሰማቸዋል የሚባልላቸው ዶክተር ካትሪን ሐምሊንን በእውቁ የአሜሪካ ቴሌቪዥን ፕሮግራም ውስጥ የምትሰራው ኦፕራ ሾው በ 20 ምርጥ ስብስቦቿ ውስጥ ስታካትት፤ በስራቸው *ተመስጣ* ወደ አዲስ አበባ በመምጣት፤ በሆስፒታሉ የሚካሄደውን ሕክምና የተመለከተ ፕሮግራም ሰርታ አስተላልፋለች፡፡

በፌስቱላ ሆስፒታል ታክመው በዳኑ አምስት ሴቶች ታሪክ ላይ የተሰራው ‹‹ኤ ወክ ኦፍ ቢውቲፉል››የተሰኘ ጥናታዊ ፊልም የዶክተር ካትሪንን ጥረት ለዓለም አሳይቷል፡፡ በ2009 ዓ.ም ከኖቤል ሽልማት ጋር የሚነጻጸረው /ላይቭሊ ሁድ አዋርድ/ ያገኙት ዶክተር ካትሪን በአውስትራሊያ መንግስት ግብዣ ከተደረገላቸው 50 ታዋቂ አውስትራሊያውያን አንዷ በመሆን በኦክቶበር 2011 በንግስት ኤልሳቤጥ በተዘጋጀ የምሳ ግብዣ ላይ ተገኝተዋል፡፡

ዶክተር ካትሪን ኢትዮጵያ ውስጥ ያሳለፉትን ህክምናና ሕይወት የሚተርክ መጽሀፍ ከጆን ሲትል ጋር በመሆን አዘጋጅተው ለንባብ አብቅተዋል፡፡

በርካቶች የፌስቱላ ተጠቂዎች በገጠራማና በቀላሉ ሊደረስባቸው በማይችሉ መንደሮች የሚኖሩ በመሆኑ ***የፌስቱላ*** ሆስፒታል በየክልሉ የህክምና ማእከላት አቋቁመዋል፡፡ሆስፒታሉና እነዚህ የክልል ማእከላት በየአመቱ 2000 ለሚደርሱ ተጎጂዎች ህክምና ይሰጣሉ፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ 60 ሺህ የሚጠጉ ህክምና ያላገኙ የፌስቱላ ተጠቂዎች የሚገኙ ሲሆን በአለም አቀፍ ደረጃ ቁጥራቸው 2 ሚሊዮን ይጠጋል፡፡ እኚህ ታላቅ ሰው ለኢትዮጵያውያን ሴቶች በአርአያነት የሚጠቀስ ተግባር ያከናወኑ አውስትራሊያዊ ቢሆኑም በተግባራቸው ግን ኢትዮጵያዊ ሆነው የዘለቁ በለውለታ ነበሩ፡፡

ምንጭ ፣አዲስ ጉዳይ መጽሔት ቁጥር 191 ህዳር 2006

ከላይ ያለውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡

1. **የተመረቁት** 4. **ፈተና**

2. ኮንትራት

5. እውቅና

3. ተጠቂዎች

6. የቀዶ ጥገና

7. በማበርከት

8. አስተዋጽኦ

9. የሚወደሱት

10. ተመስጣ

የቤት ስራ

የአንድ ታዋቂ ሰውን የህይወት ታሪክ መረጃ በመሰበስብ ጽፋችሁ በሚቀጥሉት ክፍለ ጊዜዎች አቅርቡ፡፡

ሁለተኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት አምስት፡- የሕይወት ታሪክ

በትምህርት አራት የዶክተር ሐምሊን ካትሪንን የሕይወት ታሪክን መነሻ በማድረግ ጽፋችሁ ያመጣችሁትን የሕይወት ታሪክ አንብቡ፡፡

ሁለተኛ ሳምንት፡ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ስድስት፡- የስዋስው ሕጎች /ቁጥር፣ጾታ፣ጊዜ/

የስም እርባታ /ቁጥር፣ጾታ፣ሙያ/

ስሞች ቁጥር፣ጾታና ሙያ ለሚባሉ ስዋስዋዊ ባህሪያት ቅርጻቸውን ይለዋውጣሉ፡፡ቅርጻቸውን የሚለዋውጡት ቅጥያዎችን በመጨመር ሊሆን ይችላል፡፡ ለዚህ ህግ የሚገዙ የስሞች ባህሪያትን እንመልከት

- የፊስቱላ ሕመም ተጠቂዎች ሴቶች ናቸው፡፡ አንዲት ሴት እድሜዋ ሳይደርስ ካገባች በወሊድ ወቀት በፊስቱላ ህመም ልትጠቃ ትችላለች፡፡ ወንዶች ያለእድሜ ጋብቻን መቃወም ይገባቸዋል፡፡አንድ ወንድ ሚስቱ በዚህ ህመም ከተጠቃች ከአጠገቧ ሊሸሽ አይገባም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ሴት እናት ሆና ያሳደገች ባለውለታ ስለሆነች ውለታዋን ለሚስቱ መልካም ሆኖ በመገኘት ሊከፍል ይገባል፡፡
- በዚህ አጭር ጽሑፍ ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት ስሞች ናቸው፡፡ ሴቶች-ሴት፣ወንዶች-ወንድ በሚል የቅርጽ ለውጥ በጽሁፉ ውስጥ ገብተዋል፡፡ ይህ ቅርጽ ነጠላና ብዙነትን ያመለክታል፡፡

ቁጥር መጠንን ወይም ስንትነትን የሚገልጽ ሰዋስዋዊ ባህሪ ነው፡፡የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ ስሞች አሉ፡፡አንድ ብቻ የሆነ ነገር ነጠላ፣ከአንድ በላይ የሆነ ነገር ግን ብዙ ቁጥር ይባላል፡፡

ምሳሌ

| ተ.ቁ | ስሞች/ነጠላ ቁጥር/ | ብዙ ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | ቤት | ቤቶች |
| 2 | ተማሪ | ተማሪዎች |
| 3 | ሰራተኛ | ሰራተኞች |
| 4 | ወንድ | ወንዶች |
| 5 | ሴት | ሴቶች |

ሀ. የሚከተሉትን ነጠላ ስሞች ወደ ብዙ ቁጥር ለውጡ፡፡

1.በሬ

2.ልጅ

3.ገበሬ

4.እናት

ለ . የሚከተሉትን የብዙ ቁጥር ስሞችን ወደ ነጣላ ቁጥር ለውጡ፡፡

1. ሰዎች
2. ከተሞች
3. መንገዶች
4. አስተማሪዎች

ሶስተኛ ሳምንት ፤አንደኛ ቀን

ትምህርት ሰባት፡- ጾታ

ጾታ ተፈጥሯዊና ሰዋስዋዊ ተብሎ ለሁለት ሊከፈል ይችላል፡፡ ወንድ /ተባእታይ/ ሲባል ሴት /አንስታይ/ ትባላለች፡፡

ምሳሌ

ጾታ አመልካች ያላቸው

1. ልጅ ________________ ልጂት
2. ድመት________________ ድመቲት
3. ሙሽራ________________ ሙሽሪት

ምንም አይነት የጾታ አመልካች የሌላቸው

1. አባት________________እናት
2. አጎት________________አክስት
3. በሬ ________________ላም

ከዚህ በታች የተመለከቱትን ስሞች ጾታ አመልካች የሌላቸውን ለይታችሁ ጻፉ፡፡

1. ወንድም
2. ወፍ
3. ወይፈን
4. ፍየል
5. በግ
6. ጊደር


ሶስተኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ስምንት፡- የስም ሙያ

ስሞች በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚፈጽሙት ተግባር ሙያ ይባላል፡፡ሙያቸው የባለቤትነት፣የተሳቢነት ነው፡፡የባለቤትነት ሙያ ያላቸው ስሞች የመጀመሪያውን ቦታ ይይዛሉ የተሳቢነት ሙያ ያላቸው ስሞች ደግሞ ከማሰሪያ አንቀጹ /ግሱ/ ቀድመው ይገባሉ፡፡

- እናት ልጇን አቅፋለች፡፡

ምሳሌ



የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምሳሌው መሰረት የባለቤትና የተሳቢ ሙያን በመለየት አረፍተ ነገር ጽፋችሁ አሳዩ።

1. ፈረስ
2. ተማሪ
3. ወላጅ

ሶስተኛ ሳምንት ፡ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ዘጠኝ ፡- ጊዜ

ጊዜ የምንለው ድርጊቱ የተፈጸመበትን ወይም የሚፈጸምበትን ወቅት ነው። ተፈጽሞ ያበቃን ሀላፊ ጊዜ፣እየተፈጸመ ያለ ከሆነ ያሁን ጊዜ ያልተፈጸመ ከሆነ የትንቢት/የወደፊት/ ጊዜ ይባላል።

ከዚህ በታች ባለው አጭር ጽሑፍ ውስጥ ያሉት ግሶች በጊዜ ተከፍለው ቀርበዋል፤ግሶቹ መቼ እንደተፈጸሙ ለዩ።

አባት ልጁን እንዲህ ሲል መከረው። ልጄ ዛሬ ጉልበት እያለህ ሩጥ። ሰነፎች በስንፍናቸው ምክንያት ኑሮ መሸከም ሲከብዳቸው አይተሃል። ስለዚህ ልጄ ከልሰራህ ኑሮ ይፈትንሃል። እናም አንተም ዛሬን እየሰራህ ኑር። ወደፊት የእለት እንጀራህን በሰራኸው መጠን ትበላለህ።

| | ግሱ | ጊዜ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | አሁን | ሀላፊ | ትንቢት |
| 1 | መከረ | መከረ | መክሮታል | ይመክረዋል |
| 2 | መከራት | መከራት | መክሯታል | ይመክራታል |

ከላይ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት የአሁን፣የሃላፊና የትንቢት ጊዜን በመለየት አሳዩ።

1. በላች

2. ከበደ
3. ሰራህ
4. ሰራች

የምእራፉ ማበልጸጊያ ጥያቄዎች

1. ጾታ አመልካች ቅጥያዎች ያላቸውን ሶስት ቃላት ጻፉ
2. ጊዜ አመልካች ግሶችን ከአሁን ፣ከሀላፊና ከወደፊት ጊዜ አንጻር በሶስት አረፍተ ነገሮች እየተጠቀማችሁ ስሩ።

# ምዕራፍ ስድስት

## ወዳጅ ሲከዳ

| |
|---|
| የሚጠበቁ ውጤቶች<br>ተማሪዎች ከዚህ ክፍለ ጊዜ በኃላ፡-<br>▪ የግለሰብ የህይዎት ታሪክ አዳምጣችሁ በቅደም ተከተል መልሳችሁ ትተርካላች፡፡<br>▪ መፍትሄ በሚሹ ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ችግር ፈቺ የሆነ ንግግር ታደርጋላችሁ፡፡<br>▪ አጭር ልብወለድ አንብባችሁ ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ፡፡<br>▪ ድርሰት ትጽፋላችሁ፡፡<br>▪ ስሞች ላይ ቅጥያ ምዕላዶችን በመጨመር ቅጽሎችን ትመሰርታላችሁ፡፡<br>▪ አወንታዊና አሉታዊ ዓ.ነገሮችን ትመሰርታላችሁ፡፡ |

**አንደኛ ሳምንት፡-አንደኛ ቀን**

**ትምህርት አንድ ፡-ማዳመጥ**

**ተግባር 1. ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

- የግለሰብ የህይዎት ታሪክ ሲነበብ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
- የህይወት ታሪክ ሲጻፍ ምን ምን ነጥቦች የሚካተቱበት ይመስላችኃል?

ተግባር 2. የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄ

አክሊሉ በምርምሩ ምን ውጤት የሚያገኝ ይመስላችኋል?

ተግባር 3. ካዳመጣችሁት ጽሁፍ በመነሳት የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በቃል መልሱ፡፡

1. አክሊሉ ለማ መድሐኒት ያገኘለት በሽታ ምን ተብሎ ይጠራል?
2. የበሽታው መንስኤ ምንድን ነው?
3. በሽታው የሚተላለፈው በምን ዓማካይነት ነው?
4. የበሽው መከላከያ ምን ይባላል?
5. የበሽው መከላከያ የሆነው መድሐኒት የት ይገኛል?

ተግባር4. ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት አውዳዊ ፍች ጻፉ፡፡

1. ተህዋሲያን
2. ረቂቅ
3. ረግረጋማ
4. ትጋት
5. ጽኑ

**አንደኛ ሳምንት፡-ሁለተኛ ቀን**

**ትምህርት ሁለት ፡-መናገር**

የሚከተለውን ታሪክ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ካዳመጣችሁ በኋላ ቀጥሎ በቀረበላችሁ ጥያቄ ላይ በመወያየት ንግግር ታደርጋላችሁ፡፡

በሰፈራችን ከ20 ዓመት በፊት የተቋቋመ ስልሳ አባላትን የያዘ ዕድር አለ፡፡አቶ ላዕላጎ እድሩ ሲመሰረት ከነበሩ 10 አባወራዎች አንዱ ሲሆን የእድሩን ውስጠ ደንብ ከማርቀቅ አንስቶ የተለያዩ ቁሳቁሶችን እስከ መግዛት ድረስ ከኮሚቴዎች ጋር በመተባበር ብዙ የለፋ ሰው ነው፡፡ሆኖም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አዲስ ጸባይ

በማምጣት ወርሃዊ ክፍያዎችን በወቅቱ ያለመክፈልና በእድሩ አባላት መካከል ችግር የደረሰበትን ሰው በደንቡ መሰረት ያለማገዝ ጀመረ፡፡በእነዚህ ድርጊቶች ምክንያት ከአንዳንድ አባለት በደረሰ ቅሬታ መሰረት የእድሩ ኮሚቴዎች ከአንድም ሁለት ጊዜ ጠርተው በመምከርና ገንዘብ በመቅጣት እንዲታረም ለማድረግ ቢጥሩም ሰውዬው ምንም መሻሻል አላሳየም፡፡ስለዚህ በእድሩ ወርሃዊ ስብሰባ ላይ ይህ ጉዳይ ተነስቶ ሲወያዩ ከእድሩ አባላት ከፊሉ የእድሩን ውስጠ ደንብ በተደጋጋሚ እየተላለፈ ስለሆነ ከአባልነት ይሰረዝ ሲሉ የቀሩት ደግሞ ከአባልነት ከሚሰረዝ የተወሰነ ጊዜ እንስጠውና መሻሻሉን እንጠብቅ በማለት ለሁለት ተከፈሉ፡፡

***<u>የመወያያ ጥያቄ</u>***

*እናንተ የዕድሩን አባላት ብትሆኑ ምን ሀሳብ ትሰጣላችሁ? ለምን?*

*አንደኛ ሳምንት፡- ሶስተኛ  ቀን*

*ትምህርት ሦስት ፡-ማንበብ*

ባለፈው ክፍለ ጊዜ  ከቤተ መጽሀፍትም ሆነ ከሌላ ቦታ ያገኛችሁትን አጭር ልቦለድ እንድታነቡ ትዕዛዝ ተሰጥቷችሁ ነበር፡፡ዛሬ ደግሞ ያነበባችሁትን አጭር ልብወለድ የተመለከቱ ጥያቄዎች ቀጥሎ የቀረቡ ስለሆነ በጽሁፍ ምላሽ ስጡ፡፡

1. የመጽሐፉ ርዕስ ምንድን ነው?
2. የልብወለዱ ርዕስ ምንድን ነው?
3. በልብወለዱ ውስጥ የሚገኙ ባለታሪኮች እነማን ናቸው?
4. የልቦለዱ ታሪክ የተፈጸመበትን ቦታና ጊዜ ጥቀሱ፡፡
5. የልቦለዱ ፍሬ ሀሳብ(መልዕክት) ምንድነው?

***ሁለተኛ ሣምንት፤ አንደኛ ቀን***

## ትምህርት አራት፡ ድርሰት መጻፍ

አጫጭር የድርሰት ዓይነቶች

አበይት የድርሰት አይነቶች አራት ናቸው፡፡ እነሱም ተራኪ፣ ስዕላዊ (መስታወታዊ) ገላጭ እና አመዛዛኝ ድርሰት ናቸው፡፡ እያንዳንዳቸው የተለየ ትኩረት እና ጠቀሜታ አላቸው፡፡

1. ተራኪ ድርሰት፡- ስሙ እንደሚያመለክተው ሁኔታንና ድርጊትን እንዲህ እንዲህ ሆነ፤ እንዲህ እንዲህ ተደረገ እያለ በጊዜ ቅደም ተከተል የመተረኪያ ዘዴ ነው፡፡
2. ስዕላዊ ደርሰት፡- ነገሮች፣ ሁነቶችና ድርጊቶች ለስሜት ሕዋሶቻችን እንዲደርሱና ስሜት እንዲቀሰቅሱ ተደርገው የሚቀርቡበት የድርሰት አይነት ነው፡፡
3. ገላጭ ድርሰት፡- ብዙ ጉዳዮችን ለማብራራትና ግልጽ ለማድረግ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡
4. አመዛዛኝ ድርሰት፡- አመዛዛኝ ድርሰት ከገላጭ ድርሰት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ልዩነቱ ገላጭ ጽሁፍ ማብራሪያ ብቻ ሰጥቶ ሲያበቃ አመዛዛኝ ጽሁፍ ግን አንባቢውን ወይም ሰሚውን ስለ አንድ ጉዳይ እውነትነት ወይም ውሸትነት ለማሳመን የሚጥር የድርሰት ዓይነት ነው፡፡

ሁለተኛ ሣምንት ሁለተኛ ቀን፡-

ትምህርት አምስት፡- መጻፍ/ተራኪ ድርሰት/

ተግባር አንድ፡ ከዚህ በመቀጠል የቀረበውን ተራኪ ድርሰት የድርጊት ቅደም ተከተለተሉን በመከተል በትኩረት አንብቡ፡፡

ወዳጅ ሲከዳ

እንደወትሮው ሁሉ ቀልባችን እስኪጠፋ፣ ትንፋሻችን እስኪቆራረጥ፣ ልባችን ደረታችንን እስኪደቃ በዳሰነች ወረዳ በሚገኘው ሜዳ የፀሐይ ንዳድ ሳይበግረን፣ የመሬቱ ግለት የባዶ እግራችንን ቆዳ መለብለቡ ሳያቆመን፣ ልጅነት ያጎናፀፈንን አይበገሬነት ሰንቀን በየቁጥቋጦው ስር ያለማንም ከልካይ ድብብቆሽ፣ አባሮሽ ስንጫወት እንውላለን። ለስሙ የከብቶቻችን ጠባቂ ብንሆንም ከብቶቻችንን የምናስታውሳቸው ቀኑ ለምሽቱ ተራውን ሲለቅ ብቻ ነው።

የኦሞ ወንዝ ክረምት ሲገባ ገደቡን ጥሶ አልፎ ሜዳ ላይ መተኛቱ የተለመደ በመሆኑ በቀላሉ የምናንቀሳቅሰው ጎጆአችንን ነቅለን ክረምቱ እስኪወጣ ከፍ ወዳለው ቦታ በመሄድ እንሰፍራለን። ይህን የኦሞ ወንዝ ባህሪ ስለምናውቅ ሰግተን አናውቅም።

የበቆሎ ገንፎ በወተት እያማግን እራት በልተን ከተኛን ግማሽ ለሊት አልፏል። ያልተለመደ ሁከትና ጫጫታ የከብቶቹና የጥጆቹ ማጓራት ቢሰማም የቀኑ ድካም ስለተጫነኝ ተንጋልዬ ከተኛሁበት ትንሽ ቁርበት ላይ ስገላበጥ ከጫጫታው ይልቅ በጎንና በጎን በኩል ጥሶ የገባው ቅዝቃዜ ከእንቅልፌ አነቃኝ። ባልተለመደ ግስጋሴ ከቤታችን የደረሰው የኦሞ ወንዝ እየተገማሸረ የቤታችንን ቁሳቁሶች ከወዲያ ወዲህ ያንገላታቸዋል። የዚያች ትንሽ ጎጆ ግድግዳ በኦሞ ወንዝ ተሸንፎ እናትና አባቴን እንዲሁም ሁለት እህቶቼን እንዳንገናኝ አድርጎ ለያይቶናል። የውሃው ሙላት ከመኝታዬ በቀሰቀሰኝ ቅፅበት ውሃው አንገቴ ድረስ እንደዋጠኝ ስገነዘብ ቤተሰቤን ለማስታወስ ፋታ ሳላገኝ እግሬ እንደመራኝ ከግድግዳ አልባ ጎጆዬ በዚያ ድቅድቅ ጨለማ ወጣሁ። አልፎ አልፎ ምንነቱን መለየት ያልቻልኩት አንዳች ነገር ይገፋኝና አቅጣጫ ያስቀይረኛል። በደመነፍስ ስንቀሳቀስ መሄጃዬን ሳላውቀው ስወድቅ ስነሳ እድለኛ ሆኜ ውሃው ካልደረሰበት ነጻ ስፍራ ከደረሱት ወገኖቼ አንዱ ሆኜ ተገኘሁ።

የኦሞ ወንዝ ጥማችንን ሲያረካ፣ ጨርቃችንን ሲያነፃ፣ መዝናኛችን ሆኖ ሲያጫውተን እንዳልነበር የልብ ወዳጃችን ዛሬ ግን ምን እንዳስከፋው እንጃ በእኩለ ሌሊት ገደቡን ጥሶ ንብረታችንን አንገላቶ እና አውድሞ እነሆ ዛሬ እኔን ለብቸኝነት ሕይወቴንም ለምስቅልቅል ዳርጎታል፡፡

በአዘጋጆቹ

<u>የታሪኩ ድርጊቶች በቅደም ተከተል ሲቀመጡ</u>

1. ከብት እያገዱ መጫወት
2. ሲመሽ እንቅልፍ መተኛት
3. የኦሞ ወንዝ ጎርፍ መከሰት
4. ስደት

ተግባር ሁለት <u>፡ቀደም ሲል ባነበባችሁት ተራኪ ድርሰት መሰረት እናንተም በየግልችሁ አንድ ተራኪ ድርሰት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡</u>

**ሁለተኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን**

**ትምህርት ስድስት፡ውይይትና ግምገማ**

**ተግባር፡- <u>የጻፋችሁትን ድርሰት መምህራችሁ በሚያደራጃችሁ ቡድን ገምግሙ፡፡</u>**

ከዚህ በላይ ወዳጃቻችን ሲከዳን በሚል ርዕስ ከቀረበላችሁ ተራኪ ድርሰት የተወሰነ ሀሳብ አግኝታችኋል፡፡ ቀጥሎ በቡድን በመሆን ርዕስ መርጣችሁ አንድ አጭር ተራኪ ድርሰት ጻፉ፡፡

ሶስተኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን

ትምህርት ሰባት፡- የቃላት ምስረታ

ከዚህ በታች የቀረቡትን ምሳሌዎች በጥንቃቄ ተመልክታችሁ ቀጥሎ በቀረቡት ቃላት ላይ ቅጥያ ምዕላዶችን በመጨመር ሌሎች ቃላትን መስርቱ

| ምሳሌ፡- ስም | ቅጽል |
|---|---|
| ሀይል | ሀይለኛ |
| ተራራ | ተራራማ |
| ወገን | ወገናዊ |
| ሀብት | ሀብታም |

1. ጉልበት ------------------------------------
2. ቂም ---------------------------------------
3. አሸዋ --------------------------------------
4. ድንጋይ -----------------------------------
5. ዘመን -------------------------------------
6. ሀገር --------------------------------------
7. ጥርስ -------------------------------------
8. ወረት -------------------------------------
9. ሆድ ---------------------------------------
10. ጥፍር ---------------------------------

ሦስተኛ ሳምንት፤ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ስምንት፡- ሰዋሰው

አዎንታዊና አሉታዊ አረፍተ ነገሮች

በአገልግሎታቸው ከታወቁ የአረፍተ ነገር አይነቶች መካከል አዎንታዊና አሉታዊ አረፍተነገሮች ይጠቀሳሉ፡፡

አዎንታዊ አረፍተ ነገር ስለነገሮች፣ ጉዳዮች፣ ወይም ስሜቶች ቀጥታ የሆነ አስተሳሰብን ማስተላለፊያ አረፍተ ነገር ሲሆን አሉታዊ አረፍተ ነገር በሀተታ የተነገረውን የሚያፈርስ ዓረፍተ ነገር ነው፡፡

ምሳሌ፡- ካሳ ከእናቱ ጋር ምሳ በላ፡፡ / አዎንታዊ ዓ.ነገር/

ካሳ ከእናቱ ጋር ምሳ አልበላም፡፡ / አሉታዊ ዓ.ነገር/

**ተግባር፡-**

ከላይ በቀረበላችሁ ማብራሪያና ምሳሌ መሰረት ቀጥሎ የቀረቡላችሁን ዓ.ነገሮች አዎንታዊና አሉታዊ በማለት ለዩ፡፡

ሀ. ማክቤ የቤት ስራዎችን ሰራች፡፡ ----------------------------

ለ. ኡራጎ ኀበዝ ገበሬ ነው፡፡ -------------------------------------

ሐ. ማሚቴ ጥሩ ጠላ ጠመቀች፡፡ ----------------------------------

መ. እሷ ልብሷን አላጠበችም፡፡------------------------------------

ሠ. ልጁ የታዘዘውን ስራ አልሰራም፡፡ -----------------------------

ረ. ልጅቷ ቡና አላፈላችም፡፡ ----------------------------------------

ሰ. አልማዝ የአያቷን እግር አጠበች፡፡---------------------------------

ሸ. ሻይ ቤቱ አልተዘጋም፡፡ -----------------------------------------

ሦስተኛ ሳምንት፤ ሦስተኛ ቀን

ትምህርት ዘጠኝ፡-አዎንታዊና አሉታዊ ዓ.ነገሮችን መመስረት

ቀጥሎ በቀረቡት ቃላት አስር አዎንታዊና አሉታዊ ዓ.ነገሮች መስርቱ፡፡

ሀ. ስራ

ለ. አልተለመደም

ሐ. ይከበራል

መ. አልተመረተም

ሠ. አልወለደችም

ረ. አየ

ሰ. አልተጠቀመም

ሸ. ይሆናል

ቀ. ሄደ

በ. አጠገብ

<u>የምዕራፉ ማበልፀጊያ ጥያቄዎች</u>

1. የህይወት ታሪክ ሲጻፍ ምን ምን ነጥቦች ይካተቱበታል ?
2. የድርሰት አይነቶች ምን ምንድናቸው?
3. ከተራኪ ድርሰት አላባዊያን መካከል ሦስቱን ጥቀሱ፡፡
4. የሚከተሉትን ስሞች ቅጥያ ምዕላዶችን በመጨመር ቅጽሎችን መስርቱ፡፡

   ሀ. ሀገር ---------------------------------

   ለ. ጥፍር -------------------------------

   ሐ. ድንጋይ ---------------------------

## ምዕራፍ ሰባት

## ኮተት

**<u>የሚጠበቁ ውጤቶች</u>**

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ምንባቡን አንብባችሁ ሊተላለፍ የተፈለገውን ፍሬ ሀሳብ ትናገራላችሁ፡፡
- የራሳችሁን ማህበራዊ ሚና ታብራራላችሁ፡፡
- በበጎ ተግባር ላይ ትወያያላችሁ፡፡
- የአጭር ልቦለድ ምንነትን ትገልጻላችሁ፡፡
- የአጭር ልቦለድ ባህሪያትን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- አጭር ልቦለድን አንብባችሁ ዋና ገጸ ባህሪያትን ትለያላችሁ፡፡
- የስራ ባህልን መሰረት በማድረግ በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት (አመዛዛኝ) ድርሰት ትጽፋላችሁ፡፡
- በጻፋችሁት ድርሰት አጻጻፉ ላይ ትወያያላችሁ፡፡
- የቃል ክፍሎችን ትለያለችሁ፡፡
- የዓረፍተ ነገር ክፍሎችን ትለያላችሁ፡፡
- በምሳሌው መሰረት የሰዋስው ህግን የጠበቀ ትክክለኛ ዓረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡

**አንደኛ ሳምንት፤ አንደኛ ቀን**

**ትምህርት አንድ፡- በለሆሳስ ማንበብ**

**ተግባር፡-**

ከዚህ በታች "ሱስና መዘዙ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በለሆሳስ በማንበብ ሊተላለፍ የተፈለገውን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳትና ለመናገር ሞክሩ፡፡

**የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

ከዚህ በታች የቀረበላችሁን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት፣ ከመምህራችሁ ጋር በሚከተሉት ጉዳዮች ዙሪያ ሃሳብ ተለዋወጡ፡፡

1. ሱስ ምንድነው?
2. የሱስ ጉዳቶችን ተናገሩ፡፡
3. የሚከተሉትን ቁልፍ ቃላቶችን ፍች ገምቱ፡፡

   ሀ. ውል

   ለ. አደገኛ

   ሐ. ዘለቄታው

   መ.ህልፈት

   ሠ.መጎንጨት

   ረ. ቁርኝት

**ሱስና መዘዙ**

ሱስ አንዴ ከተለመደ በኋላ በየጊዜው ውል የሚል ወይም የሚያሰኝ እንደ ትምባሆ፣ መጠጥ፣ አደንዛዥ ዕጽ፣ ቡና ወዘተ. ነገሮች ልማድ፣ አመል፣ ወይም አምሮት ነው፡፡

ሱሰኛ ሰው ሱሱን ሳያረካ አንድ ቀን እንኳን ውሎ ማደር አይችልም፡፡ ይህን ተግባር በየቀኑ ሳያሰልስ መፈጸም አለበት፡፡ ሱሱም፤ ያደንዛዥ ዕጽ ፣ የመጠጥ፣ የትምባሆም ቢሆን ልክ እንደዚሁ ነው፡፡ ይበልጥ በፈጸምነው ቁጥር የባሰውኑ በተፅፍኖ ስር እየከተተን ይሄዳል፡፡ ይህም ሆኖ ይህንን ተግባራችንን መፈጸሙን እንገፋበታለን፡፡

የሱስ ጎጂነት በሁሉም ሰው የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡፡ የጤና፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ ግንኙነት፣ የስነልቦና፣ የጊዜ ወዘተ. ጉዳቶችን በግለሰብ ፣ በቤተሰብና በማህበረሰብ ላይ ያስከትላል፡፡ ነገር ግን የዚያኑ ያህል ትኩረት የማይሰጠውና እንደቀላል የሚታይ እውነታ ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች ጠጪ ወይም አጫሽ ጓደኛቸውን "ሱሱን እንዲያቆም ለምን አትመክሩትም?" ተብለው ሲጠየቁ "እሱኮ ስለራሱ የሚያውቅ ትልቅ ሰው ነው፡፡ የኔ ምክር አያስፈልገውም፡፡ ሱስ አደገኛ እንደሆነ የሰባት አመት ልጅ እንኳን ይገነዘባል፡፡" ሲሉ ይስተዋላሉ፡፡

በርግጥም አልኮልና ሌሎች ሱስ አስያዥ ነገሮች ጎጂ ስለመሆናቸው መነገር ከጀመረ ቢያንስ በርካታ አስርት ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ ከጤና ባለሙያዎቹ ባለፈም ሱስ አስያዥ ንጥረ ነገሮቹን የሚያመርቱት ኩባንያዎችም ቢሆኑ ሱስ ለጤና ጎጂ መሆኑን እስከመግለጽ ደርሰዋል፡፡ በሲጋራ ፖኮዎች ላይ (ብዙ ጊዜ ጎላ ብሎ ባይታይም) "ማጨስ ለጤና ጎጂ ነው" የሚል ጽሁፍ ይነበባል፡፡ በአንዳንድ የመጠጥ መያዣዎችና ማስታወቂያዎች ላይም "በልኩ ይጠጡ" የሚል መልዕክት ያጋጥማል፡፡

| |
|---|
| የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች<br>1.ሱሰኛ ሰውን ምን ብላችሁ ትመክራላችሁ?<br>2.ጠጪነት ምን ጉዳት የሚያስከትል ይመስላችኋል? |

ይህም ቢሆን ሰዎችን ከሱስ ሊያስጥል ወይም በሱስ እንዳይጠመዱ ሊያደርግ አልቻለም፡፡ አለምአቀፍ የጤና ድርጅት (WHO) አልኮል መጠጣት ጤና ነክና ማህበራዊ ጉዳቶች፣ ጥገኝነት እንዲሁም ሌሎች አካላዊ ጉዳቶችን እንደሚያስከትል ያስረዳል፡፡ አልኮልን ለበርካታ አመታት መጎንጨት በግለሰቦች ላይ ከሚያደርሰው ዘለቄታዊ የጤና ጉዳት በተጨማሪ በለጋ እድሜ ለአካል ጉዳተኛነት ወይም ለህልፈት ይዳርጋል፡፡

በአጠቃላይ አልኮል ጠጪነት ከስድሳ በላይ ከሚሆኑ በሽታዎችና የጤና ጉዳቶች ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው፡፡ የአልኮል መጠጥ ለጉሮሮ ካንሰር፣ ለኩላሊት ካንሰር፣ ለጉበት፣ ለነፍስ መጥፋት፣ ለሚጥል በሽታ እንዲሁም ለተሽከርካሪ አደጋ መከሰት ከ20 - 30 % የሚሆነውን ድርሻ እንደሚይዝ የዓለም አቀፍ የጤና ድርጅት ሪፖርት ያስረዳል፡፡

## ድህረ ማንበብ /አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች

ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

1. የመጠጥ፣ የትንባሆና የአደንዛዥ እፅ ሱስ በፍፁም ልንተወው የማንችለው ነው፡፡
2. ሱሰኛ ሰው ሱሱን ሳያረካ ውሎ ማደር ይችላል፡፡
3. የቡና ሱስ ከመጠጥ ሱስ ይበልጣል፡፡
4. ሱሰኛ ሰው የሌላ ሰው ምክር አያስፈልገውም፡፡
5. ጠጪነት እስከ ሞት ሊያደርሰን ስለሚችል ከዚህ አይነት ሱሰኝነት እራሳችንን ማቀብ አለብን፡፡

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት አጭር መልስ ስጡ፡፡

1. ሱስ ይበልጥ በፈጸምነው ቁጥር የባሰውኑ በተፅእኖ ስር እየከተተን ይሄዳል ሲል ምን ማለት ነው ?
2. የሱስ ጎጂነት በሁሉም ሰው የሚታወቅ ጉዳይ ቢሆንም ትኩረት የማይሰጠውና እንደቀላል የሚታይ እውነት የሆነው ለምን ይመስላችኋል?
3. በሲጋራ ፓኮዎች ላይ "ማጨስ ለጤና ጎጂ ነው" የሚለው ፅሁፍ ብዙ ጊዜ ጎላ ብሎ የማይታየው ለምንድነው?

**አንደኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን**

**<u>ትምህርት ሁለት</u>፡- ማዳመጥና መናገር**

**ተግባር አንድ፡-** ተማሪዎች መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ "ድር ቢያብር" የሚል ምንባብ ያነብላችኋል (ታነብላችኋለች) እናንተም በጥሞና አዳምጡ፡፡





**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. (ድር ቢያብር አንበሳ ያስር) የሚለው ምሳሌያዊ ንግግር ምንን የሚገልጽ ነው?
2. ከዚህ በላይ ካሉት ምስሎች ምን እንደተረዳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

**ተግባር ሁለት፡-** ምንባቡን ካዳመጣችሁ በኋላ በአነስተኛ ቡድን ሆናችሁ በሚከተሉት የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡

**የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. የኮንሶ ማህበረሰብ የሚኖርበት አካባቢ አጠቃላይ ገጽታ ምን ይመስላል?
2. የመንደሩ ነዋሪዎች በጋራ ሆነው የሚሰሯቸው ስራዎች ምን ምንድን ናቸው?
3. የህብረት ስራው ለኮንሶዎች ምን ጥቅም አስገኝቶላቸዋል?
4. በእናንተ አካባቢ ያለው ማህበራዊ ግንኙነት ምን ይመስላል?
   በዚህ ማህበራዊ ሕይወት ውስጥ የእናንተ ሚና ምንድነው?

**አንደኛ ሳምንት፤ ሦስተኛ ቀን**

**ትምህርት ሦስት፡- የንግግር ክህሎት ማዳበር**

**ተግባር፡-** ተማሪዎች በትምህርት ሁለት በኮንሶ ማህበረሰብ ሁሉም ሰው ሕጻን፣ አዋቂ፣ ወንድ፣ ሴት ሳይል በሕብረት በመሳተፋቸው ያገኙትን ውጤት የሚገልጽ ምንባብ ማድመጣችሁና በእናንተ አካባቢም ስላለው ማህበራዊ ግንኙነት መነጋገራችሁ ይታወሳል፡፡ ዛሬም በተመሳሳይ ቡድን በመሆን እናንተ በማህበራዊ ህይወት ስላላችሁ ሚና ያረጋችሁትን ውይይት በመከለስ የጋራ አድርጋችሁ በአንድ ተወካያችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡

**ሁለተኛ ሳምንት፤ አንደኛ ቀን**

**ትምህርት አራት፡- በበጎ ተግባራት ላይ መወያየት**

**ተግባር፡-** በአነስተኛ ቡድን ተደራጁና በትምህርት ቤታችሁ በጎ አድራጎት ክበብ ስለሚከናወኑ ተግባራት ተወያዩ፡፡ በክበቡ የሚከናወኑ ተግባራት ምን ጠቀሜታ አላቸው? ይህንን ክበብ እንዴት ማጠናከር ይቻላል? ለክበቡ የገቢ ምንጭ ከየት ልታገኙ ትችላላችሁ?

***ሁለተኛ ሳምንት ሁለተኛ ቀን***

***ትምህርት አምስት፡-የንግግር ባህልን ማዳበር***

**ተግባር፡** በትምህርት አራት ስለትምህርት ቤታችሁ በጎ አድራጎት ክበብ ያደረጋችሁትን ውይይት አስታውሱ፡፡ ያነሳችሁትን ፍሬ ሀሳብ በአጭር ማስታወሻ ጻፉ፡፡ በቡድን ተወካያችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡ ።

***ሁለተኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን***

***ትምህርት ስድስት፡- አመዛዛኝ ድርሰት መጻፍ***

**ተግባር አንድ፡** ስለድርሰት ዓይነቶች የቀረበውን ማስታወሻ በጥሞና አንብቡ፡፡

## <u>የድርሰት ዓይነቶች</u>

ዋና ዋናዎቹ የድርሰት ዓይነቶች አራት ናቸው፡፡ እነሱም፡ ተራኪ ድርሰት፣ ስዕላዊ ድርሰት፣ ገላጭ ድርሰትና አመዛዛኝ ድርሰት ናቸው፡፡

አመዛዛኝ / አከራካሪ ድርሰት ÷ አከራካሪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ተመስርቶ የሚጻፍ የድርሰት ዓይነት ነው፡፡ ይህ የድርሰት አይነት አንዳንዴ ከገላጭ ድርሰት ጋር የሚመሳሰል ሊመስል ይችላል፡፡ ሆኖም ግን የተለያዩ ናቸው፡፡ ገላጭ ያብራራል፡፡ አመዛዛኝ ድርሰት ግን ያሳምናል፡፡ አንዳንዴ እስከ መስበክ ደረጃ ሊሄድ ይችላል፡፡

የአመዛዛኝ ድርሰት ዋነኛ ዓላማ፣ በሚያቀርባቸው ማስረጃዎችና በቂ ትንታኔዎች እገዛ÷ በአንባቢ ላይ የሀሳብ ተጽእኖ በማሳደር ÷ ስለ ጉዳዩ ጥልቅ ግንዛቤና ሙሉ እምነት እንዳለው ማሳየት አለበት፡፡ መረጃዎቹ የማጠቃለያው ማገናዘቢያ ናቸው ÷ እምነቱ ደግሞ የማሳመኛው መሰረት፡፡
በአመዛዛኝ ድርሰት ውስጥ የተቃራኒን ወገን የሀሳብ መሰረት ለይቶና ጠልቶ መረዳት ጠቃሚ ነው፡፡ ተቀናቃኙ ወገን የሚያነሳቸውን ፍሬ ነገሮች ቀስሞ ማውጣት ÷ እነዚያን የሚያከሽፉ ማስረጃዎችን ለማቅረብ ይረዳልና ነው፡፡ የሚጻፈው ነገር÷ የአንድን ነገር እውነትነት ወይም ሀሰትነት በምክንያት በማሳየት ÷ የጸሐፊውን እምነት ከጥቃት መከላከል መቻል አለበት፡፡ ብሎም የተቃራኒው ሀሳብ ባለቤት ሰለባ ያደረጋቸውን ሰዎች ወደራሱ እምነት ማምጣት ይሞክራል፡፡ ለዚህም ነው የተቃራኒን ወገን ሀሳብ ማወቅ የሚገባው፡፡

ተማሪዎች የአመዛዛኝ ድርሰት አስረጂ ቀጥላችሁ ተመልከቱ፡፡
ትዳር በሰው ልጆች መሰረታዊ ፍላጎቶች ተርታ ባይመደብም የወደፊት የህይወት አቅጣጫን ከመምራት አንፃር ሲታይ ግን እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ጥረህ ግረህ የምታገኘውን የወር ገቢ በአግባቡ ለመጠቀምና በእቅድ ለመምራት ትዳር ወሳኝነት አለው፡፡ ልጅ ወልዶ ለመሳም እና አሳድጎ ለቁም ነገር ለማብቃት፣ ከሀሳብ ነጻ ለመሆንና ደስተኛነትን ለማትረፍ፣ ቤት ንብረት ለማፍራት ፣ ከዝሙት ለመራቅና በዚህ ሳቢያ ከሚተላለፉ የጤና ጠንቆች ለመዳን፣ መድሃኒቱ ትዳር መስርቶ አንድ ለአንድ ፀንቶ መገኘት ብቻ ነው፡፡
ወንደላጤነት የብቸኝነት እስር ቤት እንጂ ኑሮ አይደለም፡፡ ሁልጊዜ

ብስጩ ያደርጋል፡፡ ገንዘብን ያለአግባብ ከማባከንና ያለ ዕቅድ ከመመራት በተጨማሪ በሕይወት ላይ ያለው አሉታዊ ተጽእኖ ቀላል አይደለም፡፡ ወንደላጤ ከሀሳብ ነጻ ለመሆን የሚወስደው አማራጭ መጠጥ ነው፡፡ ከጠጡም መስከርና ለዝሙት መጋለጥ ይመጣል፡፡ ወንደላጤ ከኢኮኖሚያዊ ክስረት እስከ ሞት ለሚያደርሱ ችግሮች የመጋለጥ እድሉ ሰፊ ነው ፡፡ ባለትዳር ግን ከእነዚህ ሁሉ ነገሮች የሚርቅበት አማራጭ አለው፡፡

አንዳንድ የዋሆች ÷ትዳር መመስረት ማለት በገዛ እጅ እስር ቤት እንደመግባት ነው ይላሉ፡፡ ይህ ቁንፅል አስተያየት ነው፡፡ ለዚህ ሀሳባቸው ሊያቀርቡ የሚችሉት ማሳመኛ ነጥብ የለም፡፡ በመሰረቱ ትዳር መመስረትና ቤተሰብ ማፍራት ትልቅ ኃላፊነት የመሸከም ምልክት ነው፡፡ አንድን ማህበረሰብ የመምራት ያህል የሚቆጠር እንጂ እስር ቤት ውስጥ እንዳለን አይነት የሚያዋርድ አይደለም፡፡ የህይወትን ምንነት ካጣጣሙና ትልልቅ ኃላፊነቶችንም ከተቀበሉ ሰዎች ጎራም የሚያስለፋ ነው፡፡

ምንጭ - የሻው ተሰማ፡፡ 1996 ዓ/ም፡፡
ልሳነ ብዕር ከመ ልሰነ ስብእ፤
ብራና ማተሚያ ድርጅት ገጽ 270 - 279

**ተግባር ሁለት**፡- ከዚህ በላይ በአነበባችሁት ማስታወሻና አስረጃ በሆነው አመዛዛኝ ድርሰት መሰረት <u>የአካባቢያችሁን የስራ ባህል</u> መሠረት ያደረገ አመዛዛኝ ድርሰት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ

**ሶስተኛ ሳምንት፤ አንደኛ ቀን**

**<u>ትምህርት ሰባት</u>፡- በጻፉት አመዛዛኝ ድርሰት አጻጻፍ ስርዓት ላይ መወያየት**

**ተግባር**፡- ባለፈው ትምህርት ስድስት ስር የቀረበላችሁን የድርሰት ዓይነቶች

ማስታወሻ እና የቀረበላችሁን አስረጂ አስታውሱ፡፡ በዚህ መሰረት የጻፋችሁትን አመዛዛኝ ድርሰት የአጻጻፊ ስርዓት በተመለከተ በቡድን ተወያዩ፡፡ የቡድናችሁን ሀሳብ በተወካዮቻችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

## <u>ሦስተኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን</u>

## ትምህርት ስምንት፡- አጭር ልቦለድን በማንበብ የአጻጻፍ ዘዴውን መመርመር

**ተግባር አንድ፡-** <u>ከዚህ በታች አጭር ልቦለድ ታሪክ ቀርቦላችኋል፡፡ ታሪኩን በጥሞና አንብቡና የአጻጻፍ ዘዴውን መርምሩ፡፡</u>

### ኮተት

ከቅብጠታት አንድ ቀን፣ አቶ አልአዛር ሲያቀብጣቸው ውሻቸውን ኮምቡጠርን ሁለት መለኪያ አረቄ የተቀላቀለበት ክትፎ አኮመኮሙት፡፡

‹‹እናንተ የሰው ልጆች ኮተታሞች ሲበዛ!›› አላቸው፣

‹‹አረቄዋ ከመቼው ስራዋን ሰራች!›› እያሉ ውስጥ ውስጡን፣

‹‹እንዴት እባክህ?›› ሲሉት፣

‹‹የልብሳችሁ ብዛት ሙታንታ - ካናቴራ - ሸሚዚ - ሹራብ - ኮት - ካፖርት - ባርኔጣ - ካልሲ - ጫማ - ቀበቶ - ጡት መያዣ፣አንሶላ - ብርድልብስ - አልጋ ልብስ - ፎጣ፣ኧረ ወዲያ፣ኮተታም ዘር!››

‹‹ኧረ ባክህ? እናንተስ?››

‹‹እኛማ ፀጉራችን በቃን፡፡ ፀጉራችን - በቃይ ከውስጣችን!››

‹‹እሺ!!!››

‹‹ማበጠሪያ፣ ፀጉር መያዣ፣ ፀጉር መጠቅለያ፣ የፀጉር ቅባት፣ የ…››

‹‹በቃህ አታንዛዛብኝ!››

‹‹ደሞ የቤታችሁ ጣጣስ? ማዕድ ቤት - ምግብ ቤት - እንግዳ ቤት - ሽንት ቤት…እቃ ቤት - ወንበር - ጠረጴዛ…ሶፋ - ምንጣፍ - አልጋ - ቁም ሳጥን - አግድም ስጥን! ሌላ ኮተት ዝባዝንኪ ግሳንግስ!…››

‹‹ወይ ጉድ!››

‹‹ሳህን - ማንኪያ - ሹካ - ኩባያ - ብርጭቆ - ጠርሙስ ፣ ድስት - ጋን - ገምቦ፣ ሰፌድ - መሶብ - አገልግል፣ ሞፈር - ቀምበር - ኮርቻ - ወስፈንጥር - ወስፌ››

‹‹እሰይ የኛ አዋቂ!››

‹‹ግሳንግስ - ቅራቅንቦ! - ጋሪ - ብስክሌት - ዶቅዶቄ - መኪና - ባቡር - መርከብ - ኤሮፕላን - በሮኬት ጨረቃ ላይ መውጣት››

‹‹ዝም በል አልኩህ፤ ሰካራም የውሻ ልጅ!››

‹‹ጠላ - ጠጅ - አረቂ - ወይን፣ ገበሬ - ነጋዴ - ቄስ - ጠበቃ - ዳኛ - አናጢ››

‹‹ኧረ በሕግ አምላክ ተወኝ!››

‹‹ደሞ የሕጋችሁ ብዛት፣ ወንጀለኛ መቅጫ - ፍትሐብሔር - የባሕር ንግድ - የሥነ ሥርዓት - አቤት ግሳንግስ ኮተት!››

‹‹ልብ አርግ፣ ዋ!››

‹‹ደግሞ የክሳችሁ አይነት፣ ሰካራም ፣ ተሳዳቢ፣ አጭበርባሪ፣ ነብሰገዳይ፣ እጅ እላፊ፣ አፍ እላፊ…››

‹‹አሁንስ በቃ!›› አሉና ተነስተው አነስተውት በሩን ከፍተው ውጭ አስቀምጠውት ተመልሰው በሩን ዘጉት፡፡

‹‹ሰካራም የውሻ ልጅ!›› እያሉ ግማሽ እየሳቁ፣ ለራሳቸው ሲመርቁላቸው አንድ መለኪያ አረቂ ቀዱ፡፡

ምንጭ፡- ስብሀት ገብረእግዚአብሄር

ተሻሽሎ የተወሰደ

<u>**ተግባር ሁለት**፡- ያነበባችሁትን ልቦለድ መሰረት በማድረግ መልመጃዎችን ስሩ፤ ዋና ገጸ ባህሪያትን ለዩ፤ የልቦለድ ባህሪያትን ለመለየት ሞክሩ፡፡</u>

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በልቦለዱ መሰረት እውነት ወይም ሐሰት በማለት በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. አቶ አልአዛር ቀበጥ ናቸው፡፡
2. አቶ አልአዛር ኮምቡጠር የሚባል ልጅ አላቸው፡፡
3. ኮምቡጠር ሁለት መለኪያ አረቄ የተቀላቀለበት ክትፎ ኮመኮመ፡፡
4. ኮምቡጠር ሲሰክር በድፍረት መናገር ጀመረ፡፡
5. ‹‹የቤታችሁ ጣጣ›› የተባለው በሰዎች ቤት ያለ አለመግባባት ነው፡፡

በ"ሀ" ስር ያሉትን ቃላት ከላይ ባነበባችሁት ልቦለድ መሠረት፣ በ "ለ" ስር ካሉት መግለጫዎች ጋር አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ካናቴራ | ሀ. የእርሻ መሣሪያ |
| 2. ገምቦ | ለ. መንጓዣ |
| 3. ዶቅዶቄ | ሐ. መዋቢያ ቁሳቁስ |
| 4. ቀምበር | መ. የልብስ አይነት |
| 5. ማበጠሪያ | ሠ. የቤት ቁሳቁስ |

ሦስተኛ ሳምንት፤ ሶስተኛ ቀን

**ትምህርት ዘጠኝ፡- የአጭር ልቦለድ ምንነትንና የአጭር ልቦለድ ባህሪያትን መገንዘብ**

**ተግባር አንድ፡-** ከዚህ በታች ስለአጭር ልቦለድ ምንነትና የአጭር ልቦለድ ባህሪያት የቀረበላችሁን ማስታወሻ በጥሞና አንብቡ፡፡ መምህራችሁ የሚሰጡትን ገለጻም ተከታተሉ፡፡

## የአጭር ልቦለድ ምንነት

አጭር ልቦለድ የራሱ ቅርፅና ይዘት ያለው ከሌሎች የስነ ፅሁፍ ዘሮች ተለይቶ የሚታወቅባቸው ባህሪያት ያሉት በራሱ ክልል ሲጠናና ሲመረመር የራሱ የሆነ ኪነጥበባዊ ስርዓት የሚታይበት በራሱ መጠነ ርዕይ ውል ያላቸውን ማሕበረሰባዊ እውነታዎችን ሊያሳይ የሚችል አንድ የስነ ፅሁፍ ዘር ነው።

አጭር ልቦለድ ከአስር ሺህ ቃላት በታች የሚይዝ፣ አንድ ዋነኛ ግብ ለማምጣት የተዋቀረና ተውኔታዊነት የሚታይበት አጠር ያለ ትረካ ነው። አጭር ልቦለድ በአንድ ቅጽበት በአንድ ነጠላ ሁነት ውስጥ በሚያልፍ አንድ ገጸ ባህሪ ላይ ያተኩራል። የተዋጣለት አጭር ልቦለድ በተወሰነ መቼት (ጊዜና ቦታ) የተቀረፀና አንድ ሁነት ውስጥ ገብተው በሕሊናዊ ወይም በአካላዊ ድርጊት የሚሳተፉ አንድ ወይም ጥቂት ገፀባህሪያትን ይይዛል። ግጭት ወይም የተጻራሪ ሀይላት ፍጭት የማንኛውም አጭር ልቦለድ እንብርት ነው።

በአጠቃላይ አጭር ልቦለድ ስብስብ ያለ ወይም የታመቀ፣ የጠበቀ ትስስር ያለው ፣ ፈጣንነት ጎልቶ የሚታይበትንና የሁሉም ነገር መቋጫ የሆነ አንድ ብቸኛ የትኩረት ነጥብ ያለው የልቦለድ አይነት ነው

## የአጭር ልቦለድ ባሕርያት

ዋነኛው የአጭር ልቦለድ ባህሪ ነጠላ ውጤት ነው። ነጠላ ውጤት ሁሉም የአጭር ልቦለድ አካላት ተሳስረው ወደ አንድ ዋነኛ ትኩረት የሚፈስሱበትና ደራሰው በአንባቢው አዕምሮ ተቀርጾ እንዲቀር የሚፈልገው አንድ ኪነ-ጥበባዊ ግብ ነው።

ሁለተኛው የአጭር ልቦለድ ዋኛ ባህሪ ጥድፊያ ነው። የሚቀርበው ታሪክ ብዙም ሳይጠማዘዝ ቶሎ ቶሎ መተረክ አለበት። ትልሙና የተለያዩ ክፍሎቹ ፍሰታቸውን ጠብቀው ዝርዝር ነገር ሳያበዙ የተስፋፋ የመቼት ገለጻና የገጸ ባህሪ ዳራ ሳይሰጥ በፍጥነት መጓዝ አለባቸው።

ሦስተኛው አጭር ልቦለድ ባህሪ ቁጥብነት ነው። ቁጥብነት በዋነኛነት በአጭር ልቦለድ አለባውያን አኗኗርና እርስ በርስ በሚፈጥሩት አይቀሬ ቅንጅት ውስጥ

የሚታይ ነው፡፡

ነጠላ ታሪክ ፣ በጣም ጥቂት ገጸ ባህሪያት ፣ ጠባብ መቼት ፣ ነጠላ ግጭት ፣ አንድ ጭብጥ (ነጠላ ውጤት ) ወዘተ. የቁጥብነቱ መገለጫዎች ናቸው፡፡

ምንጭ፡- ዘሪሁን አስፋው ፡፡ 1992 ዓ/ም፡፡ የስነ ጽሁፍ መሰረታዊያን ንግድ ማተሚያ ድርጅት ገጽ 228-230

ተግባር ሁለት፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ በጽሁፍ አቅርቡ

1. አጭር ልቦለድ ምንድነው ?

-------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------

2. የአጭር ልቦለድ ባህሪያትን ጥቀሱ፡፡

ሀ. ---------------------------------------------

ለ. ----------------------------------------------

ሐ. ---------------------------------------------

ባለፈው ክፍለ ጊዜ ባነበባችሁት ኮተት በሚለው ልቦለድ ታሪክ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ጻፉ፡፡

1. በልቦለዱ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገው ጭብጥ ምንድነው?

-------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------

2. በልቦለድ ታሪኩ ውስጥ ጥድፊያ እንዴት ይገለጻል?

-------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------

3. የልቦለድ ታሪኩ ቁጥብነት መገለጫዎችን ጥቀሱ፡፡

------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------

4. በልቦለድ ታሪኩ ውስጥ ስንት ገጸ ባህሪያት አሉ? ጥቀሷቸው፡፡

------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------

5. ታሪኩ የተፈጸመበትን መቼት ጥቀሱ፡፡

ቦታ -------------------------------------------------------------------------

ጊዜ -------------------------------------------------------------------------

**አራተኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን**

**ትምህርት አስር፡-** በልቦለድ ታሪኩ ውስጥ በታዩ አዳዲስ ነገሮች ዙሪያ መወያየት

**ተግባር አንድ፡-** ባነበባችሁት ታሪክ ውስጥ ከቋንቋ፣ ከባህል፣ ከገጸባህሪያት ረገድ የገጠማችሁን የተለየ ነገር በተመለከተ በቡድን ተወያዩና ሃሳባችውን በቡድን ተወካዮቻችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

**ተግባር ሁለት፡-** ከክፍል ውጪ በትርፍ ጊዜያችሁ ቢያንስ ሁለት፣ ሁለት አጭር ልቦለዶች አንብቡ፡፡ የልቦለድ ድርሰት አላባውያንን እና የአጭር ልቦለድ ባህሪያትን ትኩረት አድርጉባቸው፡፡

**አራተኛ ሳምንት፡ ሁለተኛ ቀን**

**ትምህርት አስራ አንድ፡-** ሰዋሰው (የቃል ክፍሎች)

**ተግባር፦** የአማርኛ የቃል ክፍሎችን የተመለከተ አጭር ማስታወሻ ቀርቦላችኋል፡፡ በጥሞና አንብቡ፡፡

## የቃል ክፍሎች

የአማርኛ የቃል ክፍሎችን ለመጀመሪያ ጊዜ በአምስት የከፈላቸው ኢትዮጵያዊ የስነ ልሳን ምሁር ባየ ይማም በ1987 ዓ/ም በጻፈው የአማርኛ ሰዋሰው በሚለው መጽሐፉ ነው፡፡ በዚህ የስነ ልሳን ምሁር የተዘረዘሩት የቃል ክፍሎችም ፦

1. ስም
2. ግስ
3. ቅጽል
4. መስተዋድድ እና
5. ተውሳከ ግስ ናቸው

ምሳሌ፦

| ስም | ቅጽል | ግስ | ተውሳከ ግስ | መስተዋድድ |
|---|---|---|---|---|
| ካሳ | ትልቅ | ሰበረ | ገና | ከ |
| አበበ | የዋህ | ደከመ | ቶሎ | እንደ |
| በግ | ብልህ | ሰማ | ክፉኛ | ስለ |
| ቤት | ትሁት | አገባ | ምንኛ | ወደ |
| ልጅ | ደግ | መሸ | | በ |
| ሰው | ሞኝ | ሰረቀ | | ለ |
| ሴት | በጎ | ቀበረ | | |
| ምስል | ፈጣን | አሰበ | | |
| ስካር | ሰነፍ | ተጨ | | |
| ደግነት | ረጅም | አሰሰ | | |
| ከተሜ | ክቡር | ሞከረ | | |
| ስጦታ | ልበ ቅን | ቆለፈ | | |
| ት/ቤት | ሆደ ሰፊ | ጠጣ | | |
| | | ማረከ | | |

ምንጭ፦ ጌታሁን አማረ 1989 የአማርኛ ሰዋሰው በቀላል አቀራረብ ገጽ 46-199

ከዚህ በታች የተሰጡአችሁን ቃላት የቃል ክፍል ለይታችሁ ጻፉ፡፡

| ተ/ቁ | ቃል | የቃል ክፍል |
|---|---|---|
| 1 | በሬ | |
| 2 | ተማሪ | |
| 3 | መጣ | |
| 4 | እንደ | |
| 5 | ቶሎ | |
| 6 | ብርጭቆ | |
| 7 | ገረፈ | |
| 8 | አጭር | |
| 9 | ፈረስ | |
| 10 | ዘመናዊ | |

**አራተኛ ሳምንት፤ ሦስተኛ ቀን**

**ትምህርት አስራ ሁለት፡- የአረፍተ ነገር ክፍሎች**

**ተግባር፡-** የአረፍተ ነገር ክፍሎች አጭር ማስታወሻ ቀርቦላችኋል፡፡ በጥሞና አንብቡት፡፡

**የአረፍተ ነገር ክፍሎች**

አረፍተ ነገር ሙሉ ሀሳብን መግለጽ የሚችል የሁለት ሀረጎች ቅንጅት ነው፡፡

እነሱም፦ ስማዊ ሀረግ እና ግሳዊ ሀረግ ናቸው፡፡

ምሳሌ፡-1. ገመዶ መጣ፡፡

ገመዶ - ስማዊ ሀረግ

መጣ - ግሳዊ ሀረግ

2.አስቴር ብርጭቆውን ሰበረችው፡፡

አስቴር - ስማዊ ሀረግ

ብርጭቆውን ሰበረችው - ግሳዊ ሀረግ

3.መዲና ወደ ገበያ ሄደች፡፡

መዲና - ስማዊ ሀረግ

ወደ ገበያ ሄደች - ግሳዊ ሀረግ

<u>ከዚህ በታች የተሰጧችሁን አረፍተ ነገሮች ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ ለይታችሁ ጻፉ</u>

1. ኛካል ተማሪ ነው፡፡

   ስማዊ ሀረግ ----------------------------

   ግሳዊ ሀረግ ------------------------------

2. ዘነበች እናቷን ትመስላለች፡፡

   ስማዊ ሀረግ ----------------------------

   ግሳዊ ሀረግ ------------------------------

3. ተማሪዎቹ ደብዳቤ ጻፉ፡፡

   ስማዊ ሀረግ ----------------------------

   ግሳዊ ሀረግ -----------------------------

4. ለቤና በመኪና ወደ ሆሳዕና ሄደ፡፡

   ስማዊ ሀረግ ----------------------------

   ግሳዊ ሀረግ -----------------------------

5. ሰይድ የገዛው መጸሐፍ ጠፋ፡፡

ስማዊ ሀረግ ----------------------------

ግሳዊ ሀረግ -----------------------------

ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ ያላቸው አረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

1. ------------------------------------------------------------------------------------
2. ------------------------------------------------------------------------------------
3. ------------------------------------------------------------------------------------
4. ------------------------------------------------------------------------------------
5. ------------------------------------------------------------------------------------

## የምዕራፉ ማበልጸጊያ ጥያቄዎች

ሀ. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት የቃል ክፍል

ለይታችሁ ተናገሩ፡፡

1. ጂንካ የደቡብ ኦሞ ዞን ዋና ከተማ ናት፡፡
2. ጦና የተከበሩ የወላይታ ንጉስ ነበሩ፡፡
3. የአማሮ ቡላ ከፍተኛ ጥራት አለው፡፡
4. ሦርሳ ቀይ አውራ ዶሮ ገዛ፡፡
5. ኤርጎጌ ወደ አሜሪካ ሄደች፡፡

ለ. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ቃላት በቃል

ክፍሎች እየለያችሁ አሳዩ፡፡

ምሳሌ፡- ሾፌሩ በፍጥነት ሲነዳ አደጋ አጋጠመው፡፡

ሾፌሩ (ስም)

በፍጥነት (ተውሳከ ግስ)

ሲነዳ (ግስ)

አደጋ (ስም)

አጋጠመው (ግስ)

1. ሆርዶፋ ጥሩ ሰው ነው።

2. ሰውዬው አዘውትሮ ፍራፍሬ ይመገባል።

3. ማንዴላ ሰላም ወዳድ መሪ ነበር።

ሐ.ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረጎችን ለይታችሁ አውጡ።

ምሳሌ፡- እሷ የኔ የክፍል ጓደኛ ናት።

ስማዊ ሀረግ - እሷ

ግሳዊ ሀረግ - የኔ የክፍል ጓደኛ ናት

1. ዱሎ ዛሬ ወደ ወራቤ ሄደ።
2. ሲማቶና ኢርባ ጓደኛሞች ናቸው።
3. የኮሌጃችን ተማሪዎች ፀረ ኮቪድ 19 ክትባት ተከተቡ።

## ምእራፍ ስምንት

## ወራሾቹ

አንደኛ ሳምንት፡አንደኛ ቀን

ትምህርት አንድ፡ማዳመጥ




ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ተግባር አንድ፡ <u>የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡</u>

1. ስእሉን አይታችሁ የምንባቡን ርእስ ገምቱ፡፡
2. ደቡብ ክልል የሚገኙ ብሔሮችና ብሄረሰቦች ቁጥር ምን ያህል ይሆናል?
3. ብዛታቸውና ልዩነታቸው ያመጣው ጸጋ ምን ይመስላችኋል?

ተግባር ሁለት፡ ከዚህ በመቀጠል መምህራችሁ ምንባብ ያነቡላችኋል፡፡ምንባቡን በጥንቃቄ አዳምጡ፡፡

የማዳመጥ ሂደት፡ መምህራችሁ ሲጠይቋችሁ በቃል መልሱ፡፡

ተግባር ሶስት፡ የሚከተሉትን የድህረ ንባብ ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

1. ብዝሐነት ውበት ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?
2. ልዩነት ውበት የሆነው ምን ስለሆነ ነው?
3. ስለ ብዝሐነት የሰማችሁትን ለቡድን ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡
4. ብዝሐነት ባለው ክልል በመኖራችሁ የሚሰማችሁን ስሜት አጠገባችሁ ለሚገኘው ተማሪ ግለጹ፡፡

አንደኛ ሳምንት፡-ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ሁለት፡-መናገር/ሃሳብ አፍልቆ በፍጥነት መናገር

ማንኛውም ሰው ስለራሱ መናገር ይችላል፡፡ ለሰው የሚናገረው ነገር ስለሚያውቃቸው ነገሮች ከሆነ በፍጥነት መናገር አያስቸግረውም፡፡ እናንተም ተናገሩ ብትባሉ ሃሳብ ለማመንጨት አትቸገሩም፡፡ ለመናገር ማሰብ ይቀድማል፡፡ ስለምን ልናገር ብሎ ማሰላሰል ያስፈልጋል፡፡

እናንተም ከዚህ በታች ያሉትን መመሪያዎች ተከትለችሁ ተናገሩ፡፡

1. ራሳችሁ ምን እንደምትናገሩ አስቡ፡፡
2. ያሰባችሁትን በፍጥነት ለጓደኛችሁ ተናገሩ፡፡
3. ቀጣዩን ተራ ለጓደኞቻችሁ ስጡና በፍጥነት ሲናገሩ አዳምጡ፡፡

አንደኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ሶስት፡- የተራኪ ጽሁፍ አላባውያን

ወራሾቹ

በወይና ቀበሌ አብዲናጎና ካሚቴ የተባሉ አንድ ወንድና አንዲት ሴት የባለፀጋ ልጆች ነበሩ፡፡ ከወላጆቻቸው በርካታ ንብረቶችን በውርስ ስላገኙ ሥራ አይወዱም ነበር፡፡ የክረምቱ የእርሻ ወቅት አልፎ በበጋው ጸደይ ወር ዋዜማ በሳምንቱ የመጀመሪያው ቀን አባታቸው ከመሞቱ በፊት ጎረቤት ከሁለት አመት በፊት ቆልፎ ያስቀመጠላቸውን ዕቃ መከፋፈል ፈለጉ፡፡ ወንዱ "እኔ ታላቅ ስለሆንኩ ካንቺ የሚበልጠውን መውሰድ አለብኝ እንጂ፣ እኩል መካፈል የለብኝም" ሲል፣ ሴቷ ደግሞ "አባቴ እጅግ ይወደኝ እንደነበር ታውቃለህ፣ ስለዚህ መውሰድ ያለብኝ እኔ ነኝ" በማለት መጨቃጨቅ ጀመሩ፡፡

መስማማትም ስላልቻሉ፣ሳጥኑን በአደራ ካስቀመጡላቸው ሽማግሌ ቤት ሄዱ፡፡ሁለቱም ሀሳባቸውን ለሽማግሌው በየተራ ገለፁ፡፡ ሽማግሌውም በልጆቹ ሀሳብ በጣም ተገረሙ፡፡ "ልጆቼ አባታችሁ ደግ ሰው ነበር፡፡ ለሰዎች የሚያዝን፣ ለእኔ ከማለት ይልቅ ለእናንተ የሚል ቸር ነበር፡፡ ለዚያ ደግነቱ ወሮታ የመለስኩ ስለመሰለኝ ፣የአባታችሁን አደራ ለሁለት አመታት ጠብቄ አቆይቼላችኋለሁ፡፡እንዳይባክንባችሁም በማሰብ እስካሁን ሳልነግራችሁ ቆይቻለሁ፡፡ አሁንም በውስጡ ያለውን ሀብት ባላውቅም ተስማምታችሁ እንድትከፋፈሉ እለምናችኋለሁ፡፡ አንተም ታላቅ በመሆንህ አንቺም ታናሽና ተወዳጅ በመሆንሽ የበለጠውን መውሰድ አለብኝ አትበሉ፤ ሁላችሁም እኩል ልትካፈሉ ይገባል" በማለት አግባቧቸው ፡፡ ሁለቱ ወራሾችም ሽማግሌው ባሉት መሠረት እኩል ሊከፋፈሉ ተስማሙ፡፡ሽማግሌውም በአደራ ያስቀመጡትን ከልጆቹ ፊት አቀረቡ፡፡ ልጆቹም ሳጥኑን በአባታቸው ፊርማ መታሸጉን አረጋገጡ፡፡ ከዚያም በሽማግሌው እጅ ሳጥኑ እንዲከፈት ተስማሙ፡፡ ሽማግሌውም ሳጥኑን ከፈቱት፤ በውስጡ ግን ልጆቹ እንዳሰቡት ወርቅ ሳይሆን ምክር የያዘ መጽሐፍ ሆኖ ተገኘ፡፡ ሽማግሌውም በልጆቹ አባት ብልህነት በጣም ተደነቁ፡፡የማያልቅ የሀብት ምንጭ የሆነውን መጽሐፍ በመዋዋስ እንዲያነቡትና እንዲጠቀሙበት አሳስበው አሰናበቷቸው፡፡

(አማርኛ እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ የተማሪው መጽሐፍ 6ኛ ክፍል ከገጽ112-113 ማሻሻያ ተደርጎበት የተወሰደ)

*መልመጃ*

ከላይ የተመለከተውን አጭር ተራኪ ጽሑፍ ካነበባችሁ በኋላ የሚከተሉትን የተራኪ ጽሑፍ አላባውያን ለዩ፡፡

| የተራኪ ጽሑፍ ካርታ | |
|---|---|
| መቼት | ታሪኩ የተፈጸመው መቼ ነው? |
| | ታሪኩ የተፈጸመው የት ነው? |
| | |
| ገፀ ባህሪያት | በታሪኩ ውስጥ ያሉት ዋና ዋና ሰዎች እነማን ናቸው |
| | |
| ችግር | ዋና ገፀ ባህሪው ያጋጠመው ችግር ምንድን ነው? |
| | |
| ሤራ | በታሪኩ ውስጥ የተፈጠሩት ዋና ነገሮች ምንድን ናቸው? |
| | |
| አጨራረስ | በታሪኩ ውስጥ የተከሰተው ችግር እንዴት ተቋጨ? |
| | |

ሁለተኛ ሳምንት፡አንደኛ ቀን

ትምህርት አራት፡-ማንበብ /የንባብ ስልቶች/

## የንባብ ስልቶች

ንባብ የመቀበያ ክሂል ነው፡፡ በመሆኑም የአንድን የንባብ መልዕክት ጸሐፊው (መልዕክት አስተላላፊው)ስራዬ ብሎ ማለት የፈለገውን እንዲልለት አመቻችቶ ይጽፈዋል፡፡ ጸሐፊው ማስተላለፍ የፈለገውን ጉዳይ ሊል ከፈለገበት ዓላማ አንጻር ሲጽፈው አንባቢው ደግሞ በሚያነብበው ነገር ላይ ካለው ጉዳይ ጥብቅነት ወይም አስፈላጊነት አኳያ ልብ ሰጥቶ ያነበዋል፡፡ ስለዚህ የንባብ ዓላማው የአነባበብ ስልቱን እንዴት ሊያመለክት እንደሚችል ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

### ሀ. የአሰሳ ንባብ (Scanning)

ስልቱም የሚፈለገው ጉዳይ እስኪገኝ ዓይንን ከግራ ወደ ቀኝ ከቀኝ ወደ ግራ በፍጥነት በማንቀሳቀስ፣ ገጾችን ገልበጥ ገልበጥ ከማድረግ ጋር ይያያዛል፡፡ የምንፈልገውን ስናገኝ ቆምና ረጋ ብለን እናነባለን፡፡ ተፈላጊው መረጃ ዓመተ ምህረት፣ ቀመር(ፎርሙላ)፣ የቦታ ወይም የድርጅት ስም፣

የስልክ ቁጥር፣ የትውልድ ቦታ፣ዕድሜ፣ የስራ ልምድ፣ አባባል፣ ተረት፣ በሰዎች መካከል የተደረገ ክርክር፣ የአንድ ነገር ፍቺ ትርጉም ትንታኔ ወዘተ. ሊሆን ይችላል፡፡

### ለ. የገረፍ ገረፍ ንባብ (skimming)

በገረፍታ የንባብ ስልት ዓይን በሚነበበው ጉዳይ ላይ በፍጥነት ከወዲያ ወዲህ ይንቀሳቀሳል፡፡ ዓላማው በሚነበበው ጉዳይ ውስጥ አንድ ጠቃሚ የሆነ ነገር አገኝበት ይሆን ብሎ ማንበብን ይመለከታል፡፡ ይህን ሃሳብ ወይም ዕውቅ ነገር አገኛለሁ ብለን ለመፈለግ ወይም የተወሰነ ፍሬ ነገር ለማግኘት ወቅታዊነት ያለው ትኩረት የሚስብ ቁም ነገር ባገኝበት ብለን ገልበጥ ገልበጥ በማድረግ የምናነብበው የንባብ ስልት ነው፡፡ ይህን ስልት ተጠቅመን የምናነባቸው እንደ ጋዜጣ፣ መጽሔት፣ የማስታወቂያ ሰሌዳ፣ የካርቱን መልዕክቶች ወዘተ. ናቸው፡፡

### ሐ. ጥልቅ የትኩረት ንባብ (intensive reading)

የትኩረት ንባብ በተለያዩ ስያሜዎች ሲጠራ ይስተዋላል፡፡ የጥናት ንባብ(study reading) እና የማስተዋል ንባብ ዋንኞቹ ናቸው፡፡ የትኩረት ንባብ ስልት በጥልቀት ዝግ ብሎ ወደፊትና ወደ ኋላ መለስ ቀለስ እያሉ በማብላላት ማንበብን ያመለክታል፡፡ የሚነበበው ጽሁፍ ምንም ያህል ቢበዛም ያነባበብ ስልቱ በዝግታ ነው፡፡ የምናነበውን ክፍል በትክክልና በምንጠብቀው መጠን መረዳታችንን እስክናረጋግጥ ድረስ መላልሰን እናነባለን፡፡ እየገመገምን፣ እያመዛዘንን፣ እያጣጣምን እንዲሁም የራሳችንን ሃሳብ እየጨመርን የምናስኬደው የንባብ ስልት የማስተዋል የንባብ ስልት ይባላል፡፡

### ሠ. ሰፊ ንባብ (Extensive Reading

ለጠቅላላ ዕውቀትና ለመዝናናት የሚተገበር የንባብ ስልት ነው፡፡ ዋና ዓላማው የንባብ ልምድ ለማዳበርና ለደስታ ነው፡፡በዚህ ስልት የሚነበቡት በአብዛኛው ረጃጅም ልቦለዶች፣ አጫጭር ልቦለዶች፣ በተለያዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች ስር የሚቀርቡ መጣጥፎች፣ በተለያዩ ድርጅቶች እየተዘጋጁ የሚወጡ አዝናኝ ጽሑፎች ናቸው፡፡

ከዚህ በታች የቀረበውን አጭር ምንባብ በፍጥነት አንብባችሁ ለቀረቡ ጥያቄዎች በጽሁፍ መልስ ስጡ፡፡

የገረፍ ገረፍ ንባብ

ማስታወቂያ

ቀን/11/11/2013 ዓ.ም

ቁጥር/ጋ/አ/ድ/05/215/13

ለስራ ፈላጊዎች የወጣ ማስታወቂያ

ድርጅታችን ጋርዱላ አስመጪና ላኪ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ባወጠው ክፍት የስራ ቦታ ውስጥ አንድ የገበያ ጥናት ባለሙያ አወዳድሮ መቅጠር ይፈልጋል፡፡ ለስራ መደቡ የሚስማሙ በገበያ ጥናትና ልማት ትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላችሁና መስፈረቱን የምታሟሉ ተወዳዳሪ አመልካቾች እስከ 18/05/2013 ዓ.ም በስራ ቀናት በመስሪያ ቤታችን የሰው ሐብት ቢሮ ቁጥር 3 ዋናውን የትምህርት ማስረጃ ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር በመያዝ በአካል ተገኝታችሁ እንድትመዘገቡ እያሳሰብን ድርጅታችን ሴቶችና አካል ጉዳተኞችን የሚያበረታታ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

## ማህተም

1. ማስታወቂያው የምን ማስታወቂያ ነው?
2. ስራ ፈላጊ ብትሆኑ ቶሎ ማወቅ የምትፈልጉት ምንድን ነው?
3. ድርጅቱ የሚያበረታታው ማንን ነው?
4. ይህን መረጃ በፍጥነት ለመረዳት ምን ዓይነት ስልት ተጠቀማችሁ?

ሁለተኛ ሳምንት፡ሁለተኛ ቀን

ትምህርት አምስት፡- የጥልቅ ንባብ ልምምድ

በዚህኛው የንባብ ጊዜ ለጥልቅ ንባብ የተዘጋጀውን ምንባብ አንብባችሁ ከታች ለተመለከቱት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥንቃቄ አንብቡና ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. ግሉኮስ ምን ዓይነት ስኳር ነው?
2. በዚህ ምንባብ ውሰጥ የተጠቀሰው ስኳር ከሻይ ስኳር በምን ይለያል?
3. ሰውነት ውስጥ ገብቶ ቶሎ ጥቅም የሚሰጠው የትኛው ስኳር ነው?

### ስኳር ወለድ ምግብ /ካርቦ ሀይድሬት/

ሃይል፣ ጉልበት ሰጪና ስኳር ወለድ ምግቦች ዋና ምንጫቸው ዕጽዋት ናቸው፡፡ ከእንስሳትም በመጠኑ ይገኛል፡፡ ስኳር ወለድ ምግብ በሁለት መልክ ይመደባል፤ አንደኛው ግሉኮስ/ ቀላል ስኳር ሲሆን ሁለተኛው ውስብስብ ስኳር /ስታርች/ ይባላል፡፡ ቀላል ስኳር ከፍራፍሬ፣ ከሸንኮራ ፣ከማርና ከወተት ይገኛል፡፡ ውስብስብ ስኳር ከእህል፣ ከስራስሮችና ከተለያዩ የእጽዋት ክፍሎች ይገኛል፡፡ ቀላል ስኳር ሰውነት ውስጥ ገብቶ ሐይል ለመስጠት ብዙ ጊዜ አይወስድም፡፡ ውስብስብ ስኳር ግን ሰውነታችን ወስጥ ገብቶ ወደ ቀላል ስኳር

ከተለወጠ በኋላ ድፍድፉ ወደ ጉበት ወስጥ ገብቶ ይከማችና በተፈለገ ጊዜ ደም ውስጥ ስኳር እንዳይበዛ ይቆጣጠራል፡፡

ምንጭ፡ ምግብ መድሐኒቴ፣ ከበንቲ ቀኖ፣ገጽ 9፣ 2007 ዓ.ም

ሁለተኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ስድስት፡- የጽሕፈት ደረጃዎች /የጽሑፍ ሂደት /

የአጻጻፍ ሂደት

1. የአጻጻፍ ሂደት ምንድን ነው? የአጻጻፍ ሂደት ማለት በጽሐፍ ወቅት የምንከተለው የጽሕፈት ሂደት ማለት ነው፡፡ ማንኛውም ጽሁፍ በማንኛውም ርዕስ ይጻፍ፣ ፅሁፍ በእለት ከዕለት ተግባቦት ውስጥ እንደ ንግግር ተነግሮ የሚያበቃ ሣይሆን ጸሐፊው በየጊዜው እየመላለሰ ያርመዋል፤ ያስተካክለዋል፡፡ በማረምም ይሁን በመፃፍ ሂደት ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች በበለጠ መልኩ እየደጋገመ ስለሚጽፈው፣ቀድሞ ስለጻፈውና ሲፅፍ ስለተሣሣተው በአንድ ጊዜ የሚያስብበት ሂደት ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ከስነ ልሣንና ከስነ ፅሁፍ እውቀቶች ጋር ተያይዘው የሚመጡ የቋንቋ ህግና ሥርዓት በቅደም ተከትል መፃፍ /ዓ.ነገርን በትክክል ማዋቀር/፣ ከሚጽፈው ርዕስ ጋር ተስማሚ የሚሆኑ ቃላትን መምረጥ/ ማራኪና ትክክለኛ ሀሣብን ለታዲሚ በታለመት መሠረት ማድረስ መቻልን ይጠይቃል፡፡

1.1 ርዕስ መምረጥ፡- ርዕስ በድርሰት ውስጥ የሚቀርበውን ሀሣብ ማሣየት አለበት፡፡ ርዕስ ማጥበብ በድርሰቱ የሚተለለፈውን መልእክት፣ የሚጻፈውን ይዘት፣ የአንባቢውን ማንነትና የጭብጥን ጠቀሜታ ከግምት ስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡
1.2 ልንፅፍበት በፈለግነው ርዕሰ ዙሪያ የተለያዩ መረጃዎችን ከራሣችንም ሆነ ከሌልች የመረጃ ምንጮች የሰበሰብነው መረጃ ሁሉ በድርሰታችን ውስጥ መካተት ላይኖርበት ይችላል፡፡
1.3 የምንፅፍበትን አላማ ማወቅ፡- የምንሰበስበው መረጃ አላማችንን የሚያሣካ፣የምንመርጠው የአደረጃጀት ስልት ያን አላማ ከግብ የሚያደርስ ወዘተ. ይሆናል፡፡
1.4 አንባቢን ማወቅ፡- ሲባል ድርሰታችንን የሚያነበውን ሰው ፍላጐቱን፣ እምነቱን፣ አቋሙን፣ ባህሉን፣ የትምህርት ደረጃውን፣ እድሜውን፣ ጾታውን ወዘተ. መለየት መቻል ነው፡፡

1.5 ቢጋር መንደፍ፡- ቢጋር የምንፅፍበትን መንገድ ግልጽ አድርጐ ማሳያ "ኮምፓስ" ነው፡፡ ስለዚህ ድርሰት ከመፃፋችን በፊት የጠበበውን ርዕስ መሠረት በማድረግ ንድፍ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

1.6 ማርቀቅ/መፃፍ፡- በግርድፍ የሚፃፍ የመጀመሪያው የጽሕፈት ጊዜ ተግባር ነው፡፡ ተግባሩም በቅድመ ፅህፈት የሰበሰብናቸውን መረጃዎች በአረፍተ ነገር መልክ የምናቀናብርበት ነው፡፡ ፅሁፍ /ድርሰቱ/ የተዋጣለት ይሆን ዘንድ ዓ.ነገር በአግባቡ ማዋቀር፣ ዓ.ነገርን አቀናጅቶ አንቀጽ መመስረት፣ አንቀጽን አደራጅቶ ሙሉ ድርሰት መፃፍን ይመለከታል ፡፡

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የጽህፈት ሂደት መመሪያዎችን ካነበባችሁ በኋላ በተከታዩ ክፍለ ጊዜ ሰርታችሁ የምታመጡት አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

ጽህፈትን ስታስቡ የሚከተሉትን ሂደቶች አትርሱ፡፡

1. ርእስ ምረጡ፤
2. መረጃ ሰብስቡ፣
3. ለምን አላማ መጻፍ እንደፈለጋችሁ እወቁ፣
4. ለማን እንደምትጽፉ አስቡ ፣
5. ቢጋር ንደፉ፣
6. አርቅቁ/ጻፉ፡፡

የምዕራፉ ማበልጸጊያ ጥያቄዎች

1. የንባብ ስልቶች የሚባሉት ምን ምን ናቸው?
2. ጽሁፍ ለመጻፍ ስንዘጋጅ የምንከተለውን ሂደት ዘርዝሩ፡፡

## ምእራፍ ዘጠኝ

## ዓባይ

**የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ ፡-

- ተራኪ ጽሁፍ አዳምጣችሁ ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ፡፡
- በተሰጣችሁ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ንግግር ታደርጋላችሁ፡፡
- አያያዦችን ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡
- የምቱን ስልት ተከትላችሁ ግጥም ታነባላችሁ፡፡
- ግጥምን አንብባችሁ መልዕክቱን በዝርው ትገልጻላችሁ፡፡

አንደኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን

ትምህርት አንድ፡- ማዳመጥ

ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ተግባር አንድ ፡ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቃላት ፍች ገምቱ

ግምጃ ቤት፣ ዕደ ጥበብ ፣ ጎልማሳ፣ አሉባልታ፣ መናኛ

ተግባር ሁለት፡ የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

አራቱ ወጣቶች በምን ዓይነት ስሜት ውስጥ ይገኛሉ?

ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ተግባር ሶስት፡ የሚከተሉት ጥያቄዎች "የብርሃን ልጆች" በሚል ርዕስ ካዳመጣችሁት ታሪክ የወጡ ናቸው፡፡ ለጥያቄዎቹም "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት በቃል ምላሽ ስጡ፡፡

1. በእርጋታ የተቀመጠው ጎልማ ጭንቅላቱን በኮፊያ ሸፍኗል፡፡
2. ተራራን በዶማ የሚንደው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው፡፡
3. ኒውክሌር ያብላላ የተባለው የደቡብ ኮሪያ ሕዝብ ነው፡፡
4. በግብራቸው ይታወቃሉ ያለው ብዙ ግብር ይከፍላሉ ለማለት ነው፡፡
5. የብርሃን ልጆች ልበ ሙሉ ጀግኖች ስለሆኑ ተጻራሪ ቢጮህ አይደነብሩም፡፡

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ታሪክ መሰረት በቃላችሁ መልስ ስጡ፡፡

1. ሲከራከሩ የነበሩት ወጣቶች ስንት ናቸው?
2. ሊነጋ ሲል ምን ይሆናል?
3. የብርሃን ልጆች የተባሉት እነማን ናቸው?
4. ሕዝቡ ለምን ቃተተ?
5. የብርሃን ልጆች ሀይማኖታቸው ምንድን ነው? ሐረጋቸውስ?

አንደኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ሁለት - መናገር

ተግባር አንድ፡ የሚከተለውን ጽሁፍ አንብቡ፡፡

የብርጭቆ ውሃ

አንድ መምህር ሊያስተምር ወደ ክፍል ሲገባ በውሃ የተሞላ ብርጭቆ በመዳፉ ላይ አስቀምጦ፣ "ይህ ውሃ ክብደቱ ምን ያህል የሚሆን ይመስላችኋል?" ሲል ተማሪዎቹን ጠየቀ፡፡ ከፊሉ መቶ ግራም ፣ ሌላው ሁለት መቶ ሀምሳ ፣ ሌሎችም አምስት መቶ ግራም ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጡ፡፡ ውሃ የያዘውን ብርጭቆ መዳፉ ላይ እንዳስቀመጠ ፣ እጁን ዘርግቶ "ይህን ውሃ የያዘ ብርጭቆ ለአንዲት ደቂቃ ያህል በእጄ ይዤ ብቆይ ምን እሆናለሁ?" ብሎ ጠየቃቸው፡፡ ከተማሪዎቹ አንዱ ፣ "ጥቂት ድካም ይሰማሀል፣" ሲል መለሰለት፡፡ "ለአንድ ሰዓት ይዤው ብቆይስ?" የሚለውን ጥያቄ አስከተለ፡፡ ሌላው ተማሪም፣ "እጅህን ይደክምሀል፣ ህመም ሳይሰማህ አይቀርም፤" ሲል መለሰለት፡፡ "እሺ ለአንድ ቀን ያህል ይዤው ብውልስ?" አለ፡፡ "ያኔማ እጅህ መንቀጥቀጥ ይጀምራል፤" ስትል አንዲት ተማሪ መልስ ሰጠች፡፡

መምህሩ "ለአንድ ሳምንት ያህል ይዤው ብሰነብትስ?" የሚል ሌላ ጥያቄ አነሳ፡፡ " እጅህ ይገነጠላል፣ ስቃዩም ለሌላው ሰውነትህ ይተርፋል፤" ሲሉ መለሱለት፡፡ በመጨረሻም መምህሩ፣ "የዚህ ህመም መነሻው ምንድን ነው?" አለ አንዳንዶች፣ "የውሃው ክብደት ነው" ሌሎችም ፣ "አያያዝ ነው"፤ የሚል መልስ ሰጡ፡፡ መምህሩም፣ ውሃው አምስት መቶ ግራም እንኳን አይሞላም፤እንዴት የህመሙ መነሻ ይሆናል?" ሲል የምርምር ሀሳብ አነሳ፡፡ አንዲት ጎበዝ ተማሪም፣ "ህመሙ እና ድካሙ ቀላሉን ውሃ ለረጅም ጊዜ ይዞ በመቆየቱ እንጂ በውሃው ክብደት ምክንያት የመጣ አይደለም፤" ስትል መምህሩን ያስደሰተ ምላሽ ሰጠች፡፡

"ታዲያ መፍትሄው ምንድነው?" ሲል መምህሩ ጥያቄውን ሰነዘረ፡፡ ተማሪዎቹ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ሲያስቡ ቆዩና፣ "ብርጭቆውን ገልብጦ ውሃውን መድፋት ያስፈልጋል፤ አለበለዚያ ችግሩ እየተባባሰ ይሄዳል፤" የሚለው ድምዳሜ ላይ ደረሱ፡፡

ነገር ስትጀመር ቀላል ናት፡፡ ክብሪት ስትለኮስ ቅንጣት ናት፡፡ ይዘው ለብዙ ጊዜ ለሚቆዩ ሰዎች ግን እስከ ማሳበድ ትደርሳለች፡፡ እንደ ዋዛ የተጀመረች

መለያየት፣ መኮራረፍ፣ አለመግባባት ፣ አለመደማመጥ ለብዙ ጊዜ ተይዛ በመቆየቷ ያመጣችውን ህመም የደረሰበት ብቻ ያውቃል፡፡

ምንጭ፡ የሁለት ሀውልቶች ወግ እና ሌሎች፣

ዳንኤል ክብረት፣ 2003 ዓ/ም

ተግባር ሁለት፡ ያነባባችሁትን ጽሑፍ ፡-

ሀ. በግል አሰላስሉ፡፡

ለ. አምስት ሆናችሁ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡

ሐ. በቡድን መሪያችሁ አማካኝነት ለመምህራችሁ ግለጹ፡፡

1. እንደ ዋዛ የተጀመረች መለያየት፣ መኮራረፍ፣ አለመግባባትና አለመደማመጥ ለብዙ ጊዜ ተይዛ በመቆየቷ ያመጣችውን ህመም የደረሰበት ብቻ ያውቃል፡፡ ሲል ምን ማለቱ ነው?
2. በጽሁፉ እንዲተላለፍ የተፈለገው መልዕክት ምንድን ነው?

አንደኛ ሳምንት፤ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ሶስት - መጻፍ

<u>የሚከተሉት አያያዥ ቃላትን በመጠቀም የተመሰረቱ ዓ.ነገሮች በትምህርት ሁለት ከተማራችሁት ጽሁፍ ውስጥ የተወሰዱ ናቸው፡፡ በማስተዋል አንብቧቸው፡፡</u>

1. አንድ መምህር ሊያስተምር <u>ወደ</u> ክፍል ገባ፡፡
2. ህመሙ <u>እና</u> ድካሙ የመጣው ቀላሉን ውሃ ለረጅም ጊዜ ይዞ በመቆየቱ <u>እንጂ</u> በውሃው ክብደት ምክንያት አይደለም፤”
3. ውሃውን መድፋት ያስፈልጋል፤ <u>አለበለዚያ</u> ችግሩ እየተባባሰ ይሄዳል፡፡
4. <u>እንደ</u> ዋዛ የተጀመረች መለያየት፣ለብዙ ጊዜ ተይዛ በመቆየቷ ያመጣችውን ህመም የደረሰበት ብቻ ያውቃል፡፡

ቀደም ሲል  በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው (ወደ፣እና፣ እንዲ፣አለበለዚያ) አያያዥ ቃላት ናቸው፡፡ ቀጥሎ የቀረቡትን አያያዦች ተጠቅማችሁ ዓ.ነገሮቹን አሟሉ፡፡

| |
|---|
| እንደ፣ነገር ግን፣ ስለዚህ፣ ስለ፣ አለበለዚያ፣ |

ሀ. አልማዝ ---------------- እናቷ ቆንጆ ናት፡፡

ለ. ገበያ ሄጄ ነበር --------------- የሚያስፈልገኝን አሟልቼ አልገዛሁም፡፡

ሐ. ወንድሜ ደክሞታል ------------------ ስራ ማገዝ አለብኝ፡፡

መ. ምግብ -------------------- በላሁ ጠግብያለሁ፡፡

ሠ. መድሃኒትህን ሳታቋርጥ ጨርሰህ ዋጥ፤ ----------- በሽታው ያገረሽብሀል፡፡

ረ. በትምህርቷ ውጤታማ ---------------- ሆነች ደስ ብሏታል፡፡

ሰ. ፈተና ደርሷል፤ ------------- ማጥናት አለብኝ፡፡

ሸ. እናቴ እግሯን ----------- አጠብኩ መረቀችኝ፡፡

ቀ. ጎመን ------------- ተከልኩ ዝናብ ዘነበ፡፡

በ. እንቅልፌ መጥቷል --------- የቤት ስራዬን ሰርቼ አልጨረስኩም፡፡

ሁለተኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን

ትምህርት አራት፡- መጻፍ

የሚከተሉትን አያያዦች በመጠቀም አረፍተ ነገሮች መስርቱ፡፡

| |
|---|
| እንደ፣ ስለዚህ፣ ነገር ግን፣ አለበለዚያ፣ ቢሆንም |

1. ________________________________________________

2. ________________________________________________

3. ________________________________________________

4. ________________________________________________

5. ________________________________________________

ሁለተኛ ሳምንት፡ ሁለተኛ ቀን

ትምህርት አምስት፡- ግጥም

<u>የሚከተለውን ግጥም መምህራችሁ ሲያነቡ ካዳመጣችሁ በኋላ የምቱን ስልት ተከትላችሁ ድምጻችሁን ከፍ በማድረግ አንብቡ፡፡</u>

አባይ

አባይ ነዳጅ ይሁን

መመኘቴ ለምን

ውሃም ሆኖ ይኑር

እንዲለማ ምድር፡፡

እንደ ፍላጎቱ

አይፍሰስ በከንቱ

ግድብ ሆኖም ይኑር

በኃይል እንዲቀየር፡፡

በግድቡ ሙላት

አሳ እንዲረባበት

በከበረው መሬት

እንዲትረፈረፍ ምርት፡፡

ውሃ ይሁን እንጂ

ለምን ነዳጅ ይሁን

ነዳጅ ምንም እንኳን

ቢበልጠውም ውሃን

ምንድን ነው ውሃውን

በትልቅ ገድበን

ምርት ያገኘነውን

በዶላር መንዝረን፡፡

አባይ ነዳጅ ይሁን

ድሮ እኔ ያልኩትን

ሀሳቤን ቀይሬ

ለውጫለሁ ዛሬ፡፡

ደግሞም ስንረዳው

በወግ ስናጤነው

ከሁሉ ላቅ ያለው

ትርፍ ማለት ይሄ ነው፡፡

ምንጭ፡ በይልቃል ተስፋው፣ እብድ ነኝ ፣ገጽ 111 የተወሰደ፡፡

ሀለተኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ስድስት፡- ግጥም

የሚከተሉት ጥያቄዎች አባይ በተሰኘው ግጥም ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ናቸው፡፡ ጥያቄዎቹን አንብባችሁ ምላሽ ስጡ፡፡

1. የግጥሙ መልዕክት ምንድን ነው? በቡድን ተወያዩበት፡፡
2. የግጥሙን መልዕክት በዝርው ጽሁፍ ግለፁ፡፡

ሦስተኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን

ትምህርት ሰባት፡- ግጥም

የሚከተለውን ግጥም መምህራችሁ ሲያነቡ ካዳመጣችሁ በኋላ የምቱን ስልት ተከትላችሁ መምህራችሁ በሚያዟችሁ መሰረት አንጓዎችን በመከፋፈል ጮክ ብላችሁ አንብቡ፡፡

ተባበር

በአንድነት ተባበር ተው አትለያይ

ድር አንበሳ ያስራል ሲሆን አንድ ላይ፡፡

ከመሐከል ይጥፋ ተንኮል መካሪው

ቸርነት ቅንነት ነው አሸናፊው

ከአይምሮህ ውስጥ ይውጣ ይሰረዝ ቅናት

እንዲሁም ወንድሙ ያ መጥፎ ትዕቢት

እነሱ ያሉ እንደሁ አይሰራም ቤት

አገርም አንድ አይሆን ይገባል ጠላት

ትልቁ ትንሹ ሲሆን አንድ ላይ

ሁሉ እኩል ይሆናል ሳይኖር የበላይ፡፡

ድር ሲያብር አንበሳ በመተባበር

የሰው ልጅ አንድነት ይጠቅማል ላገር፡፡

ምሳሌው ልክ ነው ለሰው ልጅ ተስማሚ

በህሊናህ ጻፈው አድርገው ቀዋሚ፡፡

ጠላትን ሲያጠቁ ሁሉም በህብረት

ደስታ ይገባል በያንዳንዱ ቤት

እንዲሁም ይጠፋል የስንፈት ቅናት፡፡

ባንድነት ተማክሮ ተባብሮ ቢሰሩ

ክፉው ደግ ይሆናል ጠፍቶ መቃቃሩ

ከትብብር ሜዳ የሮጠ ጎበዝ

ቀዳሚ ይሆናል ሁሉን በማፍዘዝ፡፡

ጥናትም ቢያጠኑ በመተባበር

ተሰውሮ አይቀርም ረቂቅ ሚስጥር፡፡

ህብረት ደመና ነው ያወርዳል ዝናም

የደረቀ ሁሉ እንዲለመልም፡፡

ህብረት ብርሃን ነው የፀሐይ ጨረር

ህብረት ጥሩ ነገር በመከባበር

አያጋጥምህም እንቅፋት ከእግር፡፡

ህበረት ጎዳና ነው የመጣ ከጥንት

ትልቁ ትንሹ የሚጓዝበት

ደግሞም የሮጠ ሰው የሚቀድመበት

ለህብረት ምሳሌ አይገኝለት

እንዲያው ዝም ብሎ ማለት ነው ህብረት

ተባበር ተባበር ተባበር በእውነት

ኢትዮጰያ ትራመድ ስንፍና ይራቃት፡፡

(ከዶ/ር ኢሳያስ አለሜ፤ ከቀድሞ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የተወሰደ)

ሦስተኛ ሳምንት፤ሁለተኛ ቀን

ትምህርት ስምንት - ግጥምን አንብቦ መረዳት

“ተባበር ” የተሰኘውን ግጥም ካነበባችሁ በኂላ ለሚከተለው ጥያቄ በቃል ምላሽ ስጡ፡፡

ግጥሙ የሚያስተላልፈው መልዕክት ምንድነው?

ሶስተኛ ሣምንት፡ ሶስተኛ ቀን

ትምህርት ዘጠኝ ፣ ክለሳ

ተግባር፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በጽሁፍ መልስ ስጡ፡፡

የምእራፉ ማበልጸጊያ ጥያቄዎች

1. በሚከተሉት አያያዥ ቃላት አረፍተ ነገር መስርቱ

ሀ/ አለበለዚያ ለ/ ስለዚህ ሐ/ ነገር ግን

2. የሚከተለውን ግጥም አንብባችሁ መልእክቱን በዝርው ግለጹ

ባንድነት ተባበር ተው አትለያይ፤
ድር አንበሳ ያስራል ሲሆን አንድ ላይ፡፡
ከመሀከል ይጥፋ ተንኮል መካሪው፤
ቸርነት ቅንነት ነው አሸናፊው፡፡

## ምእራፍ አስር

## ርእስ፡- ሀብታሙ ሰው

የሚጠበቁ ብቃቶች

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- የጓደኞቻችሁን ሀሳብ ታዳምጣላችሁ፡፡
- ሚና በመውሰድ ጭውውት ታደርጋላችሁ፡፡
- በተለያዩ ሀሳቦች ላይ ትከራከራላችሁ፡፡
- ተረቶችን በትረካዊ ዘዴ ታቀርባላችሁ፡፡
- የምሳሌያዊ አነጋገሮችን መልዕክት ታስረዳላችሁ፡፡

**አንደኛ ሳምንት ፡አንደኛ ቀን**

**ትምህርት አንድ ፡ ማዳመጥ**

**ቅድመ ማዳመጥ**

**ተግባር አንድ፡**

ለጓደኞቻችሁ በሆነ አጋጣሚ የደረሰባችሁን ችግር ተናግራችሁ ታውቃላችሁ? እስኪ ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተነጋገሩ፡፡

**ተግባር ሁለት፡**

መዘዙ በሚል ርእስ የቀረበ የአንድ ወጣት ገጠመኝን መነሻ በማድረግ በጓደኛሞች መካከል የተፈጠረ አንድ ታሪክ መምህራችሁ ያነቡላችኋል፡፡ ይህን ታሪክ መምህራችሁ ሲያነቡ በጥንቃቄ አዳምጡ፡፡

**የማዳመጥ ጊዜ፡**

እስከ አሁን ከሰማችሁት ታሪክ ምን ተረዳችሁ፤ቀጥሎ ምን የሚፈጠር ይመስላችኋል?

**ድኅረ ማዳመጥ**

**ተግባር ሶስት፡**

ስላዳመጣችሁት ዋና ሃሳብ ማስታወሻ ያዙና፤ ሃሳቡን መልሳችሁ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡ ከሰማችሁት ገጠመኝ ምን ተማራችሁ?

**አንደኛ ሳምንት፤ሁለተኛ ቀን**

**ትምህርት ሁለት ፡ መናገር(ክርክር)**

<u>በሚከተለው ታሪክ መነሻነት ለክርክር አንድ ሃሳብ ቀርቧል ፡፡ የቀረበውን ሃሳብ ወስዳችሁ ተከራከሩ፡፡</u>

ገና ወጣት ነኝ 17 አመቴ ነው ፡፡ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ የቤታችን ችግር ገፍቶ የእናቴን የሳንባ በሽታ ሕመም አባብሶ ለሞት ሲያበቃት የድህነታችን ዋና መግቢያ በር ተበርግዶ ተከፈተ፡፡ የእናቴ ሃላፊነት በኔ ትከሻ ላይ ወደቀ፡፡ችግር የቤታችንን ጓዳ ሰርስሮ ገባ ፡፡ ጉድለት አቅማችንን ፈተነው፡፡ የሚረዳን ፈጣሪ ጓዳችንን በበረከት እንዲሞላው ተመኘን፡፡ ያን ስንጠብቅ ጊዜው ፋታ ነሳን ፡፡ የጎደለውን ለመሙላት የሚሻ ሰው ድንገት ብቅ አለ ፡፡ በቅን አስተሳሰብ ቤተሰባችንን የቀረበው ጎልማሳ ልገሳውን አበረከተ፡፡ ለጊዜውም

ቢሆን የችግራችን ቀዳዳ ተደፈነ፡፡ ያኔ ነበር የዚህ ሰው ቅን መሆን አባቴን አንዲት ሴት ልጁን አሳልፎ እንዲሰጥ ያስወሰነው፡፡ የቤት ሃላፊነት በአባቴ ላይ ሲወድቅ ማየት ስላላስቻለኝ ሽክሙን በመሸከም ልካፈለው ወሰንኩ፡፡

የአባቴን ውሳኔ ልቀበል ካልኩ ሁለት ሽክም መሸከም ሊሆንብኝ ነው፡፡ ሶስተኛው ደግሞ ትምህርቴን መቀጠል የማልችልበት ትዳር የሚያመጣው ተጨማሪ ጫናም አሳሳቢ ሆነብኝ ፡፡ አባቴ ያለችው ትንሽ የወር ገቢ ማነስና የቤተሰባችን ዕጣ ፋንታ ስላሳሰበው የተጠየቀውን የትዳር ጥያቄ በአዎንታ መመለሱን ባልወደውም፣ ከትእዛዙ ማፈንገጥ አልሆነልኝም ፡፡ የአባቴን ትእዛዝ መተው ማሳዘን ፣ትምህርቴን ማቋረጥ ደግሞ ህይወቴን ማጨለም ሆኖ ታየኝ፡፡ እናንተ ብትሆኑ ምን ትመክሩኛላችሁ?

ተግባር

| |
|---|
| ይህን ታሪክ ካነበባችሁ በኋላ እናንተ በልጅቷ ቦታ ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር? ከሁለቱ ሃሳብ አንዱን መርጣችሁ ምክር ለግሱ ብትባሉ፤ ለማሳመን የትኛውን በመደገፍ ትከራከራላችሁ፡፡ መምህራችሁ በሚያደራጇችሁ ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተከራከሩ፡፡<br>• ታግባ ?<br>• አታግባ? |

በዚህ ክፍለ ጊዜ በቡድናችሁ ውስጥ ለሁለት ተከፍላችሁ ተከራከሩ፡፡

**አንደኛ ሳምንት፤ሶስተኛ ቀን**

**ትምህርት ሶስት፤ክርክር**

በትምህርት ሁለት ላይ በተነሳው ሃሳብ ከየቡድኑ የተመረጣችሁ ተወካዮች በሁለት በመከፈል ተከራከሩ፡፡

**ሁለተኛ ሳምንት፡አንደኛ ቀን**

**ትምህርት አራት፡ የሚና ጨዋታ/ዳኝነት/**

- የኮንትሮባንድና የአደንዛዥ እጽ የሚል ርእስ ወስዳችሁ የኮንትሮባንድ ነጋዴ፣የፖሊስ፣የፈታሽ ፣የዳኛ ሚና ተጫወቱ፡፡
- ሚና የሚወስደውን ተማሪ ምን ላይ መዘጋጀት እንዳለበት ተነጋገሩ፡፡
- በቡድናችሁ ጭውውት ለማቅረብ ተዘጋጁ ፡፡
- የእያንዳንዱ ቡድን አባል ሚናን በእጣ ተከፋፈሉ፡፡

**ሁለተኛ ሳምንት ፤ሁለተኛ ቀን**

**ትምህርት አምስት፤ ሚና ተከፋፍሎ ጭውውት ማቅረብ**

በትምህርት አራት ላይ የተሰጣችሁን እና የተዘጋጃችሁበትን ሚና በተማሪዎች ፊት ወጥታችሁ ተጫወቱ፡፡

**ሁለተኛ ሳምንት፤ሶስተኛ ቀን**

**ትምህርት ስድስት ፤ተረት ማውራት**

**ቀጥሎ የቀረበውን ተረት መምህራችሁ ያነቡላችኋል፤እናንተ በጥንቃቄ አዳምጡ፡፡**

**ሀብታሙ ሰው**

በጥንት ዘመን በአንድ አገር በመንደሩ የተከበረ፤ ለተቸገረ የሚሰጥ፣ለተራብ የሚያበላ አንድ ሀብታም ሰው ነበረ፡፡ በዚህ ደግ ጸባዩ ጎረቤቶቹ ደስ የሚሰኙ በመሆናቸው፤ የሚላቸውን ሁሉ ለመፈጸም ወደ ኋላ የሚሉ አይደሉም፡፡አንድ ቀን ዘመዶቹን ሊጠየቅ ወደ እሩቅ አገር ሄዶ ሳለ ‹‹ከሰው መርጦ ለሹመት ከእንጨት መርጦ ለታቦት›› እንደሚባለው የሚያምነውን አንድ ሰው ቤቱን እንዲጠብቅለት አደራ ሰጥቶ ሄደ፡፡

‹‹ወርቅ ላበደረ ጠጠር ጤፍ ላበደረ አፈር›› እንደሚባለው ይህ ሰው እምነቱን አጉድሎ የሀብታሙን መኝታ ቤት ገንጥሎ ገባና ንብረቱን የቻለውን ያህል ዘርፎት ተሰወረ፡፡ አገር ሰላም ብሎ ወደ ቤቱ ሲመለስ ‹‹ ያልጠረጠረ ተመነጠረ ›› ነውና በሚያምነው ሰው መዘረፉን ተረዳ፡፡ ጎረቤቶች እንኳን በሰላም መጣህ ሊሉ ወደ ቤቱ ሲገቡ አዝኖና ተክዞ መቀመጡን አይተው ሲጠይቁት የሆነውን ሁሉ አጫወታቸው፡፡ በዚህ ክፉ ተግባር የተበሳጩት ጎረቤቶች ይህን ዘራፊ ካለበት ፈልገው ይዘውት መጡና፤ ለፍርድ አቀረቡት፡፡

ዳኛው ተጠርጣሪውን ሰው ‹‹ለመሆኑ ሰርቀሀል?›› ብለው ሲጠይቁት አመነ፡፡ ዳኛው በል አሁን ‹‹ንብረቱን መልስ፤ ብለው ሲጠይቁት›› ሸጦ እንደበላባት

መለሰላቸው፡፡ ‹‹ፍርድ አያወቅ ዳኛ ተገን አያውቅ እረኛ›› አይነት ነበሩና ፍርዱን ገልብጠው ‹‹ታዲያ ከሸጠው ከየት ያመጣል? ሲያዩት ደህ ይመስላል፡፡›› ብለው ሀበታሙን ሰው ‹‹ ምን ያግሳ ውሃ ምን ይከፍል ደሃ›› ሲባል አልሰማህም፡፡ ጥፋቱ ጥፋት ቢሆንም ወደፊት ሰርቶ ይከፍልሀል፡፡ብለው በነጻ አሰናበቱት፡፡

‹‹ሰዶ ማሳደድ ቢያምርህ ዶሮህን በቆቅ ለውጥ›› የሚለውን ምሳሌ አስታውሶ የዚህ ሁሉ ድካም መንስኤ ቤቱን ጥሎ መሄዱ መሆኑን አሰበና ራሱን እያጽናና ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡ ‹‹ደባ ራሱን ስለት ድጉሱን ይጎዳል›› እንደተባለው ያ ወንጀለኛ ነጻ ቢሆንም በሰፈሩ የማይታመን በመሆኑ ቢታመም ጠያቂ ቢርበው አጉራሽ አጥቶ አገር ጥሎ ጠፋ ፡፡

ምንጭ፡-ሆህተ ጥበብ ዘስነ ጽሁፍ፣ በተ/ማሪያም ፋንታዬ፣ 1955፣ አርቲስቲክ ማተሚያ፡፡

## ሀ. በ «ሀ» ክፍል የተመለከቱትን ተረትና ምሳሌዎች ከ «ለ» ከፍል የሚስማማቸውን በቡድን በመወያየት መርጣችሁ አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ከሰው መርጦ ለሹመት ከእንጨት መርጦ ለታቦት | ሀ/ የክፋት ዋጋ |
| 2. ያልጠረጠረ ተመነጠረ | ለ/ ምንም የሌለው |
| 3. ፍርድ አያወቅ ዳኛ፣ ተገን አያውቅ እረኛ | ሐ/ ከንቱ ልፋት |
| 4. ምን ያግሳ ውሃ፣ ምን ይከፍል ደሃ | መ/ፍርድ ማዛባት |
| 5. ሰዶ ማሳደድ ቢያምርህ ዶሮህን በቆቅ ለውጥ | ሠ/ጥንቃቄን አትርሳ |
| 6. ደባ ራሱን ስለት ድጉሱን ይጎዳል | ረ/ ተመራጭ |

ለ/ ተረቱ ምን ያስተምረናል?

2/ ጥሩ መልእክት የሚያስተላልፉ ተረቶችን ሰብስባችሁ ለቡድናችሁ አባላት ንገሯቸው፡፡

**ሶስተኛ ሳምንት ፡አንደኛ ቀን**

**ትምህርት ሰባት፡ ተረት ማውራት**

የሰበሰባችሁትን ተረት በየቡድናችሁ በየተራ አቅርቡ፡፡

**ሶስተኛ ሳምንት፡ ሁለተኛ ቀን**

**ትምህርት ስምንት፡ የምሳሌያዊ አነጋገርን መልዕክት ማስረዳት**

<u>ማስታወሻ</u>

ምሳሌያዊ አነጋገሮች፡-

- በአጭር የተገለጹ ጥልቅ ሀሳቦችን የያዙ ዘይቤያዊ አባባሎች ናቸው፡፡
- የያዟቸው ሀሳቦች ከህብረተሰቡ የእለት ተእለት ገጠመኝ በምልከታ የተገኙ ናቸው፡፡
- ሀቅነታቸው በማህበረሰቡ የተረጋገጠላቸው ሀሳብ መግለጫዎች ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- ውሽታምና ስንቅ እያደር ይቀላል፡፡

ውሽታም ውሽቱ ሲጋለጥ ክብር ያጣል፤ ስንቅም እየተበላ ሲቆይ ክብደቱ ይቀንሳል፡፡

ተግባር

1/ በሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ላይ በጋራ ተወያይታችሁ አባባሎቹን አስረዱ፡፡

1. ተልባ ቢንጫጫ በአንድ ሙቀጫ
2. ውሎ ውሎ ከቤት ኑሮ ኑሮ ከመሬት
3. ከሞኝ ደጅ ሞፈር ይቆረጣል

2/ ሶስት ሶስት ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ጠይቃችሁ አባባሎቹን አብረርታችሁ አቅርቡ፡፡

**ሶስተኛ ሳምንት፡ ሶስተኛ ቀን**

**ትምህርት ዘጠኝ ፡ ምሳሌያዊ አነጋገርን ሰብስቦ ለውይይት ማቅረብ**

ሰብስባችሁ ያመጣችሁትን ምሳሌያዊ አነጋገር ለቡድን ጓደኞቻችሁ አቅርቡና የተነገሩበትን ሁኔታ አስረዱ፡፡ ሁሉም የቡድኑ አባላት ይሳተፉ፡፡

## አራተኛ ሳምንት፡ አንደኛ ቀን

## ትምህርት አስር ፡ ምሳሌያዊ አነጋገርን ሰብስቦ ለውይይት ማቅረብ

ሰብስባችሁ ያመጣችኋቸውን ምሳሌያዊ ንግግሮች ተመሳስሏቸውን እና ልዩነታቸው መሰረት በማድረግ ከለያችኋቸው በኋላ በቡድን ተወካያችሁ አማካይነት ለሌሎች ተማሪዎች አጋሩ፡፡

## ዋቢ መጻህፍት

ሺበሺ ለማ፡፡ 1995 ዓ.ም፡፡ አርአያዎች፡፡ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፤ አዲስ አበባ፤ኢትዮጵያ፡፡

በንቲ ቀኖ፡፡ 2007 ዓ.ም፡፡ (6ኛ ዕትም)፣ ምግብ መድሐኒቴ(ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ)፡፡

ባየ ይማም፡፡ 1987፡፡ የአማርኛ ሰዋስው፡፡ የት.መ.ማ.ማ.ድ.፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፡፡

ተክለ ማሪያም ፋንታዬ፡፡ 1955 ዓ.ም፡፡ ሆህተ ጥበብ ዘስነ ጽሁፍ ፡፡አርቲስቲክ

ማተሚያ፤አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፡፡

አብይ አህመድ (ዶ/ር)፡፡ 2012 ዓ/ም፡፡ መደመር (ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ)፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡ 1993 ዓ.ም፡፡ አማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አርትስቲክ ማተሚያ ድርጅት፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፡፡

ኬኬ(ዶ/ር)፡፡ 2008 ዓ.ም፡፡ ጥቁር አዝሙድ የህይወት ቅመም፡፡ አልፋ ማተሚያ ቤት፤አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፡፡

ዓለማየሁ ዋሴ(ዶ/ር)፡፡ 2010 ዓ.ም፡፡ መርበብት፡፡ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ. የግ.ማህበር፤አዲስ አበባ፤ኢትዮጵያ፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ 1992 ዓ/ም፡፡ የስነ ጽሁፍ መሰረታዊያን ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ዳንኤል ክብረት፡፡ 2003 ዓ/ም፡፡ የሁለት ሀውልቶች ወግ እና ሌሎች፡፡

የሻው ተሰማ፡፡ 1996፡፡ ልሳነ ብዕር ከመ ልሳነ ሰብእ፡፡ ብራና ማተሚያ ድርጅት፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፡፡

ይልቃል ተስፋው፡፡ 2007 ዓ.ም፡፡ እኔማ እብድ ነኝ፡፡ ሻላ አለም አቀፍ ማተሚያ ድርጅት፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፡፡

ዳንኤል ክብረት፡፡ 2005፡ የኔ ጀግና እና ሌሎች፡፡ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃ/የተ. የግ.ማኅበር፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፡፡

ጌታሁን አማረ፡፡ 1989፡፡ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ፡፡ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፡፡

የላምባዲና ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል(ኢቫምፓ)፡፡ 2002 ዓ.ም፡፡ ላምባዲና፡፡ ቅጽ 4፣ ቁጥር 39፡፡

የአዲስ ጉዳይ መጽሔት ዝግጅት ክፍል፡፡ 2006 ዓ.ም፡፡ አዲስ ጉዳይ ልዩ ዕትም፡፡ ቅጽ 7፣ ቁጥር 191፡፡

International Journal of Education and Research, December 2014, E-learning, Vol. 2, No. 12

Matthijs Alink and Victor Van Kommer, 2016, Hand book on Tax Administration (Second Revised Edition), IBFD print books.Unicef, September 2017, Inclusive Education.

World Health Organization, 2018, NONCOMMUNICABLE DISEASES COUNTRY PROFILES

WWW. Daniel Kibret.com

## ሙዳየ ቃላት

መጋራት (Think-aloud)፡- በአርዓያነት እያነበቡ እያሉ በተወሰነ የጊዜ ልዩነት ቆም እያሉ ስለ አንድ ነገር/ጉዳይ እንዴት እያሰብን እንደሆነ ለሌላ ሰው ሀሳብን ማካፈል፣

መለየት/ማንበብ (Decoding)፡- የተጻፉ ቃላትን (ጽሑፍን) ወደ ንግግር ቋንቋ ለመቀየር የፊደል ድምፅ ግንኙነትንና የቃላት ዕውቀትን መጠቀም፣

መላልሶ ማንበብ (Repeated reading)፡- በትክክለኛና በፍጥነት የማንበብ ችሎታን ለማጎልበት መልሶ ምገባ እየታገዙ ደጋግሞ የማንበብ ሂደት

መልሶ ማንበብ (Re-read)፡- በማንበብ ሂደት ግልጽ ያልሆነ ጉዳይ ሲያጋጥም ሀሳቡን መረዳት እስኪቻል ድረስ ወደ ኋላ እየተመለሱ ማንበብ፣

መልዕክት ሰጪ ንባብ (Prosody)፦ አንድ ጽሁፍ በትክክለኛው ወይም በተገቢው የድምፅ ቅላፄ ማንበብ፣

መምህር መር ንባብ (Guided Reading)፦ ለደረጃው የቀረበውን ጽሑፍ በትክክል ማንበብ እንዲቻል መምህራን አንብበው በማሳየት ንባቡን የሚያስቀጥሉበት ሂደት፣

መረዳት(Comprehension)፡- የንግግርን ወይም የጽሑፍን ቋንቋ የመረዳትና ትርጉም የማግኘት ሂደት፣

መነጠል (Segmenting)፡- አንድን ሙሉ  ቃል ወይም ሐረግ በተናጠላዊ ፊደሎች ወይም በአነስተኛ የቃል ክፍልፋዮች የመነጣጠል ሂደት

መገመት (prediction)፡- ከማንበብ/ከማዳመጥ በፊት ወይም በማንበብ/በማዳመጥ ሂደት ቀጥሎ ምን ሊመጣ ወይም ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት፤ ስለገፀ ባህርያቱና ስለሴራው ድምዳሜ መስጠት፣

የማዳመጥ ቃላት (Listening vocabulary)፡- ሰዎች በንግግር ጊዜ አዳምጠው የሚረዷቸው ቃላት፣

ማጠቃለል/ማሳጠር (Summarizing)፡- የምንባብን አቢይ ሀሳብ ጨምቆ የማውጣት ሂደት፣

ማጣመር (blending)፡- በአነስተኛ ክፍልፋዮች ወይም ፊደሎች ተነጣጥሎ የቀረበን ቃል በአንድ ላይ አጣምሮ የመናገር፣ የማንበብ ወይም የመጻፍ ሂደት፣

ራስን የመከታተያ ስልት (Self-checking strategy)፡- ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ መረዳታቸውን የሚያረጋግጡበት ብልሃት፣

ቃላት በደቂቃ (ቃበደ)  (WPM)፡- በአንድ ደቂቃ በፍጥነት የተነበቡ ቃላት ብዛት፣ በአንድ ደቂቃ በትክክል የተነበቡ ቃላት ብዛት (WCPM ቃላት ትክክል በደቂቃ (ቃትበደ))፣ (የተማሪዎችን የማንበብ ብቃት ደረጃ ለመወሰን ያገለግላል፡፡)

ቃላት ትንተና (Word analysis)፡- አንባቢዎች የተጻፉ ቃላትን በአነስተኛ ክፍልፋዮች ወይም ቅጥያዎች በመተንተን ለማንበብ የሚጠቀሙበት ስልት፣

ቅጥያ (Affix)፡- በቃል መጀመሪያ ወይም መጨረሻ የሚቀጠሉ ትርጉም አዘል ቅጥያዎች፣ (በቃል መጀመሪያ ሲቀጠሉ ቅድመ አምድ ቅጥያ (Prefix)፣ በቃል መጨረሻ ሲቀጠሉ ድህረ አምድ ቅጥያ (Suffix) ይባላሉ፡፡)

ቅጽበታዊነት (Automaticity)፡- ፊደላትን፣ ድምጾችንና ቃላትን ያለ ችግር፣ ሳያመነቱ፣ ሳያወላውሉ፣ በቅጽበትና በትክክል የመለየትና የማንበብ ችሎታ፣

ቀጥተኛ ጥያቄ (Explicit question)፡- መልሱ በቀጥታ ከምንባብ ወይም ከንግግር የሚገኝ ጥያቄ ዓይነት፣

ቃላትን መረዳት/ ማወቅ (Word Recognition)፡- አንባቢዎች የተጻፉ ቃላትን ለመለየት የሚጠቀሙበት ስልት

በማንበብ ሂደት መቆምና ማሰብ (Stop and think)፡- በማንበብ ሂደት ምን እየተነበበ እንደሆነ ቆም ብሎ ማሰብ፣ ስለተነበበው ምንባብ ምንም ነገር ማስታወስ ካልተቻለ ወደ ፊት ከማንበብ ይልቅ ቆም ብሎ የተነበበውን ሀሳብ በአዕምሮ ለመረዳት መሞከር፣

በቢጤ /በአቻ/መማማር (Peer tutoring)፡- ተማሪዎች ትምህርታዊ ክሂሎችን እርስ በርስ የሚማማሩበት ሂደት

የቢጋር ሠንጠረዥ (Graphic organizer)፡- የሀሳብን ግንኙነት በሥዕል ወይም በግራፍ ወይም በሠንጠረዥ የማደራጃ ስልት፣

በትብብር መማር (Cooperative learning)፡- አንድን የትምህርት ይዘት በጋራ እየተረዳዱ የመማር ሂደት፣

ቤት መምታት (Rhyme)፡- በተመሣሣይ ፊደሎች/ድምጾች የሚጨርሱ ቃላት /የግጥም ቤት/

በጋራ ማንበብ (Choral reading)፡- በርከት ያሉ ተማሪዎች አንድን ጽሑፍ በጋራ ሆነው ድምፅ በማሰማት የሚያነቡበት ስልት፣

ተራኪ ጽሑፍ (Narrative text)፡- ታሪክን በጊዜ ወይም በቦታ ወይም በድርጊት ቅደም ተከተል የሚያሳይ የጽሑፍ መዋቅር

የታሪክ መዋቅር (Story structure)፡- እንደ መቼት ፣ድርጊት፣ ሁነት፣ ችግርና መፍትሄ ያሉትን አላባውያን የሚያካትት የድርሰት መዋቅር

ትክክለኛነት (Accuracy)፡- አንድን ቃል ወይም ሐረግ ወይም ዓረፍተ ነገር ያለ ስህተትና ያለማወላወል የማንበብ ችሎታ፣

ንባብን ወደ ፊት መቀጠል (Read ahead)፡- አሻሚ ሀሳብ ሲያጋጥም ግልፅ እንዲሆን ወደ ፊት ያሉትን ዓረፍተ ነገሮች ማንበብ፤ የተወኑ ዓረፍተ ነገሮች ተነበው ሀሳቡ ግልፅ ካልሆነ ሌላ ስልት መፈለግ፣

አመራማሪ ጥያቄዎች (Implicit / inferential Questions)፡- ተማሪዎች በሚያነቡት/ በሚያዳምጡት ጽሑፍ ውስጥ ያሉ መረጃዎችን ከቀደመ ዕውቀታቸው ጋር በማገናኘት መልስ የሚሰጡባቸው የአንብቦ/ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

አስረጂ ጽሑፍ (Expository text)፡- መረጃ ሰጪ የሆነ ጽሑፍ ሆኖ ስለአንድ ርዕሰጉዳይ ወይም እውነት ለማስተማር/ለማስረዳት የሚያገለግል ጽሑፍ፣

አቀላጥፎ ማንበብ (Fluency)፡- ፊደላትን፣ ቃላትንና ሐረጋትን በትክክል፣ በፍጥነትና መልዕክት ሰጭ በመሆነ መንገድ የማንበብ ችሎታ፣

አንብቦ መረዳት (Reading comprehension)፡- አንድ ጽሑፍ አንብቦ የመረዳትና ትርጉም የማግኘት ችሎታ፣

አዕምሯዊ ምሥል (Mental picture)፡- የገፀ ባህርያት፣ የቦታና የሁነቶች ገለፃን በተመለከተ በአዕምሮ ምሥል እየፈጠሩ ማንበብ፣

አዳምጦ መረዳት (Listening comprehension)፡- ንግግርን ወይም ጽሑፍን አዳምጦ መረዳትና ትርጉም የመስጠት ችሎታ፣

የአጻጻፍ ስርዓት (Writing convention)፡- የፊደላትን ቅርጽ፣ አሰዳደር፣ የአጻጻፍ አቅጣጫና የሥርዓተ ነጥብን አጠቃቀም የሚያሳይ የአጻጻፍ ሥርዓት፣

ዋና ሀሳብ /አቢይሀሳብ/ (Main idea)፡- ከምንባብ ተጨምቆ የሚወጣ አቢይ ወይም ዋና ሀሳብ፣

ዐውድ (Context)፡- ለአንድ እንግዳ ቃል ፍቺ ፍንጭ የሚሰጡ ከቃሉ በፊት ወይም በኋላ የሚገኙ ቃላት፣ ሐረጋት ወይም ዓረፍተ ነገሮች፣

ዘውግ (Genre)፡- በልዩ መዋቅሩ ወይም ባህሪያቱ የሚታወቅ የጽሑፍ መዋቅር፤ ምሳሌ፡- ተውኔት፣ ገላጭ ድርሰት፣ ተራኪ ድርሰት፣

ዘዬ (dialect)፡- በንበት/በድምጽ፣ በቃል ወይም በሰዋስው የሚከሰት አካባቢያዊ የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነት፣

የጥንድ ንባብ (partner reading)፡- በጥንድ ሆኖ ተራ በተራ የማንበብ ሂደት

ጥያቄ መጠየቅ (ask question)፡- ጥያቄ እየጠየቁ ማንበብ፣ ምንባቡን ለመረዳት ይጠቅማል